# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-17)
- I. ለሰው ልጅ ጽድቅ በጽኑ ማስፈለጉ (1፥18—3፥20)
  - (ሀ) ለአሕዛብ ማስፈለጉ (1፥18-32)
  - (ለ) ለአይሁድ ማስፈለጉ (2፥1—3፥8)
  - (ሐ) ለሰው ልጅ ሁሉ ማስፈለጉ (3፥9-20)
- II. የእግዚአብሔር ክቡር የጽድቅ ችሮታ (3፥21—5፥21)
  - (ሀ) በእምነት ስለሚገኝ መዳን አጭር ገለጻ (3፥21-31)
  - (ለ) በእምነት ስለመዳን የአብርሃም አብነት (4፥1-25)
  - (ሐ) ጽድቅ የሚያስገኘው በረከትና አለኝታ (5፥1-11)
  - (መ) አዳምና ክርስቶስ ሲነጻጸሩ (5፥12-21)
    1. አዳም /ኀጢአት/ ኵነኔ/ ሞት
    2. ክርስቶስ /ጸጋ/ ጽድቅ/ ሕይወት
- III. ጽድቅ በእምነት ሲገለጽ (6፥1—8፥39)
  - (ሀ) ከኀጢአት ባርነት ነጻ መሆን (6፥1-23)
    1. ከክርስቶስ ጋር ለኀጢአት ሙት መሆን (6፥1-14)
    2. የጽድቅ ባሪያ ሆኖ ከክርስቶስ ጋር መኖር (6፥15-23)
  - (ለ) በሕግ ሥር ካለው ትግል ነጻ መሆን (7፥1-25)
  - (ሐ) በሕይወት መንፈስ ሕግ ነጻ መሆን (8፥1-39)
- IV. በእምነት የሚገኝ ጽድቅ፣ ከእስራኤል አንጻር (9፥1—11፥36)
  - (ሀ) የእስራኤል የእንቢተኝነት ችግር (9፥1—10፥21)
  - (ለ) የእግዚአብሔር ዕቅድ አሸናፊነት (11፥1-36)
- V. በእምነት መጽደቅ በተግባር ሲገለጽ (12፥1—15፥13)
  - (ሀ) አማኙና ቅድስና (12፥1-2)
  - (ለ) አማኙና ማኅበረሰብ (12፥3-21)
  - (ሐ) አማኙና መንግሥት (13፥1-7)
  - (መ) አማኙና የፍቅር ሕግ (13፥8—15፥13)

*መደምደሚያ* (15፥14—16፥27)

**ጸሐፊው፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የእግዚአብሔር ጽድቅ መገለጥ*

**የተጻፈበት** *ጊዜ፥ 57 ዓ.ም.*

*ታሪካዊ ዳራ*

ይህ የሮሜ መልእክት ከጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ ጥልቅ ሥነ መለኮታዊ እውነትን የያዘና ልብ ማራኪ ሲሆን ረጅምም ነው። ምናልባትም ከዐሥራ ሦስቱ መልእክቶቹ ቀዳሚ የሆነው በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ ይህንን የሮሜ መልእክት የጻፈው ለአሕዛብ ዓለም ከነበረው የሐዋርያነት ተልእኮ ጋር በተያያዘ መልኩ ነበር። የቤተ ክርስቲያንን

ትውፊት ቢቃረንም በሮም ያለች ቤተ ክርስቲያን በጴጥሮስም ሆነ በሌላ ሐዋርያ አልተመሠረተችም። የሮም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በጳውሎስ አገልግሎት ክርስቶስን ባመኑ የመቄዶንያና የእስያ ሰዎች፣ በጰንጠቈስጤ ዕለት ባመኑ አይሁድና ከአሕዛብ ወደ ይሁዳነት ገብተው በነበሩ አማኞች ሳይሆን አይቀርም (ሐሥ 2፥10)። ጳውሎስም ሮምን የሌላ ሐዋርያ ክልል እንደሆነች አድርጎ አልቈጠረም (ሮሜ 15፥20)።

ጳውሎስ በዚህ በሮሜ መጽሐፍ ላይ በሮም ላሉ አማኞች፣ ወንጌልን ይሰብክላቸው ዘንድ ብዙ ጊዜ ዕቅዶ እንደ ነበርና ደብዳቤውን እስከጻፈላቸው ጊዜ ድረስ ወደ እነርሱ መምጣቱ እንደተስተጓጐለበት ያረጋግጥላቸዋል (1፥13-15፤ 15፥22)። ወደ እነርሱ የሚመጣበትን ቀን እንደሚናፍቅና በፍጥነትም ለመምጣት ያለውን ዕቅድ ያረጋግጥላቸዋል (15፥23-32)።

ሦስተኛው ሚስዮናዊ ጉዞው መጠናቀቂያ ገደማ ላይ ደብዳቤውን በሚጽፍበት ጊዜ (15፥25-26 ከሐሥ 20፥2-3፤ ከ1ቆሮ 16፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ) ጳውሎስ በቆሮንቶስ በጋይዮስ ቤት በእንግድነት ተቀምጦ ነበር (ሮሜ 16፥23፤ 1ቆሮ 1፥14)። ይህንን የሮሜ መልእክት በረዳቱ ጤርጥዮስ አማካይነት ሲጽፍ (16፥22፤ በግምት 57/58 ዓ.ም. ጸደይ ወር፤ የሐሥ 20፥16) በወቅቱ ለጰንጠቈስጤ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ለመምጣትና በዚያውም ከአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት የሰበሰበውን ርዳታ ራሱ በግል በኢየሩሳሌም ለተቸገሩ ቅዱሳን ሊያበረክት ያቀደበት ጊዜ ነበር (15፥25-27)። ከዚያም በኋላ እግረ መንገዱን የሮምን ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘትና ከእነርሱም ድጋፍ በመቀበል የወንጌልን መልእክት ይዞ ወዲያውኑ በምዕራብ ወደሚገኘው ወደ እስጳንያ ለመሄድ ዕቅዶ ነበር (15፥24፡28)።

## ዐላማ

ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው ለሮም አገልግሎቱና ለእስጳንያ ተልእኮው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲሆን፥ ይህም ሁለት ዐላማ ነበረው፤ (1) እነዚህ በሮም ያሉ አማኞች ስለጳውሎስ መልእክትና ትምህርተ መለኮት የተዛባ ወሬ ሳይሰሙ ስላልቀሩ (ለምሳሌ፣ 3፥8፤ 6፥1-2፡15) ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የሰበከውን ወንጌል በጽሑፍ ማግለጡ አስፈላጊ እንደ ሆነ ስለተሰማው ነው። (2) በተጨማሪም በሮም ያሉ አይሁድ አሕዛብን በተመለከተ (ለምሳሌ፣ 2፥1-29፤ 3፥1፡9) እንዲሁም አሕዛብ አይሁድ በተመለከተ (ለምሳሌ፣ 11፥11-32) ካላቸው የተሳሳተ አመለካከት የተነሣ የተፈጠረውን ችግር ማረም ስለፈለገ ነው።

## ቅኝት

የሮሜ መልእክት ዐቢይ ሐሳብ በምዕራፍ 1፥16-17 ባለው ክፍል ተጠቅሶአል፤ ይህም በኀጢአት ላይ ለወረደው የእግዚአብሔር ቍጣ መፍትሔ በመሆን በጌታ ኢየሱስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። ከዚህ በኋላ፣ ጳውሎስ የወንጌልን መሠረታዊ እውነት ያቀርባል። በመጀመሪያ ኀጢአት ያስከተለውን አበሳና ለሰው ልጅም ጽድቅ የማስፈለጉ ጉዳይ ዓለም አቀፋዊ መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል (1፥18—3፥20)። አይሁድም ሆኑ አሕዛብ በኀጢአታቸው የተነሣ ከእግዚአብሔር ቍጣ ሥር በመውደቃቸው፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በእምነት ከሚሰጠው ጽድቅ በቀር አንድም ሰው እንኳ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ መገኘት አይችልም (3፥21—4፥25)።

በእምነት በኩል በሚሆን ጸጋ በነጻ ከጸደቅን፥ የመዳንንም አለኝታ ከተቀበልን (ምዕ 5)፣ የእግዚአብሔር የጽድቅ ስጦታ በክርስቶስ ሆነን ለኀጢአት በመሞታችን (ምዕ 6)፣ በሕግ ከሚገኘው ጽድቅ ጋር ካለን ግብግብም አርነት በመውጣታችን (ምዕ 7)፣ ወደ እግዚአብሔር ልጅነትና በመንፈስም ወደሚሆን አዲስ ሕይወት ተሸጋግረን ወደ ፍጽመተ ድኅነት በማምራታችን (ምዕ 8) ተገልጧል። እስራኤል ያላመነች ብትሆንም እንኳ እግዚአብሔር የድኅነት ዕቅዱን እያከናወነ ነው (ምዕ 9—11)።

በመጨረሻም ጳውሎስ በክርስቶስ ኢየሱስ የተለወጠ ሕይወት በማኅበራዊ፣ በአስተዳደራዊና በግብረገባዊ ረገድ ሁሉ ጽድቅንና ፍቅርን በተግባር መግለጥ እንደሚገባው ያስረዳል (ምዕ 12—14)፤ ይህንንም የሮሜ መልእክቱን የግል ዕቅዱን በማብራራትና (ምዕ 15) ለበርካታ ሰዎች ሰላምታ በማቅረብ ከዚያም ማሳሰቢያና ቡራኬ በማድረግ ይደመድማል (ምዕ 16)።

## ልዩ ገጽታ

የሮሜን መልእክት ልዩ የሚያደርጉት ስባት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) የሮሜ መልእክት በእጅጉ ሥርዐትን ተከትሎ የተጻፈ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥልቅ የሆነ ትምህርተ መለኮታዊ ይዘት አለው። (2) ጳውሎስ የጻፈው በጥያቄና መልስ ወይም የክርክር ስልት ባለው አቀራረብ ነው (ለምሳሌ፣ (3፥1፡4-6፡9፡31)። (3) ሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌልን

እውነተኛ ባሕርይ በሚገልጥበት ጊዜ ብሉይ ኪዳንን የመልእክቱ ዋና ምንጭ አድርጎ በሰፊው ተጠቅሞበታል። (4) ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል ያለው ትልቁ መገለጥ፣ “ከእግዚአብሔር የተገኘ ጽድቅ” እንደ ሆነ ይገልጻል (1፥16-17)፤ ይኸውም እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ ያስተካከለው በክርስቶስ በኩልና በእርሱ ውስጥ መሆኑን ብቻ ነው። (5) በሁለቱም አቅጣጫ ላለው ኀጢአት እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ከለገሰው ቸርነት ጋር ጐን ለጐን አድርጎ በማቅረብ ጳውሎስ በሁለት ዐይነት የኀጢአት ባሕርይ ላይ ያተኩራል፤ (ሀ) በግል መተላለፍ የሚደረግ ኀጢአት (1፥1—5፥11)፤ (ለ) አዳም ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ በሰው ሁሉ ልብ ያለው በውርስ የተገኘው ኀጢአትን የማድረግ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ሲሆን (5፥12—8፥39)፣ በግሪክ “ኼ ሃማርሺያ” ይባላል። (6) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ስላለው ድርሻ ከተገለጠው ሁሉ ሮሜ ምዕ 8 ሰፊ መግለጫ የሚሰጥ ክፍል ነው። (7) የሮሜ መልእክት ከቀሬታዎች በቀር አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ስላለመቀበላቸው ጠንከራ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ የሚያቀርብና በኋላም እስራኤልንም ስለሚያካትተው ሁሉን አቀፍ ስለሆነው የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው (ምዕ 9—11)።

## የሮሜን መልእክት ማንበብ

መሉውን አዲስ ኪዳን በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሮሜ መልእክት በ21 ቀናት መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1፥1-17 ❑ 1፥18-32 ❑ 2 ❑ 3 ❑ 4 ❑ 5 ❑ 5፥12-21 ❑ 6፥1-14 ❑ 6፥15—7፥6 ❑ 7፥7-25 ❑ 8፥1-17 ❑ 8፥18-39 ❑ 9፥1-29 ❑ 9፥30—10፥21 ❑ 11፥1-24 ❑ 11፥25-36 ❑ 12፥1-16 ❑ 12፥17—13፥14 ❑ 14፥1—15፥4 ❑ 15፥5-33 ❑ 16

### ማስታወሻ

1 ጳውሎስ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ፣
ሐዋ ርያ ሊሆን የተጠራና ለእግዚአብሔር
ወንጌል የተለየ፤ 2ስለዚህ ወንጌል በነቢያቱ
በኩል በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ
ተሰጠ። 3ወንጌሉም ስለ ልጁ፣ በሥጋ
ከዳዊት ዘር ስለ ሆነ፣ 4በቅድስና መንፈስ[ሀ]
ደግሞ ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ
መሆኑ በኀይል ስለ ተገለጠው[ለ] ስለ ጌታችን
ኢየ ሱስ ክርስቶስ ነው። 5በእርሱ በኩል
ስለ ስሙ ከአሕዛብ ሁሉ መካከል ሰዎችን
በእምነት አማካይነት ወደሚገኘው መታዘዝ
ለመጥራት ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን።
6እናንተ ራሳችሁም ለኢየሱስ ክርስቶስ
እንዲሆኑ ከተጠሩ መካከል ናችሁ።
7በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን
ለመሆን ለተጠራችሁ በሮም ላላችሁ ሁሉ፤
ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢየሱስ
ክር ስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## ሮምን ለማየት የ ጳውሎስ ናፍቆት

8ከሁሉ አስቀድሜ፣ እምነታችሁ በዓለም
ሁሉ በመሰማቱ፣ ስለ ሁላችሁም አምላኬን
በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ። 9ዘወትር
ምን ያህል እንደማስባችሁ፣ የልጁን
ወንጌል በመስበክ በሙሉ ልቤ የማገለግለው
እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፤ 10በጸሎቴ ሁልጊዜ
አስባ ችኋለሁ፤ አሁን ደግሞ በመጨረሻ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እናንተ እንድመጣ
መንገድ ይከፈትልኝ ዘንድ እጸልያለሁ።
ሮሜ 12፥6-8 11እንድትጸኑ የሚያስችላችሁን መንፈሳዊ
ስጦታ አካፍላችሁ ዘንድ፣ ላያችሁ
እናፍቃለሁ። 12ይኸውም እናንተና እኔ
በእያንዳን ዳችን እምነት እርስ በርሳችን
እንድንበረታታ ነው። 13ወንድሞች ሆይ፤
በሌሎች አሕዛብ ዘንድ እንደ ሆነልኝ፣
በእናንተም ዘንድ ፍሬ ለማግኘት ብዙ ጊዜ ወደ
እናንተ ልመጣ ዐቅጄ ሳለሁ፣ እስከ አሁን ድረስ
ግን መከልከሌን እንድታውቁ እወዳለሁ።
14ግሪኮች ለሆኑትና ላልሆኑት፣
ለጥበበኞችና ለማያስተውሉ፣ ዕዳ አለብኝ፤
15በሮም ለምትኖሩ፣ ለእናንተም ወንጌልን
ለመስበክ የምጓጓው ለዚህ ነው።
16በወንጌል አላፍርም፤ ምክንያቱም
ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር
ኀይል ነው፤ ይህም በመጀመሪያ ለአይሁድ፣
ቀጥሎም ለአሕዛብ ነው። 17በወንጌል
የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፤ ጽድቁም
ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት[ሐ]
የሆነ ነው፣ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል"
ተብሎ እንደ ተጻፈው።

## የእግዚአብሔር ቍጣ በሰዎች ላይ

18በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው
በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ

1፥1 ሐሥ9፥15፤ ሮሜ15፥16፤ 1ቆሮ1፥1፤ 2ቆሮ2፥12፤ 11፥7፤ 1ተሰ2፥8፡9፤ 1ጴጥ4፥17
1፥2 ሉቃ1፥70፤ ሐሥ13፥32፤ ቲቶ1፥2፤ ሮሜ3፥21፤ ገላ3፥8
1፥3 ማቴ1፥1፤ ዮሐ1፥14፤ ሮሜ9፥5
1፥4 ማቴ4፥3፤ ሐሥ2፥24፤ 1ቆሮ1፥2
1፥5 ሐሥ9፥15፤ 6፥7፤ ሮሜ16፥26፤ 1ጢሞ1፥14
1፥6 ይሁዳ1፤ ራእ17፥14
1፥7 ሐሥ9፥13፤ ሮሜ8፥39፤ 1ቆሮ1፥3፤ ኤፌ1፥2፤ 1ተሰ1፥4፤ 1ጢሞ1፥2፤ ቲቶ1፥4፤ 1ጴጥ1፥2
1፥8 ሮሜ10፥18፤ 16፥19፤ 1ቆሮ1፥4፤ ኤፌ1፥16፤ 1ተሰ2፥13፤ 2ተሰ1፥3፤ 2ጢሞ1፥3
1፥9 ኢዮ16፥19፤ ኤር42፥5፤ 2ቆሮ1፥23፤ ገላ1፥20፤ ፊል1፥8፤ 1ተሰ2፥5-10፤
1፥9 2ጢሞ1፥3 1፥10 ቆላ1፥3፤ 1ሳሙ12፥23፤ ሉቃ18፥1፤ ሐሥ1፥14፤ ሐሥ18፥21፤ ሮሜ15፥32፤ ኤፌ1፥16፤ ፊል1፥4፤ ቆላ1፥9፤ 2ተሰ1፥11፤ 2ጢሞ1፥3፤ ፊሞ1፥4
1፥11 ሮሜ15፥23፤ 1ቆሮ1፥7፤ 12፥1-31 1፥13 ሮሜ11፥25፤ 7፥1፤ 15፥22፡23 1፥14 1ቆሮ9፥16 1፥15 ሮሜ15፥20 1፥16 ዮሐ3፥15፤ ሐሥ3፥26፤ 13፥46፤ ሮሜ2፥9፡10፤ 1ቆሮ1፥18፤ 2ጢሞ1፥8 1፥17 ዕን2፥4፤ ሮሜ3፥21፤ 9፥30፤ ፊል3፥9፤ ገላ3፥11፤ ዕብ10፥38 1፥18 ዮሐ3፥36፤ ሮሜ5፥9፤ ኤፌ5፥6፤ ቆላ3፥6፤ 1ተሰ1፥10፤ ራእ19፥15

*ሀ 1፥4 ወይም በቅድስናው መንፈስ*
*ለ 1፥4 ወይም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተሾመ*
*ሐ 1፥17 ወይም ከእምነት ወደ እምነት*

1፥4 **በቅድስና መንፈስ፤** የ"ቅድስና መንፈስ" ሲል የሚያመለክተው የሥላሴ አንዱ አካል የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ነው። ቅድስናው ከሰው መንፈስ፣ ከኀጢአትና ከዓለም የተለየ የሚያደርገው ሲሆን ከፍ ያለውን ባሕርይውንም ሆነ ሥራውን ይገልጣል (ከገላ 5፥16-24 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥5 **በእምነት ... መታዘዝ፤** ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በመጀመሪያውና በመደምደሚያው ላይ እምነትን የገለጸው ከ"መታዘዝ" አንጻር እንደ ሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል (16፥26)። ጳውሎስ እንደሚለው ለድነት የሚያበቃው እምነት የሚወሰነው በቅድሚያ በሚደረጉ መሠረታዊ ነገሮች ነው፤ እነዚህም በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በፍቅር ሕይወትን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት፣ ሙሉ በሙሉ ልብን ማስገዛት፣ ምስጋና ማቅረብና መታዘዝ ናቸው ያዕ (2፥17 እና ማብ ይም፤ ከዮሐ 15፥10፡14፤ ከዕብ 5፥8-9 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ "*እምነትና ጸጋ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

1፥7 **ቅዱሳን ለመሆን ለተጠራችሁ፤** አማኞች ከኀጢአትና ከዓለም ተለይተው (ከቍ 1 ጋር ያነጻጽሩ) ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ የተደረጉና ለአገልግሎቱም የተቀደሱ ናቸው (ዘፀ 19፥6 እና ማብ፤ ዘሌ 11፥44 እና ማብ ይመ)። በዚህ የመለየት ሥራው መንፈስ ቅዱስ የአማኙን ባሕርይ በእውነተኛ ቅድስና ያድሳል (ሐሥ 9፥13 እና ማብ ይመ፤ ከ4፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 2000 ላይ፣ "*መቀደስ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

1፥16 **ድነት፤** "ድነት" ስለሚለው ቃል ፍቺና ድነትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚጠቀምባቸው ሌሎች ሁለት ቃላት ለመረዳት በገጽ 1735 ላይ፣ "*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

1፥17 **ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት፤** ጻድቅ ሰው በእምነት መኖሩን ይቀጥላል፤ ይህንንም በማድረጉ ከአንድ የእድገት ደረጃ ወደ ሌላ የእድገት ደረጃ ይሸጋገራል። በዚህም መንገድ፣ አማኙ የበለጸገ መንፈሳዊ ሕይወት ይኖረው ዘንድ በጽድቅ ጐዳና ላይ ወደፊት ይራመዳል (8፥12-13፤ 14፥13-23፤ ዕብ 10፥38 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ "*እምነትና ጸጋ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

1፥18 **የእግዚአብሔር ቍጣ፤** የእግዚአብሔር ቍጣ (በግሪክ ኦርጌ) የጽድቁና የፍቅሩ መግለጫ ነው (በገጽ 908 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር ባሕርያት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። በሰዎች ክፉ ባሕርይ (ዘፀ 4፥14፤ ዘኍ 12፥1-9፤ 2ሳሙ 6፥6-7)፣ በአገሮች ጠማማ አካሄድ (ኢሳ 10፥5፤ 13፥3፤ ኤር 50፥13፤ ሕዝ 30፥15) እና በእግዚአብሔር ሕዝብ ታማኝ አለመሆን (ዘኍ 25፥3፤ 32፥10-13፤ ዘዳ 29፥24-28) የሚነሣሣ የእግዚአብሔር የግል ቍጣና በኀጢአት ላይ የሚሰጥ የማይቀር ፍርድ ነው (ሕዝ 7፥8-9፤ ኤፌ 5፥6፤ ... ራእ 19፥15)።

# ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት

*ሮሜ 1፥16 "በወንጌል አላፍርም፤ ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤ ይህም በመጀመሪያ ለአይሁድ፥ ቀጥሎም ለአሕዛብ ነው።"*

---

እግዚአብሔር እንዲሁ በነጻ የዘላለምን ሕይወት በክርስቶስ ኢየሱስ ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ ይህን ሕይወት ያገኘንበትን ትክክለኛውን ሂደት መገንዘቡ አንዳንድ ጊዜ ቀላል አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን ግንዛቤ እንጨብጥ ዘንድ የየራሳቸው ልዩ ትኩረት ያላቸውን ሥዕላዊ መግለጫዎች አቅርቦልናል። ይህ ጽሑፍ ልዩ ትኩረት ካላቸው ሥዕላዊ መግለጫዎች ሦስቱን ያቀርብልናል፥ እነርሱም ድነት፣ መቤዠትና ጽድቅ ናቸው።

ድነት፤ በግሪኩ ቃል ሶቴሪያ የሚል ሲሆን፥ ትርጕሙም "ትድግና" "በሰላም ጠብቆ ማድረስ"፣ "ከጕዳት መጠበቅ" ማለት ነው፤ ቀድሞም ቢሆን እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ሕዝቡን የሚያድን አምላክ መሆኑን ገልጧል (መዝ 27፥1፥ 88፥1፤ ዘጸ 26፥8 እና ማብ፤ መዝ 62፥1 እና ማብ፤ ኢሳ 25፥6 እና ማብ፤ ኢሳ 53፥5 እና ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳንም ድነት፣ ሰው ሕይወትን አግኝቶ በሰማይ ካለ ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ኅብረት ሊያገኝ የሚችልበት "መንገድ" እንደሆነ ተገልጧል (ማቴ 7፥14፥ ማር 12፥14፤ ዮሐ 14፥16፤ ሐሥ 16፥17፥ 2ጴጥ 2፥2፡21 ይመ፤ ከሐሥ 9፥2፤ 22፥4 እና ከዕብ 10፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ የድነት መንገድ እስከ ፍጻሜ ድረስ ሊሄዱበት የሚገባ ነው። ድነት ከሁለት አቅጣጫ የሆነ ሦስት ደረጃ ያለው አንድ መንገድ አድርገን ልንገልጸው እንችላለን።

(1) አንዱና ብቸኛው የድነት መንገድ፤ ክርስቶስ ወደ አብ የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ነው (ዮሐ 14፥6፤ ሐሥ 4፥12)። ድነት በእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ የተሰጠ ሲሆን (ሮሜ 3፥24)፥ ይህም የሆነው በሞቱና (3፥25፤ 5፥8) በትንሣኤው (5፥10) እንዲሁም ለአማኞች በሚያደርገው የማያቋርጥ ምልጃው ነው (ዕብ 7፥25)።

(2) የድነት ሁለት አቅጣጫዎች፥ ድነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመን በጸጋ ነው (ሮሜ 3፥22፡24-25፡28)፤ ይህም በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት (ዮሐ 1፥16) እንዲሁም ሰው በሚያደርገው የእምነት ውሳኔ የሚሆን ነው (ሐሥ 16፥31፥ ሮሜ 1፥17፤ ኤፌ 1፥15፤ 2፥8 እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) ሦስቱ የድነት ደረጃዎች፥

(ሀ) ያለፈው ኀጢአት የተሰጠ የድነት ደረጃ እንደ አማኝነታችን በግላችን የኀጢአትን ይቅርታ የተቀበልንበትንና (ሐሥ 10፥43፤ ሮሜ 4፥6-8) ከመንፈሳዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት (1ዮሐ 3፥14፤ በገጽ 1606 ላይ፣ "ዳግም ልደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ ከኀጢአት ኀይል ወደ ጌታ ኀይል (ሮሜ 6፥17-23)፣ ከሰይጣን ግዛት ወደ እግዚአብሔር ግዛት (ሐሥ 26፥18), የተሸጋገርንበትን የሚያጠቃልል ነው። ይህ ድነት ከእግዚአብሔር ጋር ወደሚሆን አዲስ ኅብረት ያመጣናል (ዮሐ 1፥12) ከኀጢአትም ቅጣት ይታደገናል (ሮሜ 1፥16፥ 6፥23፤ 1ቆሮ 1፥18)።

(ለ) አሁን በመፈጸም ላይ ያለው ኀጢአት የሚሰጥ የድነት ደረጃ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት በኀጢአት ከመታሰርና ከመለማመድ ያድነናል። ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፥ (1) ከእግዚአብሔር ጋር እንደ አባታችን ከኢየሱስም ጋር እንደ ጌታችንና እንደ አዳኛችን በግል ሊኖረን የሚገባውን ኅብረት የማግኘት ዕድል (ማቴ 6፥9፤ ዮሐ 14፥18-23 እንዲሁም ገላ 4፥6 እና ማብ ይመ)፣ (2) ራሳችንን ለኀጢአት ሙት አድርገን የምንቈጥርበትን ጥሪ (ሮሜ 6፥1-14) እና ለመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ለእግዚአብሔር ቃል መገዛታችን (ሮሜ 8፥1-17፤ ዮሐ 8፥31፥ 14፥21፤ 2ጢሞ 3፥15-16)፣ (3) ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መጠራታችንንና በየጊዜው በቀጣይነት ለመሞላት የተሰጠው ትእዛዝ (ሐሥ 2፥33-39፤ ኤፌ 5፥18 በገጽ 1664 ላይ፣ "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ (4) ከተበላሸው ከአሁኑ ትውልድና (ሐሥ 2፥40፤ 2ቆሮ 6፥17) ከኀጢአት ራሳችንን እንድንለይ ያለብንን ግዴታ (ሮሜ 6፥1-14) እንዲሁም (5) ሰይጣንና አጋንንታዊ ሰራዊቱ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ የሚያደርጉትን ጦርነት እንድንዋጋ ያለብንን ጥሪ (2ቆሮ 10፥4-5፤ ኤፌ 6፥11፡16፤ 1ጴጥ 5፥8)።

(ሐ) የድነት የወደፊቱ ሂደት (ሮሜ 13፥11-12፤ 1ተሰ 5፥8-9፤ 1ጴጥ 1፥5) የሚከተሉትን

ያካትታል፤ (1) ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቍጣ ትድግና ማግኘታችን (ሮሜ 5፥9፤ 1ቆሮ 3፥15፤ 5፥5፤ 1ተሰ 1፥10፤ 5፥9)፤ (2) መለኮታዊውን ክብር በሙላት መካፈላችንና (ሮሜ 8፥29፤ 1ቆሮ 15፥49) የተለወጠውን የትንሣኤ አካል መቀበላችን (1ቆሮ 15፥52) እንዲሁም (3) እንደ ታማኝ ድል ነሺዎች የምንቀበለውን ሽልማት (ራእ 2፥7 እና ማብ ይመ)። ይህ መጪው ድነት ክርስቲያኖች ሁሉ የሚጋደሉለት የወደፊት ግብ ነው (1ቆሮ 9፥24-27፤ ፊል 3፥8-14)። አሁን የሚሰጡት ማስጠንቀቂያዎች፣ እርማቶችና ቅጣቶች በሳማቸው አማኞች መጪውን ድነታቸውን እንዳያጡ ለማድረግ ነው (1ቆሮ 5፥1-13፤ 9፥24-27፤ ፊል 2፥12፥16፤ 2ጴጥ 1፥5-11 ይመ፤ ዕብ 12፥1 እና ማብ ይመ)።

**መቤዠት፤** በግሪኩ አፖሉትሮሲስ ሲሆን፣ የሥርወ ቃሉ ትርጕም በዋጋ ክፍያ መግዛት ማለት ነው። ይህ አገላለጽ የሚያመለክተን ድነት የተገኘው በዋጋ ክፍያ መሆኑን ነው። የመቤዠት አስተምህሮ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ሊቀርብ ይችላል፤

(1) ለንቤዠበት የተገባው የኀጢአታችን ሁኔታ፤ አዲስ ኪዳን ስለ ሰው ሁኔታ ሲገልጥ፣ ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ መለየቱን (ሮሜ 3፥10-18)፣ በሰይጣን ኀይላት ግዛት ሥር መውደቁን (ሐሥ 10፥38፤ 26፥18) ለኀጢአት ባሪያ መሆኑን (ሮሜ 6፥6፤ 7፥14) ከኀጢአት ኀይል፣ ከመቀሳውና ከቅጣቱ አርነት መውጣት እንደሚያስፈልገው (ሐሥ 26፥18፤ ሮሜ 1፥18፤ 6፥1-18፥23፤ ኤፌ 5፥8፤ ቈላ 1፥13፤ 1ጴጥ 2፥9) ያመለክታል።

(2) ከዚህ እስራት ነጻ እንወጣ ዘንድ የተከፈለው ዋጋ፤ ክርስቶስ ይህንን ዋጋ የከፈለው ደሙን በማፍሰስና ሕይወቱን በመስጠት ነው (ማቴ 20፥28፤ ማር 10፥45፤ 1ቆሮ 6፥20፤ ኤፌ 1፥7፤ ቲቶ 2፥14፤ ዕብ 9፥12፤ 1ጴጥ 1፥18-19)።

(3) የተቤዡት ሰዎች የድነታቸው ውጤት፤ በክርስቶስ የተቤዡት አማኞች፣ አሁን ከሰይጣን አገዛዝ ከኀጢአትና ከበደል ኀይል ነጻ ናቸው (ሐሥ 26፥18፤ ሮሜ 6፥7፥12፥14፥18፤ ቈላ 1፥13)። ይሁን እንጂ፣ ከኀጢአት ነጻ መሆናችን ያሻንን እንድንፈጽም አያደርገንም፤ በእኛ ላይ በሰመብቱ እግዚአብሔር ነውና። ከኀጢአት ነጻ መሆናችን በፈቃዳችን ለእግዚአብሔር የምንገዛ ባሪያዎች አድርጎናል (ሐሥ 26፥18፤ ሮሜ 6፥18፥22፤ 1ቆሮ 6፥19-20፤ 7፥22-23)።

(4) በብሉይ ኪዳን የመቤዠት ትምህርት ጥላነት የተጠቀሰው የአዲስ ኪዳን የመቤዠት ትምህርት፤ ታላቁ የብሉይ ኪዳን የመቤዠት ኹነት ከግብጽ የመውጣት ሁኔታ ነበር (ዘፀ 6፥7 እና ማብ፤ 12፥26 እና ማብ ይመ)። ከዚህ በተጨማሪ፣ በመሥዋዕቱ ሥርዐት ውስጥ የእንስሳት ደም ለኀጢአት ሥርየት የሚከፈል ዋጋ ነበር (ዘሌ 9፥8 እና ማብ በገጽ 202 ላይ፣ "የሥርየት ቀን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**ማጽደቅ፤** "ማጽደቅ" (በግሪኩ ዲካዮ) የሚለው ቃል ትርጕም "በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን" (ሮሜ 2፥13)፤ "ማጽደቅ" (ሮሜ 5፥18-19) "ትክክል አድርጎ መቍጠር"፣ "ትክክል ማድረግ ወይም በትክክል ማስቀመጥ" ማለት ነው። ቃሉ የሚያመለክተው በፍርድ ቤት ከወንጀል ነጻ በመሆን የሚገኝን ትክክለኛነት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ትክክለኛ ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር በሕጉ መሠረት በደለኞች በመሆናቸው የዘላለም ሞት የተፈረደባቸውን ንስሓ የገቡ ኀጢአተኞችን ወደ መለኮታዊ ፍቅሩ በመመለስ ከእርሱና ከፈቃዱ ጋር ወዳለው ትክክለኛ ኅብረት ያመጣቸዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጽድቅና ስለ አፈጻጸሙ አያሌ እውነትን አቅርቦአል፤

(1) በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅ ስጦታ ነው (ሮሜ 3፥24፤ ኤፌ 2፥8)። በሮሜ 3፥23 ላይ "ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል" ስለሚል፣ ማንም ቢሆን ሕግን በመፈጸም ወይም በበጎ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን አይችልም (ሮሜ 4፥2-6)።

(2) በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ መገኘት፤ "በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል" የተፈጸመ ነው (ሮሜ 3፥24)። ማንም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛነት ከኀጢአትና ከኀጢአት ኀይል ነጻ ካልወጣ በቀር አልጸደቀም።

(3) በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን የሚቻለው፣ "በእርሱ ጸጋ" ሲሆን፣ የሚገኘውም ጌታና አዳኝ አድርጎ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ነው (ሮሜ 3፥22-24 ይመ፤ ከ4፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1746 ላይ፤ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆነን መገኘታችን ለኀጢአታችን ካገኘነው ይቅርታ ጋር የተገናኘ ነው (ሮሜ 4፥7)። ኀጢአተኞች በደለኞች ተብለዋል (ሮሜ 3፥9-18፥23)፤ ይሁን እንጂ ከሚያስተሰርየው የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተነሣ ይቅር ተብለዋል (ሮሜ 3፥25 እና ማብ፤ 4፥5 እና ማብ ይመ፤ 4፥25፤ 5፥6-11)።ስ

(5) በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆነን ስንገኝ፣ ከክርስቶስ ጋር

ተሰቅለናል፤ ክርስቶስም መጥቶ በእኛ ውስጥ ይኖራል (ገላ 2፥16-21)። በዚህ ሁኔታ ጻድቃን እንሆናለን፡ ለእግዚአብሔርም እንኖራለን (2፥19-21)። ክርስቶስ ሕይወታችንን በመንፈስ ቅዱስ የመለወጡ ጉዳይ (ከ2ተሰ 2፥13፤ ከ1ጴጥ 1፥2 ጋር ያነጻጽሩ) ክርስቶስ ለእኛ ካደረገው የቤዛነት ሥራ ተነጥሎ አይታይም፤ የክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አይነጣጠሉምና።

ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤
19 ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው
ለእነርሱ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር
ለእነርሱ ግልጽ አድርጎታል። 20 ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር
ባሕርይ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና
መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፤
ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም።
21 እግዚአብሔርን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ
አምላክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም
አላቀረቡለትም፤ ነገር ግን ሐሳባቸው ፍሬ
ቢስ ሆነ፤ የማያስተውል ልባቸው ጨለመ።
22 ጥበበኞች ነን ቢሉም፣ ሞኞች ሆኑ፤
23 የዘላለም አምላክን ክብር ምዉት በሆነው
ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ
በሚሳቡ ፍጥረት መልክ መሰለው ለወጡ።
24 ስለዚህም እግዚአብሔር በኀጢአት
በተሞላው የልባቸው ምኞት እርስ በርሳቸው
የገዛ አካላቸውን እንዲያስነውሩ ቅድስና
ለሌለው ርኩሰ ሥጋ አሳልፎ ሰጣቸው።
25 የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ፤
በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር አመለኩ፤ አገለገሉም፤

1፥19 ሐሥ14፥17
1፥20 መዝ19፥1-6፤ ሮሜ2፥1
1፥21 ዘፍ8፥21፤ ኤር2፥5፤ 17፥9፤ ኤፌ4፥17፥18
1፥22 1ቆሮ1፥20፥27፤ 3፥18፥19
1፥23 ዘዳ4፥16፥17፤ መዝ106፥20፤ ኤር2፥11፤ ሐሥ17፥29
1፥24 ቍ26፥28፤ መዝ81፥12፤ ኤፌ4፥19፤ 1ጴጥ4፥3
1፥25 ኢሳ44፥20፤ ኤር10፥14፤ 13፥25፤ 16፥19፥20፤ ሮሜ9፥5፤ 11፥36፤ 2ቆሮ11፥31

(1) በቀደሙት ዘመናት የእግዚአብሔር ቍጣ የተገለጠው በጐርፍ (ዘፍ 6—8)፣ በራብና በቸነፈር (ሕዝ6፥11ለ)፣ ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ (ዘዳ 29፥22-23)፣ በመበተን (ሰቆ 4፥16) እና በምድር ቃጠሎ (ኢሳ 9፥18-19) ነበር።

(2) በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔር ቍጣ በደለኛውን ንጹሕ ሳልሆኑና ለነውረኛ ፍትወት አሳልፎ በመስጠት (ቍ 24 እና ማብ ይመ) እንዲሁም በማይታዘዙት ላይ ጥፋትንና ሞትን በማምጣት (1፥18—3፥20፤ 6፥23፤ ሕዝ 18፥4፤ ኤፌ 2፥3) ተገልጧል።

(3) በሚመጣው ዘመን የእግዚአብሔር ቍጣ በዚህ ዓለም ኀጢአተኞች ላይ የሚወርደውን ታላቅ መከራ (ማቴ 24፥21፤ ራእ 5፥19) እንዲሁም በሰዎችና በመንግሥታት ሁሉ ላይ የሚመጣን የፍርድ ቀን (ሕዝ 7፥19፤ ዳን 8፥19) ያካትታል፤ ይህም "የሁከትና የጥፋት ቀን፣ የጨለማና የጭጋግ ቀን" (ሶፎ 1፥15) እንዲሁም ኃጢአተኞች የሚቀጡበት ቀን (2፥5፤ ማቴ 3፥7፤ ሉቃ 3፥17፤ ኤፌ 5፥6፤ ቈላ 3፥6፤ ራእ 11፥18፤ 14፥8-10፤ 19፥15) ይሆናል። በመጨረሻም የእግዚአብሔር ቍጣ ያልገቡት ለዘላለም እንዲቃጠሉ ያደርጋል (ማቴ 10፥28 እና ማብ ይመ)።

(4) የእግዚአብሔር ቍጣ በሰው ልጆች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ አይደለም፤ እግዚአብሔር ማምለጫውን መንገድ አዘጋጅቷልና። አንድ ሰው ከኀጢአቱ ንስሓ ገብቶ በእምነት ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ሊቀርብ ይችላል (5፥8፤ ዮሐ 3፥36፤ 1ተሰ 1፥10፤ 5፥9፤ በገጽ 1735 ላይ፤ "*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(5) ከክርስቶስ ጋር የሆኑ አማኞች በቃል ሳይሆን በእውነት ጽድቅን በመውደድና ክፋትን በመጥላት ከእግዚአብሔር ቍጣ ጋር ሊተባበሩ ይገባል (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)። አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር የሚጠላውን እንዲጠላ የሚያደርገውን በኢየሱስ ክርስቶስ (ማር 3፥5፤ ዮሐ 2፥12-17፤ ዕብ 1፥9፤ ሉቃ 19፥45 እና ማብ ይመ)፤ በጳውሎስ (ሐሥ 17፥16) እና በሌሎች ጻድቃን ሰዎች (2ጴጥ 2፥7-8፤ ራእ 2፥6 እና ማብ ይመ) የተገለጠውን ቍጣ ይደግፋል።

**1፥21 አላከበሩትም፤** ምንም እንኳን ከቍ 21-28 ድረስ ያለው ክፍል ዳግም ባልተወለዱት ዘንድ ስላለው የባሕርይ ዝቅጠት ቢናገርም፣ ለክርስቲያን መሪዎች ውድቀት አንዱ የከፋ ኀጢአት የሆነው ርኩሰት ለምን እንደ ሆነ ማስረጃዎችን ይሰጣል (የሚቀጥለውን ማብራሪያ ይመ)።

(1) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትዕቢተኛ በሚሆኑበት ጊዜ (ቍ 22) ለራሳቸው ክብር ይፈልጋሉ (ቍ 21)፤ አልፎ ተርፎም ፈጣሪን ከፍ በማድረግ ፈንታ ራሳቸውን ከፍ ያደርጋሉ (ቍ 25)። ከዚህም የተነሣ በሕይወታቸው ለፍትወተ ሥጋና ለአስነዋሪ መሻት በር ይከፈታል (ቍ 24፥26፤ 2ጴጥ 2፥2 እና ማብ፤ 15 እና ማብ ይመ)። ካልተመለሱና ንስሓ ካልገቡ ለማይረባ አእምሮ አልፈው ይሰጣሉ (ቍ 28)።

(2) እነዚህ ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት እያደረጉ እንዳሉና ድነትን እንደጨበጡ ራሳቸውን በማሳመን እንደዚሁም አሳፋሪ ሥራቸው የተለመደ ሰብአዊ ድካም መሆኑን ለማስረዳት መሞከር በአስነዋሪ ኀጢአትና ምኞት ይቀጥላሉ። "ማንም አመንዝራ ወይም ርኩስ ወይም ስስታም ማለት ጣዖት አምላኪ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም" (ኤፌ 5፥5) ለሚለው ቃል ዐይናቸውን ያሳውራሉ።

**1፥24 እግዚአብሔር … አሳልፎ ሰጣቸው፤** እግዚአብሔር አንድን ማኅበረሰብም ሆነ ሰዎችን የተወ መሆኑን ከሚረጋገጥባቸው ምልክቶች ዋነኛው ከሥነ ምግባርና ከተፈጥሮ ባሕርይ ውጭ በሆነ የወሲብ ግንኙነት መጠመዳቸው ነው። (1) "እግዚአብሔር … አሳልፎ ሰጣቸው "ማለትም ልቅ ለሆነ ፍትወት ተዋቸው ማለት ነው። "በኃጢአት በተሞላው የልባቸው ምኞት" (በግሪኩ ኤፒቱሚያ) የሚለው ቃል ላልተፈቀደ የወሲብ ግንኙነት ኀይለኛ መሻት መኖሩን ያመለክታል (ከ2ቆሮ 12፥21፤ ከገላ 5፥19፤ ከኤፌ 5፥3 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ወደ ርኩሰት አልፈው የሚሰጡባቸው ሦስቱ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) አካልን በኀጢአት ለሚያስነውረው ልቅ ወሲባዊ ግንኙነት እግዚአብሔር አሳልፎ መስጠቱ (ቍ 24)፤ (ለ) ለአስነዋሪ ግብረ ሰዶማዊ ወይም ግብረ ሰዶማዊት ምኞት እግዚአብሔር አሳልፎ መስጠቱ (ቍ 26-27)፤ (ሐ) ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም አእምሮአቸው ርኩስ ሥራቸውን በመቀበል በክፉና በልቅ ወሲባዊ ግንኙነት ደስ በመሰኘት ቀጠሉ ማለት ነው (ቍ 28)። እነዚህ ሦስት ደረጃዎችም የእግዚአብሔርን እውነተኛ መገለጥ በማይቀበሉና በርኩሰት ውስጥ ደስታን በሚሹ ሁሉ ላይ ይደርሳሉ (ቍ 18፤ ቍ27 እና ማብ ይመ)።

(3) እግዚአብሔር ዐመፀኛውን ለኀጢአት አሳልፎ የሚሰጥበት ሁለት ምክንያቶች አሉት፤ (ሀ) የፍርዱ አንዱ ክፍል በመሆኑ ኀጢአትና መዘዙ እየጨመረ እንዲሄድ ለማድረግ (2፥2)፣ (ለ) ድነትን ማግኘት እንደሚያስፈልጋቸው ለማስገንዘብ (2፥4)።

**1፥25 በሐሰት፤** "ሐሰት"፣ የሐሰት ሁሉ አባት የሆነው የሰይጣን ቃል ነው (ዮሐ 8፥44)፤ ይህም "እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ" (ዘፍ 3፥5) እንዳለው ዐይነት ነው፤ (1) የሰይጣንን ሐሰት ማመን፤ "የእግዚአብሔርን እውነት" መቃወም ሲሆን፣ በጣዖት አምልኮም መካፈል ነው (ዘፍ 3፥5፤ ቈላ 3፥5፤ 2ተሰ 2፥11 እና ማብ

ፈጣሪም ለዘላለም የተመሰገነ ነው፤ አሜን።
[26]በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አሳፋሪ
ለሆነ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም
እንኳ ለባሕርያቸው የሚገባውን ግንኙነት
ባሕርያቸው ላልሆነው ግንኙነት ለወጡ።
[27]እንዲሁም ወንዶች ለባሕርያቸው
የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው
እርስ በርሳቸው በፍትወት ተቃጠሉ፤
ወንዶች ከወንዶች ጋር ነውር ፈጸሙ፤ ለክፉ
አድራጎታቸውም የሚገባቸውን ቅጣት በገዛ
ራሳቸው ላይ አመጡ።
[28]ከዚህም በላይ በሐሳባቸው እግዚአብሔርን
ማወቅ አይጠቅምም በማለታቸው፣
መደረግ የማይገባውን እንዲያደርጉ
እግዚአብሔር ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ
ሰጣቸው። [29]በሁሉም ዐይነት ዐመፃ፣
ክፋት፣ ስግብግብነትና ምግባረ
ብልሹነት ተሞልተዋል፤ ቅናትን፣ ነፍስ
ገዳይነትን፣ ጥልን፣ አታላይነትንና ተን
ኰልን የተሞሉ ናቸው፤ ሐሜተኞች፣
[30]ስም አጥፊዎች፣ እግዚአብሔርን የሚጠሉ፣
ተሳዳቢዎች፣ ትዕቢተኞችና ትምክሕተኞች
ናቸው፤ ክፋትን የሚሠሩበትን
መንገድ ያውጠነጥናሉ፤ ለወላጆቻቸው
አይታዘዙም። [31]የማያስተውሉ፣ ውል
የሚያፈርሱ፣ ርኅራኄ የሌላቸውና
ጨካኞች ናቸው። [32]ይህን የሚያደርጉ
ሁሉ ሞት ይገባቸዋል የሚለውን ትክክለኛ
የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ ቢያውቁም፣
እነዚህን ነገሮች ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣
እንዲህ የሚያደርጉትንም ያበረታታሉ።

1፥26 ቍ 24፥28፤ ዘሌ 18፥22፥23፤ ኤፌ 4፥19፤ 1ተሰ 4፥5
1፥27 ዘሌ 18፥22፤ 20፥13፤ 1ቆሮ 6፥18
1፥28 ቍ 24፥26
1፥29 2ቆሮ 12፥20፤ 1ጢሞ 5፥13፤ ያዕ 3፥2፤ 3 ዮሐ 10
1፥30 2ጢሞ 3፥2
1፥31 2ጢሞ 3፥3
1፥32 መዝ 50፥18፤ ሉቃ 11፥48፤ ሐሥ 8፥1፤ 22፥20፤ ሮሜ 6፥23
2፥1 2ሳሙ 12፥5-7፤ ማቴ 7፥1፡2፤ ሮሜ 1፥20
2፥4 ዘፀ 34፥6፤ ሮሜ 9፥22፤ 9፥23፤ 11፥22፤ 11፥33፤ ኤፌ 1፥7፥18፤ 2፥7፤ 3፥8፥16፤ ቈላ 2፥2፤ 3፥25፤ 1ጢሞ 1፥16፤ 1ጴጥ 3፥20፤ 2ጴጥ 3፥9፤ 2ጴጥ 3፥15
2፥5 መዝ 110፥5፤ ይሁዳ 1፥6፤

## የእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ

2 ስለዚህ አንተ በሌላው ላይ የምትፈርድ፣
የምታመካኝበት የለህም፤ በሌላው
ላይ በምትፈርድበት ነገር ሁሉ፣ ራስህን
ትኰንናለህ፤ ፈራጅ የሆንኸው አንተ ያንኑ
ታደርጋለህና። [2]እንደዚህ በሚያደርጉትም
ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛ መሆኑን
እናውቃለን። [3]እንግዲህ አንተ ሰው በሌሎች
ላይ እየፈረድህ፣ ያንኑ የምታደርግ
ከሆነ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ
ይመስልሃል? [4]ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት
ወደ ንስሓ የሚመራህ መሆኑን ሳትገነዘብ፣
የቸርነቱን፣ የቻይነቱን የትዕግሥቱን ባለ
ጠግነት ትንቃለህ?
[5]ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ
ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ
በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ ቍጣን
ታከማቻለህ። [6]እግዚአብሔር "ለእያንዳንዱ
እንደ ሥራው ይሰጠዋል"፤ [7]በጎ የሆነውን

2፥5 ራእ 6፥17 2፥6 መዝ 62፥12፤ ማቴ 16፥27፤ ምሳ 24፥12
2፥7 ቍ 10፤ ማቴ 25፥46፤ 1ቆሮ 15፥53፥54፤ 2ጢሞ 1፥10

ይመ)። (2) ሐሰትን የማመንና ራስን የማምለክ የሰው ዝንባሌ የትዕቢት ውጤት በመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ አበክሮ ያስጠነቅቃል። «ልብህ በትዕቢት ተወጥሮ እኔ አምላክ ነኝ ... ብለሃል» (ሕዝ 28፥2 ይመ፤ ከምሳ 6፥17፤ 8፥13፤ 16፥18፤ ከ1ጢሞ 3፥6፤ ከያዕ 4፥6፤ ከ1ዮሐ 2፥16 ጋር ያነጻጽሩ)።

**1፥27 ወንዶች ከወንዶች ጋር፤** ሐዋርያው ጳውሎስ የግብረ ሰዶማዊነት ወይም የግብረ ሰዶማዊትነት ርኩሰት ከምግባረ ብልሹነትና በእግዚአብሔር ከመተው የተነሣ ለመጣው ለሰው ልጅ የባሕርይ ዝቅጠት ማስረጃ እንደሆነ ይናገራል (ዘፍ 19፥4-5፤ ዘሌ 18፥22 ይመ)። ግብረ ሰዶማዊነትን ወይም ግብረ ሰዶማዊትነትን እንደ ትክክለኛ የሕይወት ዘይቤ የሚቀበል ማንኛውም መንግሥት በምግባረ ብልሹነት የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው (ቍ 24 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ አስነዋሪ ድርጊት መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስፍራ ይናገራል፤ ለምሳሌ ዘፍ 19፥4-9፤ ዘሌ 20፥13፤ ዘዳ 23፥17፤ 1ነገ 14፥24፤ 15፥12፤ 22፥46፤ ኢሳ 3፥9፤ 1ቆሮ 6፥9-10፤ 1ጢሞ 1፥10፤ 2ጴጥ 2፥6፤ ይሁ 7 ይመልከቱ።

**1፥32 እንዲህ የሚያደርጉትንም ያበረታታሉ፤** ከሰው ኀጢአተኝነት አንጻር ጳውሎስ የተናገረው የመጨረሻ ቃል በአድራጊዎች ላይ ከሚሆነው ፍርድ ይልቅ በርኩሰት ደስ እየተሰኙ ክፉን በሚደግፉና በሚያደፋፍሩ ሰዎች ላይ የሚሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ የባሰ እንደ ሆነ ነው። ይህ ባሕርይ የምግባር ብልሹነት የመጨረሻ ደረጃ ነው፤ ይኸውም በሌሎች የርኩሰት ተግባር ደስ መሰኘት ነው። እንግዲህ ኀጢአት መዝናኛ ሆነ ማለት ነው፤ (1) «ያበረታታሉ» (በግሪክ ሱኑዶኬኦ) የሚለው ቃል «ይስማማሉ»፣ «ይደግፋሉ» ወይም «ይረካሉ» ማለት ሲሆን፤ በኅብረተሰቡ ዘንድ በስፋት በተገለጠ ኀጢአት እንዲሁ ደስ መሰኘታቸውን ይገልጻል።

(2) አዝናኝ በሆኑ የመገናኛ ብዙኀን ላይ ብዙውን ጊዜ እየተሰራጨ ያለው ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነው ነገር ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነው፤ ያም ሆኖ ግን ብዙ ሰዎች ድርጊቱን ሲያበረታቱትና ደስ ሲሰኙበት ይታያል። በቀጥታ ተሳታፊ ባይሆንም እንኳ ሰዎች ኀጢአትና ርኩስ የሆነውን ነገር ሲያደርጉ እየተመለከቱ መደሰትና መዝናናት እንደ ክፉ አድራጊዎቹ የእግዚአብሔርን ፍርድ በራስ ላይ መጋበዝ ነው። በየትኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የሌሎች ተቃውሞ ካልገጠመው በቀር ኀጢአት እየጨመረ ይሄዳል።

(3) በሌሎች ኀጢአትና ርኩሰት የሚዝናኑና ደስ የሚሰኙ ሰዎች፣ በተለይ ደግሞ ክርስቲያኖች ከብዙኀኑ ጋር ክፋትን ለማስፋፋት እገዛ እያደረጉ ሲሆን ኍልቍ መሳፍርት የሌላቸው ሰዎችንም ለጥፋትና ለዘላለም ኵነኔ ይዳርጋሉ። ይህ ኀጢአት ሞትን የሚያስከትል ሲሆን፣ በመጨረሻው የፍርድ ቀንም ግሃድ ወጥቶ ይፈረድበታል (2ተሰ 2፥12)።

**2፥1 ያንኑ ታደርጋለህና፤** በምዕራፍ 1 ላይ ጳውሎስ አሕዛብ ባለማመናቸው ምክንያት ለኀጢአት አልፈው እንደተሰጡ ይናገራል። አሁን ደግሞ በምዕራፍ 2 ላይ አይሁድ ተመሳሳይ ድርጊት እየፈጸሙ መሆናቸውን በመግለጽ በክርስቶስ ድነት እንደሚያስፈልጋቸው ይናገራል።

**2፥3 ያንኑ የምታደርግ ከሆነ፤** ማንም ሰው የራሱን ክፉ ባሕርይ ሳያስተካክል ሌሎች ትክክለኛውን ነገር እንዲያደርጉ ለማምራት መሞከር የለበትም። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በመካከላቸው ላለው ዓለማዊነትና ርኩሰት ታውረው የማያምነውን ኅብረተሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ ደንብ ለመምራት ይሞክራሉ (ከሉቃ 6፥42 ጋር ያነጻጽሩ)። ዓለም ወደ ተሻለ የኑሮ አካሄድ እንድትገባ ቤተ ክርስቲያን ጥረት ከማድረጓ በፊት በሰማያዊው ብርሃን ራሷን ተመልክታ መቀደስ ይጠበቅባታል።

**2፥7 ክብርን፣ ሞገስንና ዘላለማዊነትን፤** ጳውሎስ ስለድነት በሚናገረው መልእክቱ መጀመሪያ

ጽንቶ በማድረግ ክብርን፣ ሞገስንና
ዘላለማዊነ ን ለሚሹ የዘላለም ሕይወት
ይሰጣቸዋል። [8]ነገር ግን በራስ ወዳዶች፣
እውነትን ትተው ክፋትን በሚከተሉ
ፍርድና ቍጣ ይደርስባቸ ዋል። [9]ክፉ
በሚያደርግ በማንኛውም ሰው፣ አስቀድሞ
በአይሁድ ከዚያም በአሕዛብ ላይ መከራና
ጭንቀት ይሆናል፤ [10]ነገር ግን በጎ ለሚሠራ
ለማንኛውም፣ አስቀድሞ ለአይሁድ ከዚያም
ለአሕዛብ ክብር፣ ሞገስና ሰላም ይሆን
ለታል፤ [11]እግዚአብሔር ለማንም አያደላምና።
[12]ሕግ ሳይኖራቸው ኀጢአት የሠሩ
ሁሉ ያለ ሕግ ይጠፋሉ፤ ሕግ እያላቸው
ኀጢአት የሠሩ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤
[13]ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን
የሚባሉት ለሕጉ የሚታዘዙ እንጂ፣ ሕጉን
የሚሰሙ አይደሉም። [14]ሕግ የሌላቸው
አሕዛብ ሕግ የሚያዝዘውን ነገር በተፈጥሮ
ሲያደርጉ፣ ሕግ ባይኖራቸውም እነርሱ
ለራሳቸው ሕግ ናቸው። [15]ኅሊናቸው
ስለሚመሰክር፣ ሐሳባቸው ስለሚከሳቸው፣
ደግሞም ስለሚከላከልላቸው የሕግ ትእዛዝ
በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያሉ። [16]ይህም
በወ ንጌል እንደማስተምረው እግዚአብሔር
በሰው ልብ የተሰወረውን በክርስቶስ በኩል
በሚፈርድበት ዕለት ግልጽ ይሆናል።

## ሕግና አይሁድ

[17]አንተ ይሁዲ ነኝ ካልህ፣ በሕግ
የምትተማመንና ከእግዚአብሔር ጋር
ባለህ ግንኙነት የምትኰራ፣ [18]በሕግ
በመመራትህም ፈቃዱን ዐውቀህ ፍጹም
የሆነውን ለይተህ ከያዝህ፣ [19]ለዕውሮች
መሪ፣ በጨለማ ላሉትም ብርሃን መሆንህን
ርግጠኛ ከሆንህ፣ [20]በሕጉም ካገኘኸው
ዕውቀትና እውነት የተነሣ አላዋቂ ለሆኑት
መካሪ፣ ለሕፃናት አስተማሪ ከሆንህ፣
[21]እንግዲህ አንተ ሌሎችን የምታስተምር፣
ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ
የምትሰብክ፣ ትሰርቃለህን? [22]አንተ
ሰዎች ማመንዘር የለባቸውም የምትል፣
ታመነዝራለህን? አንተ ጣዖትን የምትጸየፍ፣
቎ተ መቅደስን ትመዘብራለህን? [23]አንተ
በሕግ የምትመካ፣ ሕግን በመተላለፍ
እግዚአብሔርን ታዋርዳለህን? [24]ይህም
"በእናንተ ምክንያት የእግዚአብሔር ስም
በአሕዛብ ዘንድ ይሰደባል" ተብሎ እንደ
ተጻፈው መሆኑ ነው።
[25]ሕግን የምትፈጽም ከሆነ ግዝረት ዋጋ
አለው፤ ሕግን የምትተላለፍ ከሆነ ግን
እንዳልተገረዝህ ትሆናለህ። [26]ያልተገረዙት
ሕጉ የሚያዝዘውን የሚፈጽሙ ከሆነ፣ እንደ
ተገረዙ አይቈጠሩምን? [27]አንተ የተጻፈ
ሕግ፣ ግዝረትም ቢኖርህ፣ ሕግ ተላላፊ
በመሆንህ፣ በሥጋ ያል ተገረዘው ለሕግ
በመታዘዙ ይፈርድብሃል።
[28]አንድ ሰው ለይምሰል በውጫዊው ብቻ
ይሁዲ ልሁን ቢል ይሁዳ አይሆንም፤ እውነ
ትኛ ግዝረትም ውጫዊና ሥጋዊ ሥርዐት አይ
ደለም። [29]ዳሩ ግን አንድ ሰው ይሁዲ የሚሆ

2፥8 ሕዝ22፥31፤
2ተሰ2፥12
2፥9 ቆላ10፥
መዝ32፥10፤
ሮሜ1፥16
2፥10 ቆላ9፥
ሮሜ1፥16
2፥11 ሐሥ10፥34
2፥12 ሮሜ3፥19፤
6፥14፤ 7፥4፤
1ቆሮ9፥20፡21፤
ገላ4፥21፤ 5፥18
2፥13
ያዕ1፥22፡23፡25
2፥14 ሐሥ10፥35
2፥16 መክ12፥14፤
ሐሥ10፥42፤
ሮሜ16፥25፤
1ቆሮ4፥5፤
2ጢሞ2፥8
2፥17 ቍ23፤
ኤር8፥8፤
ሚክ3፥11፤
ዮሐ5፥45፤
ሮሜ9፥4
2፥21 ማቴ23፥3፡4
2፥22 ሐሥ19፥37
2፥23 ቍ17
2፥24 ኢሳ52፥5፤
ሕዝ36፥22፤
2ጴጥ2፥2
2፥25 ቍ13፥27፤
ኤር4፥4፤
9፥25፡26፤ ገላ5፥3
2፥26 ሮሜ8፥4፤
1ቆሮ7፥19
2፥27
ማቴ12፥41፡42
2፥28 ማቴ3፥9፤
2፥28 ዮሐ8፥39፤ ሮሜ9፥6፡7፤ ገላ6፥15 2፥29 ዘዳ30፥6፤
ዮሐ5፥44፤ 12፥43፤ ሮሜ7፥6፤ 1ቆሮ4፥5፤ 2ቆሮ3፥6፤
10፥18፤ ገላ1፥10፤ ፊል3፥3፤ ቈላ2፥11፤ 1ተሰ2፥4፤
1ጴጥ3፥4

ላይ እግዚአብሔር ከመላው የሰው ዘር ጋር ባለው ግንኙነት የሚያደርገውን መሠረታዊ እውነት ይገልጣል፤ እግዚአብሔር ክፉ አድራጊዎችን ይቀጣል፣ ለጻድቃንም ዋጋ ይሰጣል (ገላ 6፥7-8፡ ዮሐ 5፥29 እና ማብ ይመ)። (1) ቅዱሳን በእምነት የጸደቁ (1፥16-17፤ 3፥24) እንዲሁም በእግዚአብሔር መለኪያ ትክክለኛ የሆነውን በማድረግ የሚተጉ ናቸው (ቆላ 7:10 ይመ፤ ከማቴ 24፥13፡ ከቈላ 1፥23፤ ከዕብ 3፥14፤ ከራእ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። ከእግዚአብሔር ለሚገኝ ክብር ትልቅ ግምት የሚሰጡ ሲሆን (1፥23፡ 2፥7፡ 5፥2፤ 8፥18) የዘላለምን ሕይወት ይሻሉ (8፥23፤ 1ቆሮ 15፥51-57፤ 1ጴጥ 1፥4፤ ራእ 21፥1—22፥5)። (2) የዘላለምን ሕይወት የሚፈልጉ በእምነት በጸጋው ያገኙታል (3፥24-25፤ ኤፌ 1፥4-7፡ 2፥8-10፤ 2ጢሞ 2፥1፡ ፊል 2፥12-13 እና ማብ ይመ)። ታማኝ የሆነው ሰው፣ "በጎ የሆነውን ጽንቶ በማድረግ ክብርን፣ ሞገስንና ዘላለማዊነትን" የሚሻ ሲሆን (ከማቴ 24፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ይህም እውን የሚሆንለት በክርስቶስ ከተሰጠው ከሚያስችለው ጸጋ የተነሣ ነው (ማቴ 7፥21 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። (3) ክፉን በሚያደርጉ ሰዎች ራስ ወዳዶች፣ ለእውነት የማይታዘዙና በዐመፃ ደስ የሚሰኙ ናቸው፤ ቍጣና ቅጣትም ይደርስባቸዋል (1፥28-32፡ 2፥8-9)።

**2፥12 ይጠፋሉ፤** ኀጢአትን የሚሠሩ ሁሉ፣ ስለ እግዚአብሔር ሕግ ምንም እውቀት ባይኖራቸውም እንኳ፣ እውነትንና ሐሰትን የሚለዩበት እውቀት ስላላቸው ይጠፋሉ (ቆላ 14፥15)። እግዚአብሔር ወንጌልን ያልሰሙትን እንዲሁ አያድናቸውም፤ ከሞቱም በኋላ ሌላ ዕድል አይሰጣቸውም። ወንጌልን መስማት ያልቻሉት የሚገጥማቸው ዘላለማዊ ጥፋት ለሰዎች ሁሉ ወንጌልን ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት እንድናደርግ ሊያነሣሣን ይገባል (ማቴ 4፥19 እና ማብ፡ 9፥37 እና ማብ ይመ)።

**2፥13 ጻድቃን የሚባሉት ለሕጉ የሚታዘዙ፤** "ሕግ" የሚለውን ቃል ጳውሎስ የተጠቀመበት መንገድ በድንጋጌ መልክ መጥቶ እንዲሁ ያለጸጋ ቢታዘዙት ድነት ያስገኛል በሚል መንፈስ አይደለም። "ሕግ" የሚለው ቃል እዚህ ላይ የሚያመለክተው ለሰው ዘር የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ነው። በእምነት፣ በመገዛትና በመታዘዝ ካልሆነ በቀር እንዲሁ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ጥቅም የለውም። ራሱን በፍቅር በሚገልጽ (ገላ 5፥6)፣ "እምነት አማካይነት ወደሚገኘው መታዘዝ" (1፥5፤ ከ16፥26 ጋር ያነጻጽሩ) መምጣት ይኖርብናል።

**2፥16 እግዚአብሔር በሰው ልብ የተሰወረውን … በሚፈርድበት፤** በገጽ 1822 ላይ፣ "*በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥24 የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ ዘንድ ይሰደባል፤** የአይሁድ ኀጢአት አሕዛብ የእግዚአብሔርን ስም እንዲሰድቡ ምክንያት ሆኗል። ዛሬም ቢሆን፣ ሌብ ያሉ አብዮተ ክርስቲያናትና የስም ክርስቲያኖች የሚያደርጉት ኀጢአት በመፀኞች የክርስቶስን ስም እንዲሰድቡ ምክንያት ይሆናል።

ነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ
ነው። ግዝረትም ግዝረት የሚሆነው በተጻፈው
ሕግ ሳይሆን፣ በመንፈስ የልብ ግዝረት
ሲኖር ነው። እንዲህ ያለው ሰው ምስጋናው
ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

## የእግዚአብሔር ታማኝነት

3 ታዲያ አይሁዳዊ መሆን ጥቅሙ ምንድን
ነው? መገረዝስ ምን ፋይዳ አለው?
2በየትኛውም መንገድ ጥቅሙ ብዙ ነው፤
ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል በአደራ
የተሰጠው ለእነርሱ ነው።
3አንዳንዶች እምነት ባይኖራቸውስ?
የእነርሱ አለማመን የእግዚአብሔርን ታማኝነት
ዋጋ ያሳጣዋልን? 4ፈጽሞ አይሆንም! ሰው
ሁሉ ሐሰተኛ፣ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ
ይሁን፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

"በቃልህ የተነገ እውነተኛ፣
በፍርድም ፊት ረቺ ትሆናለህ።"

5የእኛ ዐመፃ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አጕልቶ
የሚያሳይ ከሆነ፣ ምን ማለት እንችላለን?
እንደ ሰው ለመከራከር ያህል እግዚአብሔር በእኛ
ላይ ቍጣውን ማምጣቱ ትክክል አይደለም
ሊባል ነውን? እንደ ሰው ሲታሰብ ማለቴ
ነው። 6በርግጥ እንዲህ ሊሆን አይችልም፤
እንዲህ ቢሆንማ ኖሮ እግዚአብሔር በዓለም
ላይ እንዴት ሊፈርድ ይችላል? 7"የእኔ
ውሸተኛ መሆን የእግዚአብሔርን እውነተኛነት
የሚያጐላ፣ ክብሩንም የሚጨምርለት ከሆነ፣
ኀጢአተኛ ተብዬ እስካሁን እንዴት ይፈር
ድብኛል?" በማለት ሊከራከር የሚችል ሰው
ይኖር ይሆናል። 8ይህማ "በጎ እንዲመጣ
ክፉ እንሥራ" ይላሉ በማለት አንዳንዶች
እንደሚያስወሩብን ነው፤ በእነዚህ ሰዎች
ላይ የሚደርሰው ፍርድ ትክክለኛ ነው።

3፥2 ዘዳ4፥8፤ መዝ147፥19፤ ሐሥ7፥38፤ ሮሜ9፥4፡5
3፥3 ሮሜ10፥16፤ 2ጢሞ2፥13፤ ዕብ4፥2
3፥4 መዝ116፥11፤ 51፥4፤ ዮሐ3፥33
3፥5 ሮሜ5፥8፤ 6፥19፤ ገላ3፥15
3፥6 ዘፍ18፥25፤ ሮሜ2፥16
3፥7 ቍ4፤ ሮሜ9፥19
3፥8 ሮሜ6፥1
3፥9 ቍ1፡19፡23፤ 1ነገ8፥46፤ 2ዜና6፥36፤ መዝ106፥6፤ መክ7፥20፤ ሮሜ5፥12፤ 11፥32፤ ገላ3፥22
3፥12 መዝ14፥1-3፤ 53፥1-3
3፥13 መዝ5፥9፤ 140፥3
3፥14 መዝ10፥7
3፥17 ኢሳ59፥7፡8
3፥18 መዝ36፥1
3፥19 ቍ9፤ መዝ63፥11፤ 107፥42፤ ሕዝ16፥63፤ ዮሐ10፥34፤ ሮሜ2፥12
3፥20 ሐሥ13፥39፤ ሮሜ4፥15፤ ገላ2፥16
3፥21 ኢሳ46፥13፤ ኤር23፥6፤ ሐሥ10፥43፤ ሮሜ1፥2፡17፤ 9፥30

## ማንም ጻድቅ አይደለም

9እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ ከእነርሱ
እንበልጣለንን?* ከቶ አይደለም፤ አይሁድም
ሆኑ አሕዛብ፣ ሁሉም ከኀጢአት በታች
እንደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፤
10እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
"ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤
11አስተዋይ የለም፤
እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም
የለም።
12ሁሉም ተሳስተዋል፤
በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤
በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤
አንድም እንኳ።"
13"ጕሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤
አንደበታቸው ሽንገላን
ያዘወትራል።"
"በከንፈሮቻቸው የእባብ መርዝ
አለ።"
14"አፋቸው ርግማንና ምሬት
ሞልቶበታል።"
15"እግራቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣን ነው፤
16በመንገዳቸው ጥፋትና ጕስቍልና
ይገኛል፤
17የሰላምንም መንገድ አያውቁም።"
18"በዐይናቸው ፊት የእግዚአብሔር
ፍርሀት የለም።"
19እንግዲህ አፍ ሁሉ እንዲዘጋና ዓለም
በሙሉ በእግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥ ሕግ
የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንደ
ሆነ፣ እናውቃለን፤ 20ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ
ማንም በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው ሊባል
አይችልም፤ ይልቁንም በሕግ አማካይነት
ኀጢአትን እንገነዘባለን።

## በእምነት የሚገኝ ጽድቅ

21አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣
ከሕግ ውጪ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ

*3፥9 ወይም እንብሳለንን

**2፥29 በመንፈስ የልብ ግዝረት፤** ይህ አማኞች ከመለኮታዊው ባሕርይ እንዲካፈሉና የእግዚአብሔርን ክብር ከሚያጐድፉ ኀጢአት ተለይተው ንጹህ የሆነ ሕይወት እንዲመሩ የሚያደርግ በአማኞች ልብ ውስጥ የሚከናወን የእግዚአብሔር የጸጋ ሥራ ነው (ከዘዳ 10፥16፤ ከኤር 4፥4፤ ከ2ጴጥ 1፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ቅዱስ የሆነ አኗኗር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለመሆናችን ምስክር ነው።

**3፥9 ሁሉም ከኀጢአት በታች፤** ከምዕራፍ 1—2 ጳውሎስ ሰው ሁሉ ማለትም አሕዛብና አይሁድ የኀጢአት ባሪያዎች እንደሆኑ ገልጿአል። በ3፥9-18 ሰዎች ሁሉ ወደ ኀጢአትና ወደ ክፋት የሚመሩ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ለምን እንዳላቸው ይገልጻል፤ ያስተምራልም (የሚከተለውን ማብ ይመ)። ይኸውም ሁሉም በደለኛና ከእግዚአብሔር ቍጣ በታች በመሆናቸው ነው (ቍ 23)። ለዚህ አሳዛኝ ሁኔታ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ የሰጠው ስጦታ ይቅርታን፤ እገዛን፤ ጸጋን፣ ጽድቅንና ድነትን ነው (ቍ 21-26)።

**3፥10 ጻድቅ ማንም የለም፤** እነዚህ ጥቅሶች የሰውን ትክክለኛ ማንነት ያሳያሉ። ሰው ሁሉ በተፈጥሮው ኀጢአተኛ ነው። ሁለንተናው በኀጢአት ክፉኛ የተበከለ ሲሆን ዓለምን ወደ መምሰል (በገጽ 2022 ላይ፡ *«ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፣ ወደ ዲያቢሎስ (ማቴ 4፥10 እና ማብ ይመ) እና ወደ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ (በገጽ 1853 ላይ፣ *«የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ያደላ ነው። ሁሉ ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ ወደ ራስ ወዳድነት ዘወር ስላለ በደለኛ ነው።

**3፥18 የእግዚአብሔር ፍርሃት የለም፤** የሰዎች አስከፊ የሕይወት ገጽታ እየቀጠለ የሚሄደው ለምንድነው? በዐይናቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት ስለሌለ አይደለምን? እግዚአብሔርን ቢፈሩማ ኖሮ ዕርቅና ሰላም ይፈልጉ ነበር። ሰው እግዚአብሔርን ሲፈራ ክፋውን ያስወግዳል (ምሳ 16፥6 ይመ፤ ከምሳ 3፥7፤ 8፥13፤ 9፥10 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሐሥ 5፥11 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 291 ላይ፣ *«እግዚአብሔርን መፍራት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

ተገልጦአል። 22ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ
ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ
ነው። ልዩነት የለም፤ 23ምክንያቱም ሁሉም
ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር
ጕድሎአቸዋል፤ 24በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው
ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤
25በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማ
ስተስረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ⁿ
ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን
ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፉ
ጽድቁን ለማሳየት ነው፤ 26በአሁኑ ዘመን
ይህን ያደረገው፣ ጽድቁን ይኸውም እርሱ
ሮሜ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፤ በኢየሱስ የሚያምነውን
10፥4-13 የሚያጸድቅ መሆኑን፣ ለማሳየት ነው።
27ታዲያ ትምክሕት ወዴት ነው? እርሱማ
ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ? በሥራ ሕግ
ነውን? አይደለም፤ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።
28ማንም ሰው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን፤
በእምነት እንደሚጸድቅ እናረጋግጣለን።
29እግዚአብሔር የአይሁድ አምላክ ብቻ ነውን?
የአሕዛብስ አምላክ አይደለምን? አዎን፤
የአሕዛብም አምላክ ነው፤ 30የተገረዘውን
በእምነት፣ ያልተገረዘውንም በዚያው እምነት
የሚያጸድቅ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነውና።
31ታዲያ እንዲህ ከሆነ ከእምነት የተነሣ
ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ ይሆን? ፈጽሞ
አይደረግም፤ ሕጉን እናጸናለን እንጂ።

3፥22 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ1፥17፤ 4፥11፤ 9፥30፤ 10፥4፡12፤ ገላ2፥16፤ 3፥22፡28፤ ቆላ3፥11 3፥23 ቍ 9 3፥24 መዝ130፥7፤ ዮሐ1፥14፡16፡17፤ ሮሜ4፥16፤ 5፥21፤ 4፥25፤ 6፥14፤ 11፥5፤ 2ቆሮ12፥9፤ ኤፌ1፥7፡14፤ 2፥8፤ 4፥7፤ 1ቆሮ1፥30፤ ገላ4፥5፤ ቆላ1፥14፤ ቲቶ2፥11፤ ዕብ4፥16፤ ዕብ9፥12 3፥25 ዘፀ25፥17፤ ዘሌ16፥10፤ መዝ65፥3፤

3፥25 ሐዋ14፥16፤ 17፥30፤ 20፥28፤ ሮሜ5፥9፤ ኤፌ1፥7፤ ዕብ2፥17፤ 9፥28፤ 13፥12፤ 9፥12፡14፤ 1ጴጥ1፥19፤ 1ዮሐ4፥10፤ ራእ1፥5 3፥27 ሮሜ2፥17፡23፤ 4፥2፤ 1ቆሮ1፥29-31፤ ኤፌ2፥9 3፥28 ሐዋ13፥39፤ ሮሜ3፥20፡21፤ ኤፌ2፥9፤ ገላ2፥16፤ 3፥11፤ ያዕ2፥20፡24፡26 3፥29 ሐዋ10፥34፡35፤ ሮሜ9፥24፤ 10፥12፤ 15፥9፤ ገላ3፥28 3፥30 ሮሜ4፥11፡12፤ ገላ3፥8

*ⁿ3፥25 ወይም እግዚአብሔር ቍጣውን በመተው ኀጢአትን ለማስወገድ*

3፥21 **የእግዚአብሔር ጽድቅ፤** ይህ ሐረግ እግዚአብሔር በኀጢአት ከነበረንበት ሁኔታ አውጥቶ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ (ቍ 26) ከራሱ ጋር ትክክለኛ በሆነ ግንኙነት ያስቀመጠንና ከክፉው ኀይል ነጻ ያወጣንን የማዳኑን ሥራ ያሳያል (የድነት ሥራና የጽድቅ መገለጥ በመሠረቱ ከዚህ ጋር አንድ እንደሆኑ የሚያሳየውን የብሉይ ኪዳንን ክፍል ልብ ይበሉ፤ መዝ 98፥1-2፤ ኢሳ 46፥13፤ 51፥5-8፤ 56፥1፤ 62፥1 እንዲሁም መዝ 32፥2 እና ማብ፤ ኢሳ 56፥1-2 እና ማብ ይመ)። (1) ይህ በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለቀ ነገር አይደለም፤ ከእምነት ጋር አብሮ የሚጓዝ ለድነት የሚያበቃ የእግዚአብሔር ኀይል እንደመሆኑ መጠን፣ ዘወትር አዲስ በእጅጉም አስፈላጊ ነው (በገጽ 1735 ላይ፣ *«ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። (2) ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ወደ እኛ የሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው (ቍ 22)።

3፥22 **በማመን፤** እግዚአብሔር ለድነት የሚፈልግብን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ እንድናምን ብቻ ነው። የሚያድነውን እምነት በተመለከተ ለቀረበው አስተያየት በገጽ 1746 ላይ፤ *«እምነትና ጸጋ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

3፥24 **በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤** ይህ ጥቅስ ጳውሎስ ድነትን ለመግለጽ የሚጠቀምባቸው ሁለት የተለመዱ ቃላት ይዟል፤ እነርሱም፣ «ጸድቀዋል» እና «ቤዛነት» ሲሆኑ፣ በነዚህ ሁለት አሳቦች ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ለማግኘት በገጽ 1735 ላይ፣ *«ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

3፥25 **በደሙም፤** አዲስ ኪዳን የክርስቶስን ሞት በተመለከተ በርካታ እውነቶችን በአጽንዖት ያመለክታል።

(1) *መሥዋዕት* ነበር፤ የደሙ ማለትም የሕይወቱ ስጦታ ነው (ከ1ቆሮ 5፥7፤ ከኤፌ 5፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) በምትክነት *መሞት* ነበር፤ ይህም የሞተው ለራሱ ሳይሆን ስለሌሎች ነው (5፥8፤ 8፥32፤ ማር 10፥45፤ ኤፌ 5፥2)።

(3) በሰዎች *ፈንታ መሞት* ነበር፤ ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ይቀጣ ዘንድ በፈንታችን ሆኖ የሞት መከራን ተቀበለ (6፥23፤ በገጽ 202 ላይ፤ *«የስርየት ቀን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) *ቍጣን የሚያበርድ* ሞት ነበር፤ የክርስቶስ ለኀጢአተኞች *መሞት* የእግዚአብሔርን ጻድቅ ባሕርይና ሥርዐት ደንብ ያረካ ሲሆን፣ ከዚህም የተነሣ ንስሓ ከገባው ኀጢአተኛ ላይ ቍጣውን ሊያነሣ ቻለ። የእግዚአብሔር ማንነት የኀጢአትን ቅጣትና በእኛ ፋንታ የሚከፈልን ተገቢ ዋጋ የሚጠይቅ ነው። በክርስቶስ ደም በተገኘው ዕርቅ ምክንያት የእግዚአብሔር ቅድስና የተጠበቀ ሲሆን፣ ጸጋውንና ፍቅሩንም በድነት ውስጥ በአግባቡ ሊገልጥ ችሏል። ክርስቶስ ዋጋ ይከፍል ዘንድ የፈቀደው እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ «ዓለሙን ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር» ስለሚል ምሕረትና ፍቅሩን እንዲያሳይ እግዚአብሔር ሰዎች ይገፉት ዘንድ አያስፈልገውም (2ቆሮ 5፥19 ይመ፤ ከዮሐ 3፥16፤ ከሮሜ 5፥8፤ 8፥3፡32፤ ከ1ቆሮ 8፥6፤ ከኤፌ 4፥4-6 ጋር ያነጻጽሩ)።

(5) *የቅጣት* ሞት ነበር፤ ለማስተስረይ ወይም ለኀጢአት ካሳ የሆነ *መሥዋዕት* ነው። በመሆኑም መሥዋዕቱ በቀጥታ ያነጣጠረው ኀጢአትን ማስወገድ ላይ ነው። ከክርስቶስ ሞት የተነሣ እግዚአብሔርንና አማኙን የለየው የኀጢአት ክስና ኀይል ተደምስሷል።

(6) *ውጤት ያለው* ሞት ነበር፤ የስርየት ሞቱ፣ እምነት ከታከለበት የተፈለገውን የመዋጀት ውጤት ሊያመጣ የሚችል ኀይል በውስጡ አለ።

(7) የድል ሞት ነበር፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተዋግቶ፣ በኀጢአት፣ በሰይጣንና ሕዝብን እስረኛ አድርገው በያዙ የአጋንንት ሰራዊቱ ላይ ድልን ተቀዳጅቷል። ሞቱ በእግዚአብሔርና በሰው መንፈሳዊ ጠላቶች ላይ የመጀመሪያን ድል ያስገኘ ነው (8፥3፤ ዮሐ 12፥31-32፤ ቈላ 2፥15)። የክርስቶስ ሞት የቤዛነት ሞት ነው። የገዛ ሕይወቱን ወጆ አድርጎ በመስጠት (1ጴጥ 1፥18-19) የሰውን ዘር በባርነት ከያዙት ጠላቶች ማለትም ከኀጢአት (6፥6)፣ ከሞት (2ጢሞ 1፥10፤ 1ቆሮ 15፥54-57) እና ከሰይጣን (ሐዋ 10፥38) አርነት አውጥቶ እግዚአብሔርን እናገለግል ዘንድ ነጻ አድርጎናል (6፥18፤ በገጽ 1735 ላይ፣ *«ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

ከላይ የተጠቀሱት የክርስቶስ የመሥዋዕት ሞት ውጤቶች ለሁሉ የተደረጉ ቢሆኑም እውን የሚሆኑት ግን ኢየሱስ ክርስቶስንና ለእነርሱ የሞተ መሆኑን በእምነት ለሚቀበሉት ነው።

3፥31 **ሕጉን እናጸናለን፤** በክርስቶስ ድነትን ማግኘት ሕጉ ምንም ዋጋ የለውም ማለት አይደለም።

## አብርሃም በእምነት ጸደቀ

4 እንግዲህ በሥጋ የቀደሞ አባታችን የሆነ
አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ እንላለን?
2አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ፣
የሚመካበት ነበረው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር
ፊት መመካት አይችልም። 3መጽሐፍስ
ምን ይላል? "አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤
ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።"
4አንድ ሰው ሥራ ከሠራ ደመወዙ
እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው
ይቈጠርለታል። 5ነገር ግን ለማይሠራው፣
ኃጥኡን ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር
ለሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ
ይቈጠርለታል። 6ዳዊትም ጽድቅ ያለ
ሥራ ስለሚቈጠርለት ሰው ብፅዕና እንዲህ
ብሎአል፤
7"መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣
ኀጢአታቸው የተሰረየላቸው፣
ብፁዓን ናቸው።
8ኀጢአቱን፣ ጌታ ከቶ የማይቈጥርበት ሰው
ብፁዕ ነው።"
9ይህ ብፅዕና ለተገረዙት ብቻ ነው
ወይስ ላልተገረዙትም? የአብርሃም እምነቱ
ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት ብለናል። 10ታዲያ
እንዴት ተቈጠረለት? ከተገረዘ በኋላ ነው
ወይስ ከመገረዙ በፊት? የተቈጠረለት
ከተገረዘ በኋላ ሳይሆን ከመገረዙ በፊት
ነው። 11ሳይገረዝ በነበረው እምነት ላገኘው
ጽድቅ፣ የመገረዝን ምልክት ይኸውም
የጽድቅን ማኅተም ተቀ በለ፤ ስለዚህ
ለሚያምኑ ነገር ግን ላልተገረዙት ጽድቅ
ይቈጠርላቸው ዘንድ የሁሉ አባት ነው።
12እርሱ ለተገረዙትም አባት ነው፤ መገረዝ
ብቻ ሳይሆን፣ አባታችን አብርሃም ከመገረዙ
በፊት የነበረውን የእምነቱን ፈለግ ለሚከተሉ
ሁሉ ነው። 13እርሱ የዓለም ወራሽ እንዲሆን
አብርሃምና ዘሩ ተስፋን የተቀበሉት በሕግ
በኩል አልነበረም፤ ነገር ግን በእምነት
ከሆነው ጽድቅ ነው።
14በሕግ የሚኖሩት ወራሾች ከሆኑ፣
እምነት የማይጠቅም፣ ተስፋም ከንቱ በሆነ
ነበር፤ 15ሕግ ቍጣን ያስከትላል፤ ሕግ
በሌለበት ግን መተላለፍ አይኖርም።
16ስለዚህ ተስፋው በእምነት መጥቶአል፤
ይኸውም ተስፋው በጸጋ እንዲሆንና

4፥1 ሮሜ8፥31፤ ሉቃ3፥8
4፥2 1ቆሮ1፥31
4፥3 ቍ 5፥9፥22፤ ዘፍ15፥6፤ ገላ3፥6፤ ያዕ2፥23
4፥4 ሮሜ11፥6
4፥5 ቍ 3፥9፥22፤ ሮሜ9፥30
4፥8 መዝ32፥1፥2፤ 103፥12፤ 2ቆሮ5፥19
4፥9 ቍ 3፤ ሮሜ3፥30
4፥11 ቍ 16፥17፤ ዘፍ17፥10፥11፤ ሉቃ 3፥8፤ ሮሜ3፥22
4፥13 ዘፍ17፥4-6፤ ሐዋ13፥32፤ ሮሜ9፥30፤ ገላ3፥16፥29
4፥14 ገላ3፥18
4፥15 ሮሜ7፥7-25፤ 7፥12፤ 3፥20፤ 5፥13፤ 7፥7፤ 1ቆሮ15፥56፤ 2ቆሮ3፥7፤
4፥15 ገላ3፥10 4፥16 ቍ 11፤ ሉቃ3፥8፤ ሮሜ3፥24፤ 15፥8፤ ገላ3፥16

---

እንዲሁም በእምነት ጻድቅ ሆኖ መገኘት ሕጉን ከትክክለኛ ዐላማውና ተግባሩ ጋር ማጽናት ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቁና በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን በማግኘቱ የእግዚአብሔርን ሕግ ማክበርና መታዘዝ ይችላል (8፥2-4ን ይመ)።

**4፥3 አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤** ሥራ ሳይታከል (ሕግን በመጠበቅ) በእምነት መጽደቅ የአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን፣ የብሉይ ኪዳንም አስተምህሮ ነው። ጳውሎስ ሙሴን በመጥቀስ አብርሃም የእምነት ምሳሌ እንደሆነ ይናገራል። አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ እምነት ነበረው፤ ይኸውም ከአምላኩ ጋር በታማኝነት የተሳሰረ፣ የተስፋ ቃሉን ያመነ (ቍ 20፥21፤ ዘፍ 12፥1-3፤ 15፥5-6) በመታዘዝም እምነቱን የገለጸ ነበር (ዘፍ 12፥1-4፤ 22፥1-19፤ ዕብ 11፥8-19፤ ያዕ 2፥21-22፤ በገጽ 47 ላይ፣ *"የአብርሃም መጠራት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥5 እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል፤** የአብርሃም እምነት ጽድቅ ሆኖ ተቈጥሮለታል። ሰውን ለድነት የሚያበቃው እምነት ከውጤት አንጻር ሲታይ ከጽድቅ እኩል ይቈጠራል።

(1) ጳውሎስ ምዕራፍ 4 ላይ «ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል» ወይንም «ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት» የሚለውን ሐሳብ በምዕራፍ አራት ውስጥ ብዙ ጊዜ የተጠቀመ ሲሆን በእያንዳንዱ ውስጥም እምነት ወይም ማመን ከመቈጠር ጋር እንደተያያዘ አመልክቷል (ዘፍ 15፥6 እና ማብ ይመ)።

(2) የአማኙ እምነት ጽድቅ ሆኖ መቈጠሩ፣ የእምነት ወይም ለክርስቶስ የመሰጠት ውጤት ብቻ አይደለም፤ ከሁሉ በላይ የመለኮታዊው ጸጋና ምሕረት ውጤት ነው (ቍ 16)።

(3) እግዚአብሔር የአማኞች ልብ በእምነት ወደ ክርስቶስ መመለሱን ሲመለከት ኀጢአታቸውን እንዲሁ ይቅር ከማለቱም በላይ እምነታቸውንም ጽድቅ እንደሆነ በመቍጠር እንደ ልጆቹ ይቀበላቸዋል (ቍ 5-8፤ በገጽ 1735 ላይ፣ *«ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ጽድቅ ሆኖ ከተቈጠረው ከዚህ እምነት ጋር እግዚአብሔር ለመቀደስ የሚያስችለውን ጸጋውን ይሰጣል (ቍ 16፤ 5፥2፤ ፊል 3፥9፤ ቲቶ 3፥5-7)።

(4) እንደ ጽድቅ የሚቈጠረውና ይቅርታን የሚያስገኘው እምነት፣ በክርስቶስና በሚያስተሰርየው ሞቱ ላይ ያረፈው እምነት ነው (3፥24-26)። ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሥዋዕት ሆኖ ከሞተው ሞት በቀር ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት መንገድ ከቶ የለም (5፥10 እና ማብ ይመ)።

**4፥7 መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፤** ይህ ከመዝ 32፥1-2 ላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ዳዊትም (መዝ 32፥2 እና ማብ ይመ) ሆነ ጳውሎስ እንደ ጽድቅ የተቈጠረው እምነታችን የኀጢአት ይቅርታንና ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን እንደሚጨምር መገንዘባቸውን ያመለክታል። በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ የተመሠረተና በክርስቶስ የመስቀል ሞት እውን የሆነ ስጦታ ነው (ቍ 5 እና ማብ ይመ፤ ከ2ቆሮ 5፥19፡21 ጋር ያነጻጽሩ)።

**4፥12 አባታችን አብርሃም ... የነበረውን የእምነቱን፤** የአብርሃም እምነት ጽኑ፣ ታማኝ፣ ታዛዥ፣ እየጠነከረ የሚያድግና ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሰጥ እውነተኛ እምነት ነበር (ቍ 16-21)። እንዲህ ዐይነቱ እምነት ነው የእግዚአብሔር ልጆች የሚያደርገን።

**4፥16 ተስፋው በእምነት መጥቶአል፤** አማኞች የሚድኑት በእምነት በጸጋ ብቻ ነው። ይሁንና ለድነት ስለሚያበቃው እምነት የሚናገሩ ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው። (1) ሰው በእምነት ሲድን የሚድነው ለድነት በሚያበቃው እምነት ብቻ አይደለም። ያዕቆብ፣ «ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው» (ያዕ 2፥14-26) ሲል፣ ጳውሎስ ደግሞ «በፍቅር የሚገለጽ እምነት» (ገላ 5፥6) ይላል። ለድነት የሚያበቃው እምነት ሕያው በመሆኑ ለክርስቶስ የሚገባውን ታዛዥነትና ፍቅር እንዲሁም ለሌሎች ለሚደረገው አገልግሎት ትልቅ ግምት የሚሰጥ ነው። ከልብ የሆነ ንስሓ መግባትን እንዲሁም ክርስቶስን

ለአብርሃም ዘር ሁሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ
ነው፤ ይህም በሕግ የእርሱ ለሆኑት ብቻ
ሳይሆን፣ በእምነት የአብርሃም ለሆኑትም
ነው፤ እርሱም የሁላችን አባት ነው፤ [17]ይህም
"የብዙ ሕዝብ አባት አድርጌሃለሁ" ተብሎ
እንደ ተጻፈው ነው፤ እርሱም ለሙታን
ሕይወትን በሚሰጥ፣ ያልነበረውንም እንደ
ነበረ በሚያደርግ፣ ባመነበት አምላክ ፊት
አባታችን ነው።
[18]"ዘርህም እንዲሁ ይሆናል" ተብሎ
ለእርሱ በተነገረው መሠረት፣ ምንም ተስፋ
በሌለበት፣ አብርሃም በተስፋ አምኖ የብዙ
ሕዝብ አባት ሆነ። [19]እርሱ የመቶ ዓመት
ሰው ሆኖ ሳለ፣ የራሱም ሰውነት ሆነ የሣራ
ማሕፀን ምውት እንደ ነበረ እያወቀ በእምነቱ
አልደከመም። [20]ይልቁንም በእምነቱ
በመጽናት ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ እንጂ፣
የእግዚአብሔርን ተስፋ አልተጠራጠረም፤
1ቆሮ [21]እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም
13፥2 በሙሉ ልብ ርግጠኛ ነበር። [22]ስለዚህ፣
"ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።" [23]"ጽድቅ
ሆኖ ተቈጠረለት" የሚለው ቃል የተጻፈው
ለእርሱ ብቻ አይደለም፤ [24]ነገር ግን
እግዚአብሔር ጽድቅ አድርጎ ለሚቈጥርልን፣
ጌታችን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው በእርሱ
ለምናምን ለእኛም ጭምር ነው። [25]እርሱ ስለ
ኀጢአታችን እንዲሞት ዐልፎ ተሰጠ፤ እኛን
ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ።

## ሰላምና ደስታ

5 እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን[a]። [2]በእርሱም
በኩል አሁን ወደ ቆምንበት ጸጋ በእምነት
መግባት ችለናል፤ የእግዚአብሔርንም ክብር
ተስፋ በማድረግ ሐሤት እናደርጋለን[a]።
[3]በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም

4፥17 ዘፍ17፥5፤ ኢሳ48፥13፤ ዮሐ5፥21፤ 1ቆሮ1፥28
4፥18 ቊ 17፤ ዘፍ15፥5
4፥19 ዘፍ17፥17፤ 18፥11፤ ዕብ11፥11፡12
4፥20 1ሳሙ30፥6፤ ማቴ9፥8
4፥21 ዘፍ18፥14፤ ማቴ19፥26
4፥22 ቊ 3
4፥24 መዝ102፥18፤ ዕን2፥2፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ10፥9፤ 15፥4፤ 1ቆሮ9፥10፤ 10፥11፤ 2ጢሞ3፥16፡17፤ 1ጴጥ1፥21
4፥25 ኢሳ53፥5፡6፤ ኢሳ53፥11፤ ሮሜ5፥6፡8፤ 8፥32፤ 1ቆሮ6፥11፤ 2ቆሮ5፥21፤ ሮሜ3፥24፤ 5፥1፡9፡16፡18፤ 8፥30፤ 2ቆሮ5፥15
5፥1 ቊ 10፤ ሉቃ2፥14፤ ሮሜ4፥25፤ 3፥28
5፥2 1ቆሮ15፥1፤ ኤፌ2፥18፤ 3፥12፤ ዕብ3፥6
5፥3 ማቴ5፥12፤ ዕብ10፥36

*[a]5፥1፡2፡3 ወይም ሰላም ይኑረን፤ እናድርግ፤ እናድርግ*

ጌታ አድርጎ በመቀበል ለእርሱ መገዛትን ሳያካትት እግዚአብሔር እንዲሁ በደፈናው ኀጢአትን ይቅር እንደሚል የሚቀበል እምነት ለድነት ከሚያበቃው ከአዲስ ኪዳን እምነት የጐደለ ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በ"እምነት" ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የድነትን ሰፊውን ገጽታ ችላ ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በእምነት መዳን ከኩነኔ መዳንን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ፣ ለቅድስናና ለመልካም ሥራ መዳንንም ያቅፋል (ኤፌ. 2፥10)።

**4፥16 በጸጋው እንዲሆን፤** እግዚአብሔር የሚሰጠው ድነት፣ ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና በሕግ ፍጹም በመታዘዝ የሚገኝ ቢሆን ኖሮ ማንም ሊድን አይችልም ነበር፤ ሕጉን ሙሉ በሙሉ መፈጸም አይቻልምና። ነገር ግን በእምነት በጸጋ ብቻ የሚገኝ ስለሆነ ወደ እግዚአብሔር የሚመለስ ሁሉ ይድናል። እግዚአብሔር ኀጢአታችንን በምሕረቱ ይቅር በማለት ሕይወታችንን ሊለውጥና የእግዚአብሔር ልጆች ሊያደርገን መለኮታዊ ጸጋውን (መንፈሱንና ኀይሉን) ይሰጠናል (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥22 ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት፤** ጳውሎስ ስለመጽደቅ በምዕ 4 ላይ ሲያብራራ የትም ቦታ ላይ የእግዚአብሔር ወይም የክርስቶስ ጽድቅ ለአማኙ እንደ ተቈጠረ ወይም እንደ ተላለፈ አይናገርም። መጽደቅ የመጣው የክርስቶስ የብሉይ ኪዳንን ሕግ መጠበቅ ወደ አማኙ ሲተላለፍ ነው ብለን መናገር የለብንም። ሕግን በመጠበቅ የሚተላለፍ ከሆነ ጽድቅ ሆኖ ከተቈጠረው ከአብርሃም እምነት የተለየ ይሆናል (ቊ 12)፤ የተስፋ ቃሉን ያጣጥላል (ቊ 14)፣ ድነትንም የጸጋ ሳይሆን ... ሥራ ውጤት ያደርገዋል (ቊ 16)። ጳውሎስ ... ም ቅድስና "በሕግ በኩል" (ቊ 13) ... ሔር ምሕረት፣ ጸጋ፣ ፍቅርና ይቅርታ ... እንደሚመጣ በእጽንዖት የተናገረ ... ም እምነትም ይኸውም ማመኑ፣ ... ጋር መጣበቁ፣ ልበሙሉነቱ እንዲሁም ... በተስፋው የነበረው የጸና ዋስትና በእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ ጽድቅ ሆኖ እንደ ተቈጠረ አመልክቷል (ቊ 16-22)።

**4፥25 ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ፤** በሕይወታችን የሚሠራው የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሀልዎትና ጸጋ ከሌለ መጽደቅ አይኖርም። መጽደቅ ቀደም ሲል የተከናወነ ብቸኛ የፍርድ ተግባር ብቻ ሳይሆን፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት በማድረግ የሚካሄድ የዕድሜ ልክ ጽድቅ ነው።

**5፥1 እንግዲህ በእምነት ስለጸደቅን፤** በእምነት የሆነ ጽድቅ ለአማኙ ብዙ ውጤቶችን ያስገኛል፤ እነዚህም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን (በገጽ 1150 ላይ፤ "*የእግዚአብሔር ሰላም*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ጸጋን፣ ተስፋን፣ ዋስትናን፤ መከራን፤ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ መንፈስ ቅዱስን፣ ከቍጣ መዳንን፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን፣ ከክርስቶስ ሕይወትና ሀልዎት የተነሣ ድነትንና በእግዚአብሔር ደስ መሰኘትን (ቊ 1-11)።

**5፥3 በመከራችንም ሐሤት እናደርጋለን፤** መከራ በክርስቶስ ካገኘነው ድነት የተነሣ ከምንቀበላቸው በረከቶች አንዱ እንደ ሆነ ጳውሎስ ይገልጻል፤ (1) "መከራ" የሚለው ቃል ጫና የሚፈጥሩብንን ማንኛውንም ዐይነት ችግር ያመለክታል፤ ይህም የገንዘብ ወይም የሥጋ ፍላጎት አለመሟላትን፣ ፈታኝ ሁኔታዎችን፣ ሐዘንን፣ ሕመምን፣ ስደትን፣ እንክብካቤ ማጣትን ወይም ብቸኝነትን ይጨምራል (በገጽ 744 ላይ፣ "*የጻድቃን መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በእነዚህ ችግሮች መካከል የእግዚአብሔርን ፊት በትጋት እንድንፈልግና በሕይወት የሚያጋጥሙንን መከራ እንድናሸንፍ የሚረዳንን የጽናት መንፈስ ባሕርይ እንዲኖረን ጸጋው ያግዘናል። መከራ ወደ ተስፋ መቍረጥ ሳይሆን ወደ ጽናት የሚመራ (ቊ 3) ሲሆን፣ ጽናት ደግሞ የተፈተነን ባሕርይ ይፈጥራል (ቊ 4)፤ የተፈተነ ባሕርይ ደግሞ የማያሳፍርና እያደገ የሚሄድ ተስፋን ይፈጥራል (ቊ 5)።

(3) የእግዚአብሔር ጸጋ አሁን ካጋጠመን ችግር አልፈን በእግዚአብሔር ላይ ያለንን የማይናወጥ ተስፋ እንድንመለከት እንዲሁም በአዲስ ሰማይና ምድር

ሐሤት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ
ትዕግሥትን እንደሚያስ ገኝ እናውቃለን።
4ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ
ባሕርይን፣ የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን፤
5ይህም ተስፋ ለዕፍረት አይዳርገንም፤
እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን
በልባችን አፍስሶአልና።
6ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲደርስ፣
ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና።
7ለጻድቅ የሚሞት ሰው ማግኘት እጅጉን
ያዳግታል፤ ለደግ ሰው ሲል ሊሞት
የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። 8ነገር
ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ
እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለ ውን
የራሱን ፍቅር ያሳያል።
9እነሆ በደሙ ከጸደቅን፣ ይልቁንማ
በእርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ቍጣ እንዴት
አንድንም! 10የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ
ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን
በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት
የላቀ አይሆንም! 11ይህ ብቻ አይደለም፤
ነገር ግን አሁን ዕርቅን ባገኘንበት በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ
ሐሤት እናደርጋለን።

5፥5 ቍ 8፤ ዮሐ3፥16፤ ሐሥ2፥33፤ ሮሜ310፥45፤ ፊል1፥20፤ ቲቶ3፥5፥6፤ ዕብ3፥6፤ 1ዮሐ3፥2፥3
5፥6 ቍ 8፥10፤ ማር 1፥15፤ ሮሜ4፥25፤ ኤፌ1፥10፤ ገላ4፥4
5፥8 ዮሐ3፥16፤ 15፥13፤ 1ጴጥ3፥18፤ 1ዮሐ3፥16፤ 4፥10
5፥9 ሮሜ4፥25፤ 3፥25፤ 1፥18
5፥10 ቍ 11፤ ሮሜ8፥34፤ 11፥15፤ 11፥28፤ 2ቆሮ5፥18፥19፤ ቈላ1፥20፥21፥22፤ ዕብ7፥25
5፥11 ቍ 10
5፥12 ቍ 14፥15፥ 16፥17፥18፤ ዘፍ2፥17፤ 3፥1-7፤ 1ቆሮ15፥21፥22፤ 3፥19፤ ሮሜ3፥9፤ 6፥23

## ሞት በአዳም፣ ሕይወት በክርስቶስ

12ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል
ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት
በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ
ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም
ኀጢአትን ሠርተዋል፤ 13ሕግ ከመሰጠቱ
በፊት ኀጢአት በዓለም ላይ ነበር፤ ነገር
ግን ሕግ በሌለበት ኀጢአት አይቈጠርም።
14ይሁን እንጂ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ
ድረስ ባሉት፣ እንደ አዳም ሕግን በመጣስ
ኀጢአት ባልሠሩት ላይ እንኳ ሞት ነግሦ፤
አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ ነበረ።
15ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን
አይደለም፤ በአንድ ሰው መተላለፍ ብዙዎቹ
ከሞቱ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ ሰው፤
ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመጣው
ስጦታ ለብዙዎች እንዴት አብልጦ
ይትረፈረፍ! 16ደግሞም የእግዚአብሔር
ስጦታ እንደ አንዱ ሰው የኀጢአት ውጤት
አይደለም፤ ምክንያቱም ፍርዱ የአንድን
ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ፤
ስጦታው ግን እያሌ መተላለፍን ተከትሎ
ጽድቅን አመጣ። 17በአንድ ሰው መተላለፍ

5፥13 ሮሜ4፥15 5፥14 ዘፍ3፥11፥12፤ 1ቆሮ15፥22፥45
5፥15 ቍ 12፥18፥19፤ ሐሥ15፥11 5፥17 ቍ 12፤ ዮሐ10፥10

ላይ ጽድቅንና ቅድስናን ለመመሥረት (1ተሰ 4፥13) የጌታን መመለስ እንድንናፍቅ ያደርገናል (ራእ 19-22) ይህ በእንዲህ እንዳለም፣ እግዚአብሔር በመከራችን ሊያጽናናንና ክርስቶስ በአጠገባችን እንዳለ እንዲሰማን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ፍቅሩን በልባችን ያፈሳል (ዮሐ 14፥16-23)።

**5፥5 እግዚአብሔር ... ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና፤** ክርስቲያኖች፥ በተለይ በመከራ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ፍቅር (እግዚአብሔር ለአማኞች ያለውን ፍቅር) በልባቸው ይለማመዳሉ። "አፍስሶአልና" የሚለው ግስ በውድ ቀጣይ ተግባርን የሚያመለክት ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን በፍቅሩ ማረስረሱን እንደሚቀጥል ያስገነዝባል። በመከራ የሚያጸናንን (ቍ 3) ወደፊት ስለሚጠብቀን ክብር ያለው ተስፋ ሕልም እንዳልሆነ (ቍ 4-5) የሚያረጋግጥ ልን ሁልጊዜ አብሮን ያለው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ክርስቶስ ለእኛ ሲል መመለሱ የተረጋገጠ እውነት ነው (ከ8፥11፤ ከመዝ 22፥4-5፤ ከዮሐ 14፥3 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥10 *በሕይወቱማ መዳናችን*፤** የአማኙ ድነት፣ ይቅርታን ባገኘበትና ከእግዚአብሔር ጋር በታረቀበት በክርስቶስ ደምና በትንሣኤው ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ልምምድ ቀዳሚው ድነት ነው (3፥21-26፤ 4፥5-9)። አማኙ ሕያው በሆነ እምነትና ሕያው ከሆነው ክርስቶስ ጋር ባለው ኅብረት መዳኑን ይቀጥላል (በገጽ 1735 ላይ፣ "*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ጠላቶች ሳለን ስለእኛ እንዲሞት ልጁን እስከ ድረስ እግዚአብሔር ከወደደን፣ አሁንማ ልጆቹ እንደመሆናችን በልጁ ባለን እምነት ከሚመጣው ቍጣ እኛን ሊታደግ እንዴት የሚያስፈልገውን ሁሉ አያደርግ (4፥22—5፥2፤ 5፥9-10፤ 1ቆሮ 1፥30፤ ፊል 2፥12-16፤ ቈላ 3፥3-4፤ 1ተሰ 1፥10፤ 2ጢሞ 2፥12፤ ያዕ 1፥12፤ ራእ 2፥7 እና ማብ ይመ)።

**5፥12 ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም ... ገባ፤** በአዳም ውድቀት ምክንያት ኀጢአት ቋሚ ባሕርይ ወይም ራሱን የቻለ ኀይል ሆኖ ወደ ሰው ዘር ገባ (ቍ 17፥19፤ ዘፍ 3፤ 1ቆሮ 15፥21-22)።
(1) ከዚህም የተነሣ ሁለት ውጤቶች ተከተሉ፤
(ሀ) ኀጢአትና ጥፋት ወደ አዳም ልብና ሕይወት ገቡ።
(ለ) አዳም ለሰው ሕይወት ሁሉ መበከል ምክንያት በመሆን ኀጢአትን ወደ ሰው ዘር ሁሉ አስተላለፈ። ከዚያም ሰው ሁሉ ተወልዶ ወደ ዓለም ሲመጣ የኀጢአትና የክፋት ዝንባሌ ያዘ ነው (ቍ 19፤ 1፥21፤ 7፥24፤ ዘፍ 6፥5፥12፤ 8፥21፤ መዝ 14፥1-3፤ ኤር 17፥9፤ ማር 7፥21-22፤ 1ቆሮ 2፥14፤ ገላ 5፥19-21፤ ኤፌ 2፥1-3፤ ቈላ 1፥21፤ 1ዮሐ 5፥19)።
(2) ሞት በኀጢአት ምክንያት ወደ ዓለም የገባ ሲሆን፣ "ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል" ስለሚል ሰው ሁሉ ይሞታል (ቍ 12፥14፤ ከ3፥23፤ ከዘፍ 2፥17 እና ከ3፥29 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 765 ላይ፤ "*ሞት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥14 ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ባሉት ... ላይ ሞት ነግሦ፤** የሰው ዘር የሚሞተው እንደ አዳም የሞት ፍርድ የሚያስከትለውን የእግዚአብሔርን የቃል ሕግ ስለተላለፈ ሳይሆን (ቍ 13-14)፣ በተፈጥሮውና በሥራው ኀጢአተኛ በመሆኑ እንዲሁም በልቡ የተጻፈውን የሕሊና ሕግ ተላላፊ ስለሆነ ነው (2፥14-15)።

**5፥15 የእግዚአብሔር ጸጋ ... እንዴት አብልጦ ይትረፈረፍ፤** ከቍ 12-21 ላይ ጳውሎስ የውድቀትን መዘዝ ሊሽር የሚችለውን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የቀረበውን መቤዠት ፍጹም ብቃት እንዳለው ይገልጻል። ይህ የመልእክቱ ዋና ሐሳብ ነው፤ አዳም ኀጢአትንና ሞትን አስከተለ፤ ክርስቶስ ደግሞ ጸጋንና ሕይወትን አመጣ (ቍ 17)።

# እምነትና ጸጋ

*ሮሜ 5፥2 "ይህም የሆነው ኀጢአት በሞት እንደነገሠ ሁሉ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ይገኝ ዘንድ ጸጋ በጽድቅ እንዲነግሥ ነው።"*

---

ድነታችን ከእግዚአብሔር በጸጋ የተሰጠ ነው፤ ይሁን እንጂ ተፈጻሚ የሚሆነው ሰው በእምነት ሲቀበለው ነው። የድነትን ሂደት ለመረዳት እነዚህን ሁለት ቃላት መገንዘብ የግድ ነው።

ለድነት የሚያበቃ እምነት፤ እግዚአብሔር ለድነታችን የሚጠብቅብን በክርስቶስ ኢየሱስ እንድናምን ብቻ ነው። በክርስቶስ ማመን ማለት በአፍ የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስን በጌትነቱና በአዳኝነቱ ለመከተል ከሚሹ አማኞች የሚመነጭ ልባዊ እርምጃ ነው (ማቴ 4፥19፤ 16፥24፤ ሉቃ 9፥23-25፤ ዮሐ 10፥4:27፤ 12፥26፤ ራእ 14፥4)። (1) የአዲስ ኪዳን የእምነት እሳቤ አራት ዐበይት ፍሬ ሐሳቦችን ያጠቃልላል፤

(ሀ) እምነት ማለት የተሰቀለውንና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን እንደግል አዳኛችንና ጌታችን አድርጎ ከልብ ማመንና በእርሱም መደገፍ ማለት ነው (ሮሜ 1፥17 እና ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳን ለተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዳችንንና ሁለንተናችንን በማስገዛት በሙሉ ልባችን ማመንን ያካትታል (ሮሜ 6፥17፤ ኤፌ 6፥6፤ ዕብ 10፥22)።

(ለ) እምነት በእውነተኛ ጸጸት በክርስቶስ በኩል ከኀጢአት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው (ሐዋ 17፥30፤ 2ቆሮ 7፥10)። ለድነት የሚያበቃ እምነት ሁል ጊዜ የንስሓ እምነት ነው (ሐዋ 2፥37-38 ይመ፤ ማቴ 3፥2 እና የንስሓ ማብራሪያውን ይመ)።

(ሐ) እምነት እግዚአብሔርን በማመን፣ ለእርሱ ምስጋናን በማቅረብ፣ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን በማግኘት በሚነሣሣየኑሮ ዘይቤ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቃሉ መታዘዝን ያካትታል (ዮሐ 3፥3-6፤ 14፥15:21-24፤ ዕብ 5፥8-9) ስለዚህ እምነትና መታዘዝ የማይነጣጠሉ ናቸው (ሮሜ 1፥5፤ ከሮሜ 16፥26 ጋር ያነጻጽሩ)። ራስን ለቅድስና ሳይሰጡ ድነት አለኝ ማለት ተገቢ አይደለም።

(መ) እምነት፤ ራስን በፍቅር፣ በምስጋናና በታማኝነት በመግለጽ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከልብ የሆነ መስጠትና ቀረኝትን ያካትታል። እምነት በጥልቀት ሲታይ ከፍቅር የሚለይ አይደለም። እምነት በክርስቶስ ላይ ባተኰረ፣ በግል መሥዋዕትነትና ራስን በመስጠት ተግባር ላይ የተመሠረተ ነው (ማቴ 22፥37፤ ዮሐ 21፥15-17፤ ሐዋ 8፥37፤ ሮሜ 6፥17፤ ገላ 2፥20፤ ኤፌ 6፥6፤ 1ጴጥ 1፥8)።

(2) ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርጎ ማመን አንድ ጊዜ የሚከናወን ተግባር ሲሆን፣ በቀጣይነትም ሊያድግና ሊጐለብት የሚገባው ነው (ዮሐ 1፥12 እና ማብ ይመ)። በአንዱ ለእኛ በሞተው ላይ እምነት ስላለን (ሮሜ 4፥25፤ 8፥32፤ 1ተሰ 5፥9-10)፤ እምነታችን ሊያድግና ታላቅ ሊሆን ይገባል (ሮሜ 4፥20፤ 2ተሰ 1፥3፤ 1ጴጥ 1፥3-9)። በእግዚአብሔር መታመንና ለእርሱ መታዘዝ ወደ ታማኝነትና ወደ መስጠት ያደርሳሉ (ሮሜ 14፥8፤ 2ቆሮ 5፥15)። ታማኝነትና መሰጠት ደግሞ ለጌታ ኢየሱስ ልዩ ፍቅርና ከእርሱም ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት እንዲኖረን ያደርጋሉ (ፊል 1፥21፤ 3፥8-10፤ ዮሐ 15፥4 እና ማብ፤ ገላ 2፥20 እና ማብ ይመ)። ይህ በክርስቶስ ያለን እምነት ከእግዚአብሔር ጋር ወደ አዲስ ኅብረት በማምጣት ከቍጣው ነጻ ያደርገናል (ሮሜ 1፥18፤ 8፥1)፤ ከዚህ አዲስ ኅብረት የተነሣም ለኀጢአት ሞተን (ሮሜ 6፥1-18) የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንሆናለን (ገላ 3፥5፤ 4፥6)።

ጸጋ፤ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ ፍቅሩን በማሳየት የጸጋና የምሕረት አምላክ መሆኑን ገልጸአል፤ ይህም እነርሱ ስለተገባቸው ሳይሆን ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ለገባው ተስፋ ታማኝ ለመሆን ስለወደደ ነው (ዘፀ 6፥9 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 129 ላይ፣ "የፋሲካ በዓል" በሚልና በገጽ 202 ላይ ደግሞ "የሰርየት ቀን" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ይህን ሁበይ ርእስ በመቀጠል ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነ የእግዚአብሔር ሀልዎትና ፍቅር መሆኑን በመግለጽ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለአማኞች የተሰጠ ምሕረት፣ ይቅርታ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማድረግ መሻትና ኀይል መሆኑን አስተምረዋል (ዮሐ 3፥16፤ 1ቆሮ 15፥10፤ ፊል 2፥13፤ 1ጢሞ 1፥15-16)። የአማኙ ሕይወት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ በዚህ ጸጋ ላይ የተደገፈ ነው።

(1) እግዚአብሔር ለማያምኑ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ያምኑ ዘንድ ጸጋን ይሰጣል (1ቆሮ 1፥4፤ ኤፌ 2፥8-9፤ ቲቶ 2፥11፤ 3፥4)።

(2) እግዚአብሔር ለአማኞች "ከኀጢአት ነጻ ይወጡ ዘንድ" (ሮሜ 6፥20፡22)፣ እንደበጎ ፈቃዱ ማድረግም መፈለግም ይችሉ ዘንድ (ፊል 2፥13 ይመ፤ ከቲቶ 2፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 7፥21 እና ማብ ይመ) ይጸልዩ ዘንድ (ዘካ 12፥10)፣ በክርስቶስ ያድጉ ዘንድ (2ጴጥ 3፥18) እናም ለክርስቶስ ይመሰክሩ ዘንድ (ሐሥ 4፥33፤ 11፥23) ጸጋን ይሰጣቸዋል።

(3) የእግዚአብሔርን ጸጋ በትጋት ልንሻና ልንፈልግ ይገባናል (ዕብ 4፥16)። የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልባቸው አንዳንድ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማጥናትና መታዘዝ (ዮሐ 15፥1-11፤ 20፥31፤ 2ጢሞ 3፥15) የምሥራቹ ቃል ሲሰበክ መስማት (ሉቃ 24፥47፤ ሐሥ 1፥8፤ ሮሜ 1፥16፤ 1ቆሮ 1፥17-18)፣ መጸለይ (ዕብ 4፥16፤ ይሁ 20) መጾም (ማቴ 4፥2፤ 6፥16)፣ ክርስቶስን በዝማሬና በመንፈሳዊ ቅኔ ማምለክ (ቈላ 3፥16)፣ ሳያቋርጡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት (ኤፌ 5፥18) እንዲሁም የጌታን እራት መካፈል (ሐሥ 2፥42፤ ኤፌ 2፥9 እና ማብ ይመ)።

(4) የእግዚአብሔር ጸጋ እምቢ ሊባል የሚቻል (ዕብ 12፥15)፣ በከንቱ የሚቀበሉት (2ቆሮ 6፥1)፣ ሊጠፉ የሚችል (1ተሰ 5፥19)፣ ገለል ሊያደርጉት የሚቻልና (ገላ 2፥21) በአማኙ ሊተው የሚቻል ነው (ገላ 5፥4)።

ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሠ
ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የትትረፈረፈ ጸጋና
የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ
ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት
አብልጠው በሕይወት አይነግሡ!
18ከእንግዲህ በአንድ ሰው መተላለፍ
የተነሣ ኵነኔ በሁሉ ሰው ላይ እንደ መጣ፣
እንዲሁም በአንዱ የጽድቅ ሥራ ለሰው ሁሉ
ሕይወትን የሚ ሰጥ ጽድቅ ተገኘ። 19በአንዱ
ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች
እንደ ሆኑ፣ በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ
ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።
20ሕግ በመምጣቱ መተላለፍ በዛ፤ ነገር
ግን ኀጢአት በበዛበት ጸጋ አብልጦ የተት
ረፈረፈ ሆነ፤ 21ይህም የሆነው ኀጢአት
በሞት እንደ ነገሠ ሁሉ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ
በኩል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ደገኝ ዘንድ
ጸጋ በጽድቅ እንዲነግሥ ነው።

5፥18 ቍ12፤
ኢሳ53፥11፤
ሮሜ4፥25
5፥19 ቍ12፤
ሮሜ3፥9፤ ፊል2፥8
5፥20 ሮሜ3፥20፤
6፥1፤ 7፥7፡8፤
ገላ3፥19፤
1ጢሞ1፥13፡14
5፥21 ቍ12፡14
ማቴ25፥46፤
ሮሜ6፡16፤ 3፥24
6፥1 ቍ15፤
ሮሜ3፥5፡8፤ 8፥31
6፥2 ቍ
6፡10፡11፥18፤
ሮሜ8፥13፤
ቈላ3፥5፤
1ጴጥ2፥24
6፥3 ማቴ28፥19

## ለኀጢአት መሞት፣ በክርስቶስ ሕያው መሆን

6 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ
ኀጢአት እየሠራን እንኑር? 2ከቶ
አይሆንም፤ ለኀጢአት ሞተናል፤ ታዲያ
እንዴት አድርገን ከእንግዲህ በእርሱ
እንኖራለን? 3ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ
እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ
እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?
4ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ
ተነሣ፣ እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት
እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር

6፥4 ቍ6፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ7፥6፤ 2ቆሮ5፥17፤
ኤፌ4፥22-24፤ ቈላ3፥10

**5፥18 ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ጽድቅ፤** በሰው ሁሉ ላይ ያለው ኵነኔ በእያንዳንዱ ሰው እውን የሚሆነው በእግዚአብሔር ላይ እንዲሁም በልባቸው በተጻፈው ወይንም በቃሉ ላይ በተጻፈው የእርሱ መገለጥ ላይ ሲያምፁ ነው (ከ2፥12-16 ጋር ያነጻጽሩ)። “ሕይወትን የሚሰጥ ጽድቅ” የተባለው ለሰው ሁሉ የተዘጋጀ ነው፤ ይህንንም ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑና ጸጋውን፣ ሕይወቱንና የጽድቅ ስጦታውን በእርሱ በኩል ሲቀበሉ የራሳቸው ያደርጉታል (ቍ 17)።

**5፥21 ጸጋ፤** ስለ “ጸጋ” በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ትርጕም በተመለከተ የተሰጠውን ማብራሪያ ለማግኘት በገጽ 1746 ላይ፣ “እምነትና ጸጋ” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**6፥1 ኀጢአት እየሠራን እንኑር?** አማኞች ኀጢአት በመሥራት ቢቀጥሉ እንኳን በክርስቶስ በኩል ካለው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ከኵነኔ ይጠበቃሉ የሚለውን የተሳሳተ ሐሳብ ጳውሎስ በምዕ 6 ላይ ይቃወማል። ጳውሎስ ይህንን የጸጋን ትክክለኛ አስተምህሮ የሚያጣምመውን ትምህርት የተቃወመው የሚቀተለውን መሠረታዊ እውነት በማጉላት ነበር፤ “በክርስቶስ” ያሉ እውነተኛ አማኞች የሚለዩት ወደ ክርስቶስ አካል በመጠመቃቸውና ለኀጢአት በመሞታቸው ነው። ከኀጢአት ዓለም ወደ ሕይወት ዓለም ማለትም ክርስቶስ ወዳለበት ዓለም ተሻግረዋል (ቍ 2-12)። እውነተኛ አማኞች ከኀጢአት ፈጽመው ስለተለዩ ኀጢአትን በመሥራት አይቀጥሉም። በአንጻሩ ግን ሰዎች ኀጢአትን በመሥራት ቢቀጥሉ እውነተኛ አማኞች አይደሉም (ከ1ዮሐ 3፥4-10 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ አበክሮ የሚያስገነዝበው ሰዎች በአንድ ጊዜ የኀጢአትም የክርስቶስም ባሮች ሊሆኑ አለመቻላቸውን ነው (ቍ 11-13፤ 16-18)። ለኀጢአት ራሳቸውን ከሰጡ ውጤቱ ኵነኔና የዘላለም ሞት ይሆናል (ቍ 16፡23)።

**6፥1 ኀጢአት፤** (1) አዲስ ኪዳን ኀጢአትን በተለያየ ገጽታው ለመግለጽ አያሌ የግሪክ ቃላትን ይጠቀማል። ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) ሃማርቲያ፣ “መተላለፍ”፣ “ስሕተት መሥራት” ወይም “በእግዚአብሔር ላይ የተሠራ በደል” ማለት ነው (ዮሐ 9፥41)። (ለ) አዲኪያ “ስሕተት መሥራት”፣ “ክፋት”፣ “ኢፍትሐዊነትን” ያመለክታል (1፥18፤ 1ዮሐ 5፥17)። ስሕተት ሁሉ መውደድ ካለመቻል የሚመጣ ስለሆነ የፍቅር እጦት ተብሎ ሊተረጎም ይችላል (ማቴ 22፥37-40፤ ሉቃ 10፥27-37)። በሌላም በኩል አዲኪያ ባሪያ የሚያደርግና የሚያስት በግል ባሕርይ ውስጥ የሚገኝ ኀይል ነው (5፥12፤ ዕብ 3፥13)። (ሐ) አኖሚያ፣ “ክፋትን”፣ “ሥርዐት አልበኝነትን” እና “በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ዐመፀኝነትን” ያመለክታል (ቍ 19፤ 1ዮሐ 3፥4)። (መ) አፒስቲያ፣ “አለማመንን” ወይም “ታማኝ አለመሆንን” ያመለክታል (3፥3፤ ዕብ 3፥12)።

(2) ከነዚህ ፍቺዎች ለኀጢአት መፈጠር ዋና ምክንያት የሚሆነው ነገር ራስ ወዳድነት ነው፤ ይህም የሌሎችን ደህንነትና የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ጕዳይ ሳንል፣ አንድ ነገር ለራሳችን ለማድረግ ወይም ለደስታችን ስንል በሌሎች ላይ ክፉዎች እንድንሆንና በእግዚአብሔርና በሕጉ ላይ እንድናምፅ ያደርገናል። ዞር ዞሮ ኀጢአት ለእግዚአብሔርና ለቃሉ አልገዛም ማለት ነው (1፥18-25፤ 8፥7)። ይኸውም የእግዚአብሔር ጠላት (5፥10፤ ቈላ 1፥21) እንዲሁም ለእርሱ ታዛዥ አለመሆን (11፥32፤ ኤፌ 2፥2፤ 5፥6) ማለት ነው።

(3) ኀጢአት በሰው ውስጥ ያለ ምግባረ ብልሹነት ሲሆን፣ የሰዎችን ቀና ሐሳብ ይጻረራል፤ ዐመፅን ደስ ብሎን እንድንፈጽምና በሌሎች የክፋት ሥራ ደስ እንድንሰኝ ያደርገናል (1፥21-32 ይመ፤ ከዘፍ 6፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። ባሪያ የሚያደርግና የሚያበላሽም ኀይል ነው (3፥9፤ 6፥12፤ 7፥14፤ ገላ 3፥22)። ኀጢአት በሰው ፍላጎት ውስጥ ሥር የሰደደ ነው (ያዕ 1፥14፤ 4፥1-2፤ 1ጴጥ 2፥11 እና ማብ ይመ)።

(4) ኀጢአት በአዳም በኩል ወደ ሰው ዘር የገባ (5፥12)፣ ሁሉንም የበከለ (5፥12)፤ መለኮታዊ ፍርድን ያስከተለ (1፥18)፤ አካላዊና መንፈሳዊ ሞት የሚያመጣ (ቍ 23፤ ዘፍ 2፥17) ሲሆን፣ ኀይሉን የሚያጣውም በክርስቶስና በመዋጀት ሥራው ስናምን ብቻ ነው (5፥8-11፤ ገላ 3፥13፤ ኤፌ 4፥20-24፤ 1ዮሐ 1፥9፤ ራእ 1፥5)።

**6፥2 ለኀጢአት ሞተናል፤** ቍ 11 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥4 በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል፤** ጥምቀት፣ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ተቀብሮ መነሣቱን የሚያመለክት ቢሆንም ከዚህም በላይ ነው። በእውነተኛ እምነት የተደረገ ጥምቀት ኀጢአትን በመቃወም ለክርስቶስ መሰጠትን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ የማያቋርጥ የመለኮታዊ ሕይወት ፍሰትን ያመጣል። (ጥምቀትን በተመለከተ ሐሥ 22፥16 እና ማብ ይመ)። ጥምቀት ማለት ከትንሣኤ ሕይወቱ ጋር በአንድነት እንኖር ዘንድ ከክርስቶስ መሞትና መቀበር ጋር መተባበር ነው (ቍ 4-5)። ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ

ተቀብረናል።
5በሞቱ ከእርሱ ጋር እንደዚህ ከተባበ
ርን፣ በትንሣኤው ደግሞ በርግጥ ከእርሱ
ጋር እንተባበራለን። 6እንግዲህ የኀጢአት
ባሮች እንዳንሆን፣ የኀጢአት ሰውነት[a]
እንዲሻር፣ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር
እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ 7ምክንያቱም
የሞተ ከኀጢአት ነጻ ወጥቶአል።
8ከክርስቶስ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ
ጋር እንደምንኖር እናምናለን።
9ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶአልና፣
ዳግመኛ እንደማይሞት እናውቃለንና፤
ሞት ከእንግዲህ በእርሱ ላይ ጕልበት
አይኖረውም። 10በሞተ ጊዜ፣ ለአንዴና ለመ
ጨረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤ ነገር ግን
በሕይወት መኖርን ለእግዚአብሔር ይኖራል።
11እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ
ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ
ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን
ቍጠሩ። 12ስለዚህ ክፉ መሻቱን ትፈጽሙ
ዘንድ በሚሞት ሥጋችሁ ላይ ኀጢአት
እንዲነግሥበት አታድርጉ። 13ብልቶቻችሁን
የክፋት መሣሪያ አድርጋችሁ ለኀጢአት
አታቅርቡ፤ ይልቁንስ ከሞት ወደ ሕይወት
እንደ ተሻገሩ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን
ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም
የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር
አቅርቡ። 14ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች
ስላልሆናችሁ፣ ኀጢአት አይገዛችሁምና። ሮሜ 8፥1-5

## የጽድቅ ባሮች

15እንግዲህ ምን ይሁን? ከሕግ በታች
ሳይሆን፣ ከጸጋ በታች በመሆናችን ኀጢአት
እንሥራን? በጭራሽ አይገባም! 16ራሳችሁን

6፥5 ቈላ 2፥12፤ 3፥1፤ ... 

6፥5 ቍ 4፥8፤ ሮሜ 8፥11፤ 2ቆሮ 4፥10፤ ኤፌ 2፥6፤ ፊል 3፥10፥11፤ ቈላ 2፥12፤ 3፥1፤ 2ጢሞ 2፥11፤ 5፥24፤ 6፥14
6፥7 ቍ 18
6፥8 ቍ 5
6፥9 ቍ 4፤ ሐሥ 2፥24፤ ራእ 1፥18
6፥10 ቍ 2፤ ዕብ 7፥27
6፥6 ቍ 2፥3-8፤ 16፤ ሮሜ 7፥24፤ 2ቆሮ 4፥10፤ ገላ 2፥20፤ 5፥24፤ ኤፌ 4፥22፤ ፊል 3፥10፤ ቈላ 2፥12፥20፤ 3፥3
6፥11 ቍ 2
6፥12 ቍ 16
6፥13 ቍ 16፥19፤ ሮሜ 7፥5፤ 12፥1፤ 2ቆሮ 5፥14፥15፤ 1ጴጥ 2፥24
6፥14 ቍ 16፤ ሮሜ 2፥12፤ 3፥24
6፥15 ቍ 1፥14
6፥16 ቍ 6፥12፥14፤ 17፥20፥23፤ ዘፍ 4፥7፤ መዝ 51፥5፤ 119፥133፤ ዮሐ 8፥34፤ ሮሜ 5፥21፤ 7፥14፥23፥25፤ 8፥2፤ 2ጴጥ 2፥19

[a] 6፥6 ወይም ኀይል እንዲያጣ

ሁሉ፣ ለድነት በማያበቃው እምነት ውስጥ ያለነው እኛ በእርግጥ በአዲስ ሕይወት እንራመዳለን (ቍ. 5)።

**6፥6 የኀጢአት ሰውነት ... አሮጌው ሰዋችን፤** ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ሁለት የተለያ ገላጭ ሐረጎችን ያሳያል፤ (1) "አሮጌው ሰዋችን"፤ ይህ በኀጢአት የኖረውን አማኙ ዳግም ከመወለዱ በፊት የነበረውን ሕይወት ያመለክታል። አማኙ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንዲቀበልና አዲስ ሰው እንዲሆን ዘንድ ይህ አሮጌው ሰው ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ተሰቀለ (ከገላ 2፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) "የኀጢአት ሰውነት"፡ ይህ ኀጢአተኛ በሆነው ምኞት ቍጥጥር ሥር ያለውን ሥጋ ያመለክታል። ሥጋ ለኀጢአት የነበረው ባርነት አሁን ተሰብሮአል (ከ2ቆሮ 5፥17፤ ከኤፌ 4፥22፤ ከቈላ 3፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህ ጊዜ በኋላ አማኞች አሮጌው አኗኗራቸው ሕይወታቸውንና ሥጋቸውን እንዲገዛ መፍቀድ የለባቸውም (2ቆሮ 5፥17፤ ኤፌ 4፥22፤ ቈላ 3፥9-10)።

**6፥7 ከኀጢአት ነጻ ወጥቶአልና፤** ዮሐ 8፥36 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥10 ለኀጢአት ሞቶአል፤** ክርስቶስ ያለኀጢአት የነበረ ቢሆንም ስለ እኛ ብሎ በኀጢአት ኀይል ተሠቃየ፤ ተዋረደም (5፥21 ይመ፤ ከ2ቆሮ 5፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። ሞቱ የኀጢአትን ዕዳ ለመክፈል የተደረገ ሞት ነበር፤ በትንሣኤው ደግሞ በኀጢአት ኀይል ላይ ድልን ተቀዳጀ። እንደዚሁም፥ በሞቱ ከእርሱ ጋር የተባበሩ በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ (ቍ. 4-5፡10) ከኀጢአት ኀይል ነፃ ወጥተዋል (ቍ. 2፡11)።

**6፥11 ለኀጢአት እንደሞታችሁ ... ራሳችሁን ቍጠሩ፤** በምዕራፍ 6 ላይ ያለው መሠረታዊ እውነት አማኝ በሞቱና በሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር ያለው አንድነት ነው። ስለዚህ እውነተኛ አማኝ ከሆንህ ለኀጢአት ሞተሃልና ይህን እውነት ልብ ልትል ይገባል፤ (1) ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር አንተ ለኀጢአት ሞተሀል፤ እግዚአብሔርም አንተን የሚቈጥርህ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል እንደሞትህና በትንሣኤው አብረህ እንደተነሣህ ነው (ቍ. 5-10)። (2) በመንፈስ ዳግም ስትወለድ ለኀጢአት ሞተሃል (በገጽ 1606 ላይ፣ "ዳግም ልደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ኀጢአትን ለመቃወም (ቍ. 14-18)፣ የሥጋን ሥራ እየገደላችሁ በየዕለቱ ለመሞት (8፥13) እና ለእግዚአብሔር በሚታዘዝ አዲስ ሕይወት ለመኖር (ቍ. 5-14፡18፡22) የክርስቶስ ኀይል ተሰጣችሁ። (3) ለኀጢአት እንደሞታችሁ እንዲሁም ኀጢአትን በመቃወም ለክርስቶስ ለመኖር እንደወሰናችሁ በማወጅ በውሃ ስትጠመቁ ለኀጢአት ሞታችኋል (ቍ. 3፡5፤ 6፥4 እና ማብ ይመ)።

**6፥12 ኀጢአት እንዲነግሥበት አታድርጉ፤** የኀጢአት ዙፋን ስለተገለበጠ መልሶ ለመቈጣጠር የሚያደርገውን ጥረት ሳታቋርጡ መቃወም አለባችሁ። ኀጢአት አስቀድሞ በሥጋ መሻት ላይ ለመሠልጠን ስለሚሞክር፣ ይህን መሻት በክርስቶስ ባለ እምነት ልንቈጣጠረው ይገባል (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)። ይህንንም ማድረግ የምንችለው የሥጋን ክፉ መሻት በመካድ (ቍ. 12)፣ የትኛውንም ብልት ለኀጢአት ባሪያ አድርጎ ከማቅረብ በመታቀብ (ቍ. 13)፤ ሰውነታችንንና መላው ማንነታችንን የእግዚአብሔርና የጽድቅ ባሪያ በማድረግ ነው (ቍ. 13-19)።

**6፥15 ኀጢአት እንሥራን?** በጳውሎስ ዘመን በቤተክርስቲያን የነበሩ አንዳንዶች ጸጋ ለኀጢአት ይቅርታን ስለሚያስገኝ፣ ክርስቲያን ኀጢአትን መቃወም የለበትም ብለው ያምኑ ነበር። ሐዋርያው ለዚህ መልስ ሲሰጥ እያንዳንዱ አማኝ ባለማቋረጥ ኀጢአትን ለመቃወምና ክርስቶስን ለመከተል የወሰነውን ውሳኔ ማጽናት እንደሚገባው አሳውቋል (ቍ. 19)። (1) አማኞች ክርስቶስን ከተቀበሉ በኋላ ማንን እንደሚያገለግሉ መምረጥ አለባቸው (ቍ. 16)። (ሀ) ወደ ኀጢአት ሊመለሱ፣ በሕይወታቸው ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ችላ በማለት ዳግም ባሪያ ሊሆኑ እልፍ ተርፎም ሊሞቱ (መንፈሳዊና ዘላለማዊ) ይችላሉ (ቍ. 16፡21፡23)፤ ወይም (ለ) ከኀጢአት ነጻ ሆነው (ቍ. 17) ራሳቸውን የእግዚአብሔርና የጽድቅ ባሪያ አድርገው በማቅረብ መቀደስንና የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ (ቍ. 19፡22)። (2) ከቍ. 15-23 ባለው ክፍል መሠረት ክርስቶስን የሕይወታቸው ጌታ ያላደረጉና የኀጢአትን ኀይል የማይቋቋሙ ክርስቶስ አዳኛቸው እንደሆነ የመመስከር መብት የላቸውም፡ "ማንም ለሁለት ጌታ ሊታዘዝ አይችልም"ና (ማቴ 6፥24፤ ሉቃ 6፥46፤ 2ቆሮ 6፥14—7፥1፤ ያዕ 4፥4፤ 1ዮሐ 2፥15-17)።

እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ፣
ለምትታዘዙት ለእርሱ፣ ይኸውም ወደ
ሞት ለሚወስደው ለኀጢአት ወይም ወደ
ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ ባሮች
እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? [17]ነገር ግን
የኀጢአት ባሮች የነበ ራችሁ ቢሆንም፣
ለተሰጣችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ
የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር
የተመሰገነ ይሁን፤ [18]ከኀጢአት ነጻ
ወጥታችሁ፣ የጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል።
[19]በተፈጥሮ ደካሞች ስለ ሆናችሁ፣ በሰው
ቋንቋ ይህን እላለሁ፤ ብልቶቻችሁን በባርነት
ለርኵሰትና እየባሰ ለሚሄድ ክፋት ታቀ ርቡ
እንደ ነበር፣ አሁን ደግሞ ወደ ቅድስና
ለሚወስደው ጽድቅ ባሪያ አድርጋችሁ
አቅርቡ። [20]የኀጢአት ባሮች ሳላችሁ ከጽድቅ
ነጻ ነበራችሁ። [21]አሁን ከምታፍሩበት ነገር
ያን ጊዜ ምን ጥቅም አገኛችሁ? የዚያ ነገር
ውጤት ሞት ነው። [22]አሁን ግን ከኀጢአት
ነጻ ወጥታችሁ የእግዚአብሔር ባሮች ሆናችኋል፤
የምትሰበስቡትም ፍሬ ወደ ቅድስና
ይመራል፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት
ነው። [23]የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤
የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ
ኢየሱስ[ሀ] የዘላለም ሕይወት ነው።

## የጋብቻ ምሳሌ

**7** ወንድሞች ሆይ፤ ሕግን ለሚያውቁ
ሰዎች እናገራለሁ፤ ሕግ በአንድ
ሰው ላይ ሥልጣን የሚኖረው፣ ሰውየው
በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ መሆኑን
አታውቁምን? [2]እንዲት ያገባች ሴት ከባሏ
ጋር በሕግ የታሰረች የምትሆነው እርሱ
በሕይወት እስካለ ድረስ ነው፤ ባሏ ቢሞት
ግን ከጋብቻ ሕግ ነጻ ትሆናለች። [3]ነገር
ግን ባሏ በሕይወት እያለ ሌላ ሰው ብታገባ
አመንዝራ ትባላለች፤ ባሏ ቢሞት ግን ሌላ
ሰው ብታገባም እንኳ፣ ከዚያ ሕግ ነጻ
ትሆናለች፤ አመንዝራ አትባልም።
[4]ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተም በክር
ስቶስ ኢየሱስ ሥጋ ለሕግ ሞታችኋል፤
ይህም ከሙታን ለተነሣው ለእርሱ፣ ለሌላው
ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ ነው።
[5]ኀጢአተኛ በሆነ ተፈጥሮ[ተ] ቍጥጥር ሥር
ሳለን፣ ለሞት ፍሬ እንድናፈራ በሕግ የተቀ
ሰቀሰው የኀጢአት መሻት በሥጋችን ላይ
ይሠራ ነበር። [6]አሁን ግን ቀድሞ ጠፍሮ
አስሮን ለነበረው ሞተን፣ ከሕግ ነጻ ወጥተ
ናል፤ ይህም አሮጌ በሆነው በተጻፈው ሕግ
ሳይሆን፣ አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ
እንድናገለግል ነው።

## ከኀጢአት ጋር መታገል

[7]እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ በራሱ
ኀጢአት ነውን? በፍጹም አይደለም፤ ነገር

6፥17 ቍ 16፤ ሮሜ1፥8፤ 2ቆሮ2፥14፤ 2ጢሞ1፥13
6፥18 ቍ 2፡7፡22፡ 16፡22፤ ሮሜ8፥2፤ 1ጴጥ4፥1
6፥19 ቍ 13፡22፤ ሮሜ3፥5፤ ገላ3፥15
6፥20 ቍ 16
6፥21 ቍ 23
6፥22 ቍ 18፡19፤ ማቴ25፥46፤ ሮሜ7፥25፤ 1ቆሮ7፥22፤ ኤፌ6፥6፤ 1ጴጥ2፥16
6፥23 ቍ 16፡21፤ ዘፍ2፥17፤ ምሳ10፥16፤ ሕዝ18፥4፤ ማቴ25፥46፤ ሮሜ1፥32፤ 5፥12፤ 7፥5፡13፤ 8፥6፡13፤ ገላ6፥7፡8፤ ያዕ1፥15
7፥1 ሐሥ1፥16፤ 22፥5፤ ሮሜ1፥13፤ 1ቆሮ1፥10፤ 5፥11፤ 6፥6፤ 14፥20፡26፤ ገላ3፥15፤ 6፥18
7፥2 1ቆሮ7፥39
7፥3 ሉቃ16፥18
7፥4 ቍ 6፤ ሮሜ6፥6፤ 8፥2፤ ገላ2፥19፡20፤ ገላ3፥23-25፤ 4፥31፤ 5፥1፤ ቈላ1፥22
7፥5 ሮሜ7፥7-11፤ 6፥13-23፤ ገላ5፥24
7፥6 ቍ 4፤ ሮሜ2፥29፤ 2ቆሮ3፥6
7፥7 ቍ 12፤ ዘፀ20፥17፤ ዘዳ5፥21፤ ሮሜ4፥15፤ 8፥31

[ሀ]6፥23 ወይም *በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል*
[ተ]7፥5 ወይም *በሥጋ፤ እንዲሁም ቍ 25 ይመ*

**6፥16 ወደ ሞት ለሚወስደው ለኃጢአት፤** ከጸጋ በታች ስለሆኑ ያለ ሥጋት ኀጢአትን መሥራት እንደሚችሉ ለሚያስቡ አማኞች ጳውሎስ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ አማኞች ራሳቸውን ለኀጢአት ሲሰጡ በእርግጥ ተመልሰው የኀጢአት ባሪያ ይሆናሉ (ከሉቃ 16፥13፤ ከዮሐ 8፥34 ጋር ያነጻጽሩ)፤ «ሞት»ንም ያስከትልባቸዋል (ቍ 23)፡፡ በዚህ ስፍራ «ሞት» ማለት፥ «ከጌታ ፊትና ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት» (2ተሰ 1፥9) ሲሆን፣ «የዘላለም ሕይወት» (ቍ 23) ተቃራኒ ነው፡፡

**6፥17 ለተሰጣችሁለት ትምህርት ... ስለ ታዘዛችሁ፤** በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ክርስቲያኖች በሐዋርያት መርሖችና አማኙ ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት፣ ለእርሱም ባለው መሰጠት በመመሥረት ለተወሰኑ የትምህርትና የአኗኗር ደንቦች ይታዘዙ ነበር (ከማቴ 5—7 እና ከሐሥ 2፥42 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ (1) እነዚህ ደንቦች አዲስ አማኞች ክርስቶስን ጌታ አድርገው ሲቀበሉ የሚጠብቋቸው አጭር የክርስትና አስተምህሮዎችና የሥነ ምግባር መግለጫዎች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ በጳውሎስ መልእክቶችም፣ «ጤናማ ትምህርት» ወይም «ጤናማ ቃል» ተብለው ተጠርተዋል (1ጢሞ 1፥10፤ 2ጢሞ 1፥13፤ 4፥3፤ ቲቶ 1፥9 እና 2፥1 ይመ)፡፡ (2) ክርስትና ሐሳብንና ልምምድን ለመቈጣጠር የሚያስችል አንድም ዐይነት ወጥ የሆነ ትምህርት የለውም፤ ወይም የሕይወት መመሪያ ደንብ እንዲኖር ማድረግ፤ «ሕግ አክራሪነት» ነው ማለት ጳውሎስ ካስተማረው የክርስትና እምነት ጋር የማይጣጣም ነው፡፡ ክርስትና መንፈሳዊ መለኪያዎችን ማዕከል ባደረገ ሁኔታ ልባዊ ታዛዥነትን ይፈልጋል (ሕግ አክራሪነትን በተመለከተ ማር 7፥6 እና ማብ ይመ)፡፡

**7፥4 ለሕግ ሞታችኋል፤** ወደ ብሉይ ኪዳን ሕግ ተመልሰን ለድነትና በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ለማግኘት ስንል መሥዋዕት አናቀርብም (ከገላ 3፥23-25፤ 4፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 144 ላይ፣ «*የብሉይ ኪዳን ሕግ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ ከብሉይ ኪዳን ሕግ ተለይተን ከክርስቶስ ጋር የተባበርን ሲሆን፤ ለድነታችንም ዋስትና የምናደርገው ክርስቶስን ነው፡፡ በኢየሱስ በማመን (1ዮሐ 5፥13) እንዲሁም መንፈሱንና ጸጋውን በመቀበል (በገጽ 1746 ላይ፣ «*እምነትና ጸጋ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ይቅርታን እናገኛለን፤ ከዚያም ዳግም መወለድና ለእግዚአብሔር ፍሬ ማፍራት እንችላለን (6፥22-23፤ 8፥3-4፤ ማቴ 5፥17 እና ማብ ይመ፤ ኤፌ 2፥10፤ ገላ 5፥22-23፤ ቈላ 1፥5-6)፡፡

**7፥7 በሕግ በኩል ባይሆን ኖሮ፣ ኀጢአት ምን እንደ ሆነ ባላወቅሁም ነበር፤** ይህ ክፍል (ቍ 7-25) ጳውሎስም ሆነ ሌላ ሰው ከመለወጡ በፊት በጸጋው፣ በምሕረቱና በብርታቱ ላይ ሳይደገፍ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚያደርገውን ሙከራ ይገልጻል (8፥5 እና በገጽ 1746 ላይ፣ «*እምነትና ጸጋ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ (1) በቍ 7-12 ላይ ጳውሎስ ሰው በኀላፊነት መጠየቅ የሚችልበትን ዕድሜ እስከሚደርስ ድረስ ያለውን የአለማወቅ ደረጃ ይገልጻል፡፡ በቍ 9 መሠረት «ሕያው» ናቸው፤ ይህም ማለት በውጭ ወይም በልባቸው ላይ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ሕግ ሆን

ግን በሕግ በኩል ባይሆን ኖሮ፣ ኀጢአት
ምን እንደ ሆነ ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ
"አትመኝ" ባይል ኖሮ፣ ምኞት ምን እንደ
ሆነ በርግጥ አላውቅም ነበር። [8]ኀጢአት ግን
ትእዛዙ ባስገኘው ዕድል ተጠቅሞ በእኔ
ውስጥ ማንኛውንም ዐይነት አጕል ምኞት
አስነሣ፤ ኀጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና።
[9]ሕጉ ሳይኖር ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ ከመጣ
በኋላ ግን፣ ኀጢአት ሕያው ሆነ፤ እኔም
ሞትሁ። [10]ለሕይወት እንዲሆን የታሰበው
ያ ትእዛዝም ሞትን እንዳመጣ ተገነዘብሁ፤
[11]ኀጢአት በትእዛዝ በኩል የተገኘውን
ዕድል በመጠቀም አታለለኝ፤ በትእዛዝም
ገደለኝ። [12]ስለዚህ ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤
ትእዛዙም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው።
[13]ታዲያ በጎ የሆነው ነገር ሞት ሆነብኝን?
ከቶ አይደለም፤ ነገር ግን ኀጢአት በኀጢአ
ትነቱ ይታወቅ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር በኩል
ሞትን አመጣብኝ፤ ይኸውም ኀጢአት
በትእዛዝ በኩል ይብሱን ኀጢአት ይሆን
ዘንድ ነው።
[14]ሕጉ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለን፤

7፥8 ቍ11፤ ሮሜ4፥15
7፥10 ዘሌ18፥5፤ ሉቃ10፥26-28፤ ሮሜ10፥5፤ ገላ3፥12
7፥11 ቍ8፤ ዘፍ3፥13
7፥12 ቍ7፥13፥14፥16፤ ሮሜ4፥15፤ 8፥4፤ ገላ3፥21፤ 1ጢሞ1፥8
7፥13 ቍ12፤ ሮሜ6፥23
7፥14 1ነገ21፥20፥25፤ 2ነገ17፥17፤ ሮሜ6፥16፤ 1ቆሮ3፥1

በሰው እስከተሳሰታበት ጊዜ ድረስ ከወቀሳና ከመንፈሳዊ ተጠያቂነት ነጻ የነበሩትን ሕይወት ማለት ነው (ከ2፥14-15፣ ከ7፥7፡9፡11 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ከቍ 13-20 ባለው ክፍል ደግሞ ኀጢአት መሆኑ ሳይታሰብ የተፈጸመ ነገር ሕጉ ሲታወቅ ኀጢአት እንደ ሆነ ስለሚገለጥና ሰዎችንም በደለኞች ስለሚያደርግ ጳውሎስ በኀጢአት ባርነት ሥር የመሆን ሁኔታን ያመለክታል። ሰዎች ኀጢአትን ለመቋቋም ጥረት ቢያደርጉም እንኳ ኀጢአት የበላይ ገዥያቸው ይሆናል።

(3) በቍ 21-25 ላይ ሰዎች የኀጢአትን ምንነትና ኀይል ባወቁ ቍጥር የቱን ያህል ከተስፋቢስነት ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ ጳውሎስ ያሳያል።

**7፥9 ሕያው ነበርሁ፤** "ሕያው ነበርሁ" እና "ኀጢአት ... ገደለኝ" (ቍ 11) የሚሉት የጳውሎስ ገለጻዎች አንድ ሕፃን ልጅ ነፍስ ዐውቆ የእግዚአብሔርን ሕግ እስካልተላለፈ ድረስ ጥፋተኛ አይደለም የሚለውን አመለካከት ይደግፋሉ (2፥14-15፡ ያለፈውን ማብ ይመ)። ሕፃናት ወደዚህ ዓለም ሲመጡ የውርስ ኀጢአት ይዘው የሚወለዱ የዘላለም ኵነኔ ይገባቸዋል የሚለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም።

**7፥12 ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤** ማቴ 5፥17 እና ማብራሪያውን፤ ገላ 3፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**7፥14 ሕጉ፤** ጳውሎስ በምዕ 7 ላይ የሚናገረው ምናልባት በብሉይ ኪዳን ሥር ሆኖ እውነትን በመቀበል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖር ዐቅም ያጣን ዳግም ያልተወለደን ሰው፣ ወይም ዳግም ልደትን አግኝቶ በቅድስና ለመኖር ዐቅም ያጣን ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ ጽድቅን፣ በጎነትንና ቅድስናን በግል ጥረታችን አግኝተን ኀጢአትን መቃወምና የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ እንደማንችል በማሳየት ከኀጢአት ኀይል ጋር ለብቻው የሚታገል ሰው ያለበትን ከፍተኛ ችግር ይገልጻል። በሌላም በኩል ዳግም ልደትን ያላገኘ ሰው በቃሉ ላይ የተገለጸውን ቅድስናን በመሻት ረገድ ከፍተኛ ትግል አይኖርበትም። ክርስቲያን ግን ያለበት ትግል እጅግ ከፍተኛ ነው። ይህም ከክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ያለው ክርስቲያን ከኀጢአት ኀይል ጋር የሚያደርገው ትግል ነው (ከገላ 5፥16-18 ጋር ያነጻጽሩ)። በምዕ 8 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ በመመላለስ በኀጢአት ላይ ድልን እንዴት መቀዳጀት እንደሚቻል ገልጸአል።

**7፥14 ለኀጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ ሥጋዊ ነኝ፤** አንዳንዶች በምዕ 7 ላይ ካሉት ቃላት ሁሉ ይህ ሐረግ ከሕግ በታች ከዳግም ልደት በፊት ስላለ ሰው ይናገራል ይላሉ። ይህ የሆነበትን ምክንያት ሲገልጹ፦(1) ጳውሎስ ምዕ 7 ላይ ሕግ ከጸጋ ሙሉ ሊያድነን በቂ አይደለም የሚለውን ሐሳብ ይገልጻል እንጂ የጸጋው ወንጌል ሊያድነን በቂ አይደለም አላለም (ከገላ 3፥24 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) በቍ 5 ላይ ጳውሎስ "ኀጢአተኛ በሆነ ተፈጥሮ ቍጥጥር ሥር" ያሉ ሲል፥ መንፈሳዊያን ያልሆኑ ሥጋውያንን ነው፤ እነዚህም "ለሞት ፍሬ" ማለትም ለዘላለም ሞት ፍሬ እንደሚያፈሩ ይናገራል። በ8፥13 ላይ ደግሞ "እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁና" በማለት ይገልጻል (ከገላ 5፥19-21 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ በምዕ7 ላይ የተጠቀሰው ሰው በመንፈስ የሞተ ሰው ነው ማለት ነው።

(3) "ለኀጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ" የሚለው አባባል በኀጢአት ኀይል ቍጥጥር ሥር መውደቅ ማለት ነው (ከ1ነገ 21፥20፡25፣ 2ነገ 17፥17 ጋር ያነጻጽ። ክርስቶስ ደሙን ቤዛ አድርጎ (ማቴ 20፥28 እና ማብ ይመ) ከኀጢአት ኀይል በማዳን ኀጢአት በእኛ ላይ እንዳይሠለጥን ስላደረገ (6፥14)፣ ከላይ የተጠቀሰው ሐረግ በክርስቶስ ያመነውን ሰው አያመለክትም። ክርስቶስ ራሱ እንዲህ ብሎአል፥ "ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ" (ዮሐ 8፥36 እና ማብ ይመ፤ ከሮሜ 8፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። በእርግጥም ኢየሱስ የሚለው ስም "እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና" ማለት ነው (ማቴ 1፥21)።

(4) በአማኞች ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ (ምዕ 8) "ለኀጢአት እንደ ባሪያ" እንዲሸጡ አይተዋቸውም። ጳውሎስ በመቀጠልም "የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢአት ... ሕግ ነጻ አውጥቶኛል" (8፥2) ብሎአል፤ በመቀጠል፣ "በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በምንመላለስ በእኛ" (8፥4) ሲልም ራሱን በመጨመር ነው። ይህም "ግዴታ አለብን፤ ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንድንኖር ለሥጋ አይደለም" (8፥12) የሚለውን ለማስገንዘብ ነው።

በሌላ በኩል ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕ 7 ላይ የተለጸው ዳግም ልደትን አግኝቶ በቅድስና ለመኖር ዐቅም ያጣን ክርስቲያን ነው የሚሉት፣ ከላይ የተሰጡትን ሐሳቦች አይቀበሉም፤ ለሐሳባቸው ድጋፍ የሚያቀርቡት ምክንያት፦ (1) በምዕ 7 ላይ ያለው ምንባብ ሙሉ በሙሉ የተጠቀሰው በአሁን ጊዜያት ግስ ነው።

(2) ሐዋርያው ጳውሎስ በትሕትና ስለ ራሱ ያቀረበው ሐሳብ (ቍ 18) የሚያመለክተው ዳግም የተወለደን ክርስቲያን ነው።

(3) ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሕግ የሚሰጠው ከፍተኛ ግምት (ቍ 14:16) የክርስቲያንን የሕይወት ልምምድ የሚያመለክት ነው።

(4) በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ ይህን ምንባብ የያዘው ክፍል ጳውሎስ መቀደስ ማለትም ክርስቲያን በሕይወቱ ወደ ቅድስና የሚያድግበትን ልምምድ የሚያስተምርበት ነው፤ ይህ ከሆነም ዳግም የተወለደን ክርስቲያን የሕይወት እድገት ሂደት የሚያመለክት ነው።

እኔ ግን ለኀጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ
ሥጋዊ ነኝ። 15የማደርገውን አላውቅም፤ ለማ
ድረግ የምፈልገውን አላደርግም፤ ነገር ግን
የምጠላውን ያን አደርጋለሁና። 16ማድረግ
የማልፈልገውን የማደርግ ከሆንኩ፣ ሕጉ በጎ
እንደ ሆነ እመሰክራለሁ፤ 17እንዲህ ከሆነ፣
ይህን የማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን፣ በእኔ
ውስጥ የሚኖረው ኀጢአት ነው። 18በእኔ፣
ማለትም ኀጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ
ውስጥ ምንም በጎ ነገር እንደማይኖር
ዐውቃለሁ፤ በጎ የሆ ነውን የማድረግ ምኞት
አለኝ፤ ነገር ግን ልፈጽ መው አልችልም።
19የማደርገው ላደርገው የምፈልገውን በጎ
ነገር አይደለም፤ ዳሩ ግን ለማድ ረግ
የማልፈልገውን ክፉ ነገር ነው። 20ላደር ገው
የማልፈልገውን ነገር የማደርገው ከሆነ፣ ያን
የማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን፣ የሚያደርገው
በእኔ ውስጥ የሚኖረው ኀጢአት ነው።
21ስለዚህ ይህ ሕግ እየሠራ እንደ ሆነ ተረ
ድቻለሁ፤ ይኸውም በጎ ነገር ለመሥራት
ስፈልግ፣ ክፉት ከእኔ ጋር አለ። 22በውስጤ
በእግዚአብሔር ሕግ ሐሤት አደርጋለሁ፤
23ነገር ግን በብልቶቼ ውስጥ ለሚሠራው
የኀጢአት ሕግ እኔን እስረኛ በማድረግ፣
ከአ እምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋ ሌላ ሕግ
በብልቶቼ ውስጥ ሲሠራ አያለሁ። 24እኔ
ምን ዐይነት ጐስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ ለሞት

7፥15 ቍ 19፤ ገላ5፥17
7፥16 ቍ 12
7፥17 ቍ 20
7፥18 ቍ 25፤ ገላ5፥24
7፥19 ቍ 15
7፥20 ቍ 17
7፥21 ቍ 23፡25
7፥22 መዝ1፥2፤ 40፥8፤ ኤፌ3፥16
7፥23 ሮሜ6፥16፤ ገላ5፥17፤ 1ጴጥ2፥11፤ ያዕ4፥1
7፥24 ሮሜ6፥6፤ 8፥2
7፥25 ሮሜ6፥16፡22፤ 2ቆሮ2፥14
8፥1 ቍ 34፡39፤ ሮሜ16፥3
8፥2 ዮሐ8፥32፡36፤ ሮሜ6፥16፡18፤ 7፥25፤ 1ቆሮ15፥45፤ 7፥4
8፥3 ሮሜ7፥18፡19፤ ፊል2፥7፤ ገላ5፥24፤ ዕብ2፥14፡17፤ 7፥18፤ 10፥1-4
8፥4 ሮሜ2፥26፤ ገላ5፥16

ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል?
25በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን።
እንግዲያስ እኔ ራሴ በአእምሮዬ
ለእግዚአብሔር ሕግ ባሪያ ስሆን፣ በኀጢአተኛ
ተፈጥሮዬ ግን ለኀጢአት ሕግ ባሪያ ነኝ።

## ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ

8 ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ* ያሉት
አሁን ኵነኔ የለባቸውም፤ 2ምክንያቱም
የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ
ኢየሱስ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ
አውጥቶአችኋል።* 3ሕግ ከሥጋ ባሕርይ*
የተነሣ ደክሞ ሊፈጽም ያልቻለውን፣
እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኀጢአተኛ ሰው
አምሳል፣ የኀጢአት መሥዋዕት* እንዲሆን
በመላክ ፈጸመው፤ በዚህም ኀጢአትን በሥጋ
ኰነነ፤ 4ይኸውም በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ

*7፥18 ወይም ሥጋዬ
*8፥1 አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ቅጆች ስለዚህ እንደ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ በኖረው በክርስቶስ ኢየሱስ ይላሉ።
*8፥3 ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮ፤ እንዲሁም ቍ 4፡5፡8፡9፡12፡13 ይመ
*8፥3 ወይም ስለ ኀጢአት መሥዋዕት
*8፥3 ወይም በኀጢአተኛ ሰው
*አንዳንድ የጥንት ቅጆች ኋአውጥቶኛልቃ ይላሉ።

**7፥15 ለማድረግ የምፈልገውን አላደርግም፤** የማያድነው የክርስቶስ ጸጋ ሳይኖራቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመፈጸም የሚሞክሩ፣ የልባቸውን መልካም ፈቃድ ለማድረግ ዐቅም ያንሳቸዋል። ኀጢአትና ክፋት በውስጣቸው ሆነው ይገዙአቸዋል እንጂ የራሳቸው ገዢዎች አይደሉም፤ የኀጢአት ባሮች (ቍ 15-21) እና «የኀጢአት ሕግ እስረኛ» (ቍ 23) ናቸው። እንዲሁም ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ቍጥጥር ሥር ካልሆኑ በቀር ከዚህ ውጭ አይሆኑም። በክርስቶስ በኩል በፈተና ውስጥ መውጫ መንገዱን አዘጋጅቶ መቆም የሚያስችል እግዚአብሔር ብቻ ነው (1ቆሮ 10፥13)።

**7፥22 በእግዚአብሔር ሕግ ሐሤት አደርጋለሁ፤** በብሉይ ኪዳን ሕግ ሥር ያሉ ብዙዎች በውስጣቸው (በነፍስ፣ በሕሊና) በእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዛት ደስ ይሰኛሉ (ከመዝ 119፤ ከኢሳ 58፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። ይሁን እንጂ መልስ ብለው ድጋፍን ከሕግ ብቻ ሲፈልጉ፣ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ይቈጣጠራቸው ነበር (ቍ 23)። እንደዚሁም ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ጽድቅ፣ ንጽሕናና ልቀት ዐውቀው በክርስቶስ የሚገኘውን የዳግም ልደት ጸጋ በእውነት ስላልተላማመዱ በኀጢአት እስራት ሥሩ ይገኛሉ። ከኀጢአት እስራትና ክርክሱት ነጻ የሆነ ሕይወት ለማግኘት በእውነት ዳግም ካልተወለድን፣ ንስሓ በመግባት በመንፈስ ቅዱስ የታደሰ ሕይወት ካልኖረን በቀር ጥረታችን ሁሉ ከንቱ ይሆናል (ዮሐ 3፥3፤ ሮሜ 8፤ 2ቆሮ 5፥17)።

**7፥24 እኔ ምን ዓይነት ጎስቋላ ሰው ነኝ፤** ዳግም ያልተወለደ ሰው ከኀጢአት ጋር የሚያደርገው ግብ ግብ ከንቱና ዞሮ ዞሮ ለኀጢአት ባሪያ መሆን ነው (ቍ 14፡23)፤ ዳግም የተወለደም ሰው ኀጢአት የማድረግ ልማዱን ቢቀጥል ተመልሶ የኀጢአት ባሪያ ይሆናል። ያለ እግዚአብሔር መንፈስ የሚደረግ ትግል ሁሉ ውጤቱ ኪሳራ ነው። በዚህ ዐይነት ሁኔታ ያለ ሰው ምንኛ አሳዛኝ ነው? እንዴትስ ይድናል? የሚድነው «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል» (ቍ 25)፤ «ከኀጢአትና ከሞት ሕግ» ነጻ የሚያወጣን እርሱ ብቻ ነውና።

**8፥1 በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት፤** ጳውሎስ ከክርስቶስ ውጪ ያለ ሕይወት ሽንፈትና መከራ ያለበት እንደ ሆነ ሲያመለክት ለኀጢአት ባርነትም የተሰጠ እንደ ሆነ ያሳያል። ምዕ 8 ላይ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ከኵነኔ ነጻ መውጣት፣ በኀጢአት ላይ ድል ማግኘትና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ እውን የሚሆነው በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከክርስቶስ ጋር አንድነት ሲኖረን እንደሆነ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስን በመቀበልና በመከተል ከኀጢአት ኀይል ነጻ የወጣን ሲሆን፣ በክርስቶስ ወደ ሚገኘው የመጨረሻው ክብርም እየመራን ነው፤ ይህም ልምምድ በወንጌል ትምህርት መሠረት የምንኖረው ትክክለኛው የክርስትና ሕይወት ነው።

**8፥2 የሕይወት መንፈስ ሕግ፤** ይህ «የሕይወት መንፈስ ሕግ» በአማኞች ልብ ውስጥ የሚንቀሳቀስና በትክክል የማስኬድን ተግባር የሚፈጽመው የመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ከእርሱ የሚገኘው ሕይወት ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ኀጢአተኞች ሕይወት በመምጣት ከኀጢአት ኀይል ነጻ ያወጣቸዋል (ከ7፥23 ጋር ያነጽሩ)። የሕይወት መንፈስ ሕግ ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ የሚሆነው አማኞች መንፈስ ቅዱስን ለመታዘዝ ራሳቸውን ሲሰጡ ነው (ቍ 4-5፡13-14)። ይህን ካደረጉም ኀጢአትን ማሸነፍ እንዲችሉ የሚረዳቸውን አዲስ ኀይል በውስጣቸው ሲሠራ ያገኙታል። «የኀጢአትና የሞት ሕግ» ሰዎችን ባርነት ውስጥ በማስገባት (7፥14) ወደ ተስፋቢስነት የሚያወርዳቸው (7፥24) የኀጢአት የመግዛት ኀይል ነው።

**8፥4 በእኛ ሕጉ የሚጠይቀው ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጸም፤** በአማኞች ውስጥ

በምንመላለስ በእኛ፣ ሕጉ የሚጠይቀው
ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጸም ነው።
5እንደ ሥጋ የሚኖሩ ልባቸውን በሥጋ
ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ፤ እንደ መንፈስ*
የሚኖሩ ግን ልባቸውን በመንፈስ ፍላጎት
ላይ ያደርጋሉ። 6የሥጋን ነገር ማሰብ[ፐ] ሞት
ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና
ሰላም ነው። 7ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ[^]
ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር
ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም።
8በሥጋ የሚመሩትም እግዚአብሔርን ማስደሰት
አይችሉም።
9እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ
በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን
በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ
ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም።
10ነገር ግን ክርስቶስ በውስጣችሁ ካለ፣
ሰውነታችሁ ከኀጢአት የተነሣ የሞተ

8፥5 ገላ5፥19-21፥22-25
8፥6 ቍ13፤ ሮሜ6፥23፤ ገላ6፥8
8፥7 ያዕ4፥4
8፥8 ገላ5፥24
8፥9 ቍ11፤ ዮሐ14፥17፤ ሐሥ16፥7፤ 1ቆሮ6፥19፤ ገላ5፥24፤ 2ጢሞ1፥14፤ 1ዮሐ4፥13
8፥10 ቍ9፤ ዘፀ29፥45፤ ዮሐ14፥20፥23፤ 2ቆሮ13፥5፤ ገላ2፥20፤ ኤፌ3፥17፤ ቆላ1፥27፤ ራእ3፥20

ቢሆንም፣ መንፈሳችሁ ከጽድቅ የተነሣ
ሕያው ነው። 11ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው
የእርሱ መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ፣
ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው፣ በውስጣችሁ
በሚኖረው በመንፈሱ ሟች ለሆነው
ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል።
12ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ግዴታ
አለብን፤ ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ
እንድንኖር ለሥጋ አይደለም። 13እንደ ሥጋ
ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ክፉ የሆነውን
የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ ግን፣
በሕይወት ትኖራላችሁ፤ 14በእግዚአብሔር

8፥11 ዮሐ5፥21፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ6፥5 8፥12 ቍ4፤ ገላ5፥24 8፥13 ቍ6፤ ሮሜ6፥23፤ 6፥2፤ ገላ6፥8
8፥14 ቍ19፤ ሆሴ1፥10፤ ሚል3፥17፤ ማቴ5፥9፤ ዮሐ1፥12፤ ገላ5፥18፤ ገላ3፥26፤ 4፥5፤ ኤፌ1፥5፤ ራእ21፥7

[ፐ]8፥6 ወይም ስለ ሥጋ ማሰብ
[^]8፥7 ወይም ስለ ሥጋ የሚያስብ አእምሮ

የሚመራው መንፈስ ቅዱስ የጽድቅን ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችላቸው ሲሆን፣ በዚህም የእግዚአብሔር ግብረገባዊ ሕግ እንደ ተፈጸመ ይታያል። ስለዚህ የጸጋ ሥራና ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ እርስ በርስ አይቃረኑም (ከ2፥13፤ 3፥31፥ 6፥15፤ 7፥12፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። ሁለቱም ጽድቅንና ቅድስናን ያመለክታሉ።

**8፥5 እንደ ሥጋ ፈቃድ … መንፈስ፤** ጳውሎስ ከ5-14 ባሉት ቍጥሮች ሁለት ዐይነት ሰዎችን ይገልጻል፤ እነርሱም እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ናቸው። (1) "እንደ ሥጋ ፈቃድ" መኖር ማለት መመኘት፣ ደስታን ለማግኘት መሯሯጥ፣ ኀጢአተኛ ተፈጥሮን ለማርካት መጠመድና መማሰን ማለት ነው። እንዲህ ያለው ሕይወት የሚይዘው ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነ የወሲብ ግንኙነትን፣ ምንዝርናን፣ ጥላቻን፣ በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ የእድገት ምኞትን፣ የቍጣን ግንፍላና የመሳሰሉትን ብቻ ሳይሆን (ገላ 9፥19-20)፣ ስድ የወሲብ ቋንቋን ለመስማት መጓጓትን፣ ወሲባዊ ግንኙነትን የሚያሳይ ስዕል የማየት ልክፍትን፣ ሱስ በሚያሲዝ ዕፅ መጠመድን፣ በድራማ፣ በመጻሕፍት፥ በቴሌቭዥን ወይም በፊልምና በመሳሰሉት በሚታዩ የወሲብ ትእይንቶች፣ በአእምሮም ሆነ በስሜት መርካትንም ጭምር ነው (በገጽ 1853 ላይ፥ "*የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) "እንደ መንፈስ ፈቃድ" መኖር ማለት የመንፈስ ቅዱስን ምሪትና እርዳታ መፈለግና ለእርሱም መገዛት እንዲሁም ሐሳብን በእግዚአብሔር ነገር ላይ ማሳረፍ ማለት ነው (በገጽ 1853 ላይ፣ "*የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ እንዲሁም በእኛ ውስጥና በእኛ በኩል ፈቃዱን ለመፈጸም ርዳታውንና ጸጋውን እንዲሰጠን በመታመን በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ በማስተዋል መኖር ማለት ነው።

(3) የሥጋ ፈቃድንና የመንፈስ ፈቃድን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ አይቻልም (ቍ 7-8፤ ገላ 5፥17-18)። ማንም ሰው በመንፈስ ቅዱስ የኀጢአትን መሻት መቋቋም ሲሳነውና እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ሲጀምር (ቍ 13) የእግዚአብሔር ጠላት ከመሆኑም በላይ (ቍ 7፤ ያዕ 4፥4) ዕጣ ፈንታውም መንፈሳዊና የዘላለም ሞት ነው (ቍ 13)። የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር የሚወዱና ለዚሁ ቅድሚያ የሚሰጡ የዘላለም ሕይወትን ያገኛሉ፤ ከእግዚአብሔር ጋርም ኅብረት ይኖራቸዋል (ቍ 10-11፥15-16)።

**8፥9 የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፤** ሁሉም አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ያድራል (ከ1ቆሮ 3፥16፤ 6፥19-20፤ ከኤፌ 1፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ፥ በገጽ 1679 ላይ፣ "*የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**8፥10 ሰውነታችሁ ከኀጢአት የተነሣ ምውት ሲሆን፤** ኀጢአት ሰውነታችንን ስላበላሸው፣ የተበላሸው ሰውነታችን መሞት ወይም መለወጥ አለበት (ከ1ቆሮ 15፥50-54፤ ከ1ተሰ 4፥13-17 ጋር ያነጻጽሩ)። ይሁን እንጂ ክርስቶስ በውስጣችን ስላለ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወት ከአሁኑ እንለማመዳለን።

**8፥13 ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ፤** ኀጢአት ሁልጊዜ የራሱ ሊያደርገን ስለሚፈልግ፣ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ሥራ ሊገድብ ከሚችል ነገር ሁሉ ጋር ያለማቋረጥ መጋደል እንደሚገባ ጳውሎስ አሳስቧል (ከ6፥11-19 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) ይህ መንፈሳዊ መጋደል በሰይጣንና በክፉ መንፈሳውያን ሰራዊት ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም (ኤፌ 6፥12) ዋነኛ ዐላማው የኀጢአተኛ ተፈጥሮን ስሜትና ፍላጎት መቃወም ነው (ገላ 5፥16-21፤ ያዕ 4፥1፤ 1ጴጥ 2፥11)። አማኞች እንደ መሆናችን መጠን ሁልጊዜ ለኀጢአተኛ መሻታችን ነው ወይስ ተለይተን ለምንሆንበት መለኮታዊ ማንነት ነው የምንታዘዘው በማለት መጠየቅ አለብን (ገላ 5፥16፥18፤ 2ጴጥ 1፥4)።

(2) ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ መግደል ያለመቻል መንፈሳዊ ሞት (ቍ 6፥13) እና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ርስትን ማጣት ሊያስከትል ይችላል (ገላ 5፥19-21)። "ትሞታላችሁና" የሚለው ቃል አንድ ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ሕይወት ወደ መንፈሳዊ ሞት ሊሄድ እንደሚችል ያመለክታል። ስለዚህም በአዲስ ልደት የምንቀበለው የእግዚአብሔር ሕይወት (ዮሐ 3፥3-6) ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ለመግደል ከማይፈልግ አማኝ ነፍስ ውስጥ እየታጣ ሊሄድ ይችላል።

**8፥14 እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤** በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የድነትን ዋስትና መሠረት ያመለክታል። አንድ ሰው ክፉውን የሥጋ ሥራ ባለማቋረጥ የሚገድል

መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር
ልጆች ናቸውና። 15እንደ ገና የፍርሀት ባሪያ
የሚያደርጋችሁን መንፈስ ሳይሆን፣ "አባ[ሀ]፣
አባት" ብለን የምንጠራበትን የልጅነት[ለ]
መንፈስ ተቀብላችኋልና፤ 16የእግዚአብሔር
ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ
ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል።
17ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ
ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በርግጥ የመከራው
ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣
ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።

### የሚመጣው ክብር

18የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገ
ለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር
ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ።
19ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ
በናፍቆት ይጠባበቃል። 20ፍጥረት ሁሉ ለከ
ንቱነት ተዳርጎአል፤ ይኸውም በራሱ ምርጫ
ሳይሆን፣ ለተስፋ እንዲገዛ ካደረገው ከፈቃዱ
የተነሣ ነው።[መ] 21ይህም ፍጥረት ራሱ ከመ
በስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ
ሆነው ወደ ከበረው ነጻነት እንዲደርስ ነው።
22እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ
ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እን
ደሚገኝ እናውቃለን። 23እርሱ ብቻ ሳይሆን፣
የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን
እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን
ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን

8፥15 ማር14፥36፤ ዮሐ20፥22፤ ገላ4፥5፡6፤ 2ጢሞ1፥7
8፥16 ቍ14፤ ዮሐ1፥12፤ 2ቆሮ1፥22፤ ኤፌ1፥13
8፥17 ሐሥ20፥32፤ 2ቆሮ1፥5፤ ገላ3፥29፤ 4፥7፤ ኤፌ3፥6፤ ቲቶ3፥7፤ 2ጢሞ2፥12፤ 1ጴጥ4፥13
8፥18 2ቆሮ4፥17፤ 1ጴጥ4፥13፤ 5፥1
8፥19 ቍ14
8፥20 ዘፍ3፥17-19፤ 5፥29
8፥21 ዮሐ1፥12፤ ሐሥ3፥21፤
8፥21 2ጴጥ3፥13፤ ራእ21፥1 8፥22 ኤር12፥4
8፥23 ቍ11፤ 19፤ 2ቆሮ5፥2፡4፡5፤ ገላ5፥5፤ ፊል3፥21

*[ሀ]8፥15 በአራማይክ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ስም ነው*
*[ለ]8፥15 ወይም እንደ ልጅ*
*[መ]8፥20፡21 ወይም በተስፋ አስገዝቶታል።*

ከሆነ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ነው ማለት ነው። በመንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።

**8፥14 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ፤** አማኝ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲያስብ፣ እንዲናገርና እንዲኖር መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያድራል። (1) በመሠረቱ ምሪቱ አማኝን የሚያነሣሣ ነው፤ ይኸውም (ሀ) የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲደረግና ክፋው የሥጋ ሥራ ይሞት ዘንድ ውስጣዊ ማነሣሣት (ቍ 13፤ ፊል 2፥13፤ ቲቶ 2፥11-12)፣ (ለ) ምንጊዜም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ (1ቆሮ 2፥12-13 ይመ፤ ከ2ጴጥ 1፥20-21 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (ሐ) የሕይወትን አቅጣጫ በማሳየት ረገድ የታቀደ (ሉቃ 4፥1፤ ሐሥ 10፥19-20፤ 16፥6-7)፥ (መ) ኀጢአት የሞላበትን መሻት የሚቃወም (ገላ 5፥17-18፤ 1ጴጥ 2፥11)፥ (ሠ) ስለ በደል ወቀሳን የሚያቀርብ፣ ስለ ክርስቶስ የጽድቅ መለኪያና እግዚአብሔር ክፋውን እንደሚቀጣ የሚያስብ (ዮሐ 16፥8-11)፣ (ረ) አማኞች በእምነት እንዲጸኑ የሚመክርና ክርስቶስን ከማመን ውጪ እንዳይሆኑ የሚያስጠነቅቅ (ቍ 13፤ ዕብ 3፥7-14)፣ (ሰ) አማኞች ለመንፈስ ቅዱስ ማነሣሣት እንቢተኞች በመሆን ሲቀጥሉ ትቶአቸው እንደሚሄድ በማሳየት (1፥28፤ ኤፌ 4፥17-19፡30-31፤ 1ተሰ 5፥19)፣ (ሸ) ሲተዉት መንፈሳዊ ሞትን በማስከተል (ቍ 6፡13)፥ እና (ቀ) ሲታዘዙት መንፈሳዊ ሕይወትንና ሰላምን በመስጠት (ቍ 6፡10-11፡13፤ ገላ 5፥22-23) ነው።

(2) የመንፈስ ቅዱስ ማነሣሣት የሚመጣው በሚከተሉት መንገዶች ነው፤ (ሀ) የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ (ዮሐ 14፥26፤ 15፥7፡26፤ 16፥13፤ 2ጢሞ 3፥16-17)፥ (ለ) በትጋት በመጸለይ (ቍ 26፤ ሐሥ 13፥2-3)፤ (ሐ) መንፈሳዊ ስብከትና ትምህርት በመከታተል (2ጢሞ 4፥1-2፤ ዕብ 13፥7፡17)፥ (መ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መገለጥ በመለማመድ (1ቆሮ 12፥7-10 እና 14፥6 ይመ)፥ (ሠ) የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና የታመኑ መንፈሳዊ መሪዎችን ምክር በመስማት (ኤፌ 6፥1፤ ቈላ 3፥20)።

**8፥15 አባ፣ አባት፤** ገላ 4፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**8፥16 መንፈስ ራሱ ... ይመሰክርልናል፤** መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ በኩል አሁን ከክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን መተማመማኛን ይሰጠናል (ቍ 15)፤ እንዲሁም ክርስቶስ እንደወደደን፣ አሁንም እንደሚወደን በሰማይም መካከለኛ ሆኖልን እንደሚኖር ያስረግጥልናል (ከዕብ 7፥25 ጋር ያነጻጽሩ)። አብ አንድያ ልጁን ከወደደበት ፍቅር ባላነሰ ሁኔታ እኛንም እንደ ልጆቹ ተቀብሎ የወደደን መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ያመለክተናል (ዮሐ 14፥21፡23፤ 17፥23)። በመጨረሻም፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን "አባ፣ አባት" ብለን የምንጮኽበትን ፍቅርና ድፍረት ይፈጥራል (ቍ 15)።

**8፥17 የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፤** ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ የምናገኘው የአሸናፊነት ሕይወት ቀላል እንዳይደለ ያሳስበናል። ኢየሱስ መከራን ተቀበለ፤ እኛም ተከታዮቹ መከራን እንቀበላለን። ይህ መከራ የእርሱን መከራ መካፈላችንን የሚያመለክት ሲሆን (ከ2ቆሮ 1፥5፤ ከፊል 3፥10፤ ከቈላ 1፥24፤ ከ2ጢሞ 2፥11-12)፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ልጆች ኅብረት ለመፍጠር፣ ከክርስቶስ ጋር ለመመሳሰል፣ ለእርሱ ለመመስከርና ዓለምን ላለመምሰል የመወሰናችን ውጤት ነው (ከ12፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)።

**8፥18 የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን፤** ሕመምን፣ በሽታን፣ ኀላቀልናን፣ ተስፋ መቍረጥን፣ ድኽነትን፣ መገፋትን፣ ሐዘንን፣ ስደትንና ሌሎቹንም የሚያስከትተው የአሁኑ ዘመን መከራ በሙሉ ሊመጣ ባለው ዘመን ለታመኑ ክርስቲያኖች ሊሰጥ ካለው በረከት፣ ርስትና ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም ማለት አይደለም (ከ2ቆሮ 4፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

**8፥22 ፍጥረት ሁሉ ... በመቃተት ላይ እንደሚገኝ፤** ጳውሎስ በቍ 22-27 ላይ ስለ ሦስት ዐይነት መቃተት ይናገራል፤ ይህም የፍጥረት (ቍ 22)፥ የአማኞች (ቍ 23) እና የመንፈስ ቅዱስ (ቍ 26) ነው። "ፍጥረት" ይኸውም ሕይወት ያለውና የሌለው ሁሉ ከሰው ኀጢአት የተነሣ ለመከራና ለጥፋት አልፎ ተሰጥቷል (ቍ 20)። ስለዚህ እግዚአብሔር ተፈጥሮን ይታደግና ዳግም ይፈጥር ዘንድ ዐቅዶአል። የእግዚአብሔር ታማኝ ልጆች ሙሉ ርስታቸውን በሚቀበሉበት ጊዜ (ቍ 14፡23) ሁሉም ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚታደስበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይኖራል (ከ2ቆሮ 5፥17፤ ገላ 6፥15፤ ራእ 21፥1፡5 ያነጻጽሩ)።

**8፥23 እኛ ራሳችን ... እንቃትታለን፤** አማኞች መንፈስ ቅዱስንና በረከቱን የተቀበሉ ቢሆንም ሙሉ የሆነውን መዋጀት እየተጠባበቁ አሁንም በመቃተት ላይ ይገኛሉ። ይህ መቃተት ሁለት ምክንያቶች አሉት፤

በውስጣችን እንቃትታለን። 24በዚህ ተስፋ
ድነናል፤ ተስፋው የሚታይ ከሆነ ግን ተስፋ
አይደ ለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ
ያደርገዋል? 25ነገር ግን ገና ያላየነውን ተስፋ
ካደረግን በትዕግሥት እንጠብቀዋለን።
26እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን
ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን
አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ
በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል።
27ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ
የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም
መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን
ይማልዳልና።

## ከአሸናፊዎች በላይ

28እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ
ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲ
ሠራ እንደሚያደርግላቸው[a] እናውቃለን።[b]
29እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን
መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤
ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል
እርሱ በኵር እንዲሆን ነው። 30አስቀድሞ
የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን
አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው።
31ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን?
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን
ይችላል? 32ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን
ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ
ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰ
ጠን? 33እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ
ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤
34ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? የሞተው፣

8፥24 2ቆሮ4፥18፤ 1ተሰ5፥8፤ ቲቶ3፥7
8፥25 መዝ37፥7
8፥26 ቍ15፥16፤ ኤፌ6፥18
8፥27 ቍ34፤ ራእ2፥23
8፥28 ቍ30፤ ዘፍ50፥20፤ ኢሳ38፥17፤ ኤር29፥11፤ ሮሜ11፥29፤ 1ቆሮ1፥9፤ ገላ1፥6፥15፤ ኤፌ1፥11፤ 4፥1፥4፤ 2ተሰ2፥12፤ 2ጢሞ1፥9፤ ዕብ6፥17፤ 9፥15፤ 1ጴጥ2፥9፤ 2ጴጥ1፥10፤ 3፥11
8፥29 ሮሜ11፥2፤ 1ቆሮ15፥49፤ 2ቆሮ3፥18፤ ኤፌ1፥5፥11፤ ፊል3፥21፤ ቈላ1፥18፤
8፥29 1ጴጥ1፥2፤ 1ዮሐ3፥2 8፥30 ቍ28፤ ሮሜ4፥25፤ 9፥23፤ ኤፌ1፥5፥11 8፥31 ዘፀ3፥12፤ መዝ56፥9፤ 118፥6፤ ኢሳ8፥10፤ 41፥10፤ ኤር20፥11፤ ሐጌ1፥13፤ ሮሜ4፥1፤ 6፥1፤ 7፥7፤ 9፥14፥30፤ ዕብ13፥6 8፥32 ዘፍ22፥13፤ ሚል3፥17፤ ዮሐ3፥16፤ ሮሜ5፥8 8፥33 ኢሳ50፥8፥9 8፥34 ቍ1፤ 27፤ ኢዮ16፥20፤ ኢሳ53፥12፤ ማር16፥19፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ5፥6-8፤ ዕብ7፥25፤ 9፥24፤ 1ዮሐ2፥1

*[a]8፥28 ወይም በነ የሆነውን ለማድረግ እርሱን ከሚወዱት ጋር ይሠራል።*
*[b]8፥28 አንዳንድ ቅጆች እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን ይላሉ።*
**መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው።*

(1) ሐዘን በማያመጣባቸው የኀጢአት ዓለም የሚኖሩ አማኞች አሁንም ድረስ በጉድለት፣ በሕመምና በሐዘን ውስጥ እያለፉ ናቸው። መቃተቱም ከዚህ ሁኔታ የተነሣ የሚሰማንን የጠለቀ ሐዘን ይገልጣል (ከ2ቆሮ 5፥2-4 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) በትንሣኤ ጊዜ የሚቀበሉትን ሙሉ መዋጀትና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በማሰብ ይቃትታሉ። በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ክብር እንዲገለጥና እንደ ልጆች ያላቸው ሙሉ መብት እውን እንዲሆን ይቃትታሉ (ከ2ቆሮ 5፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

**8፥26 መንፈስ ... ለእኛ ይማልድልናል፤** መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በጸሎት እንዴት እንደሚረዳ ሦስት ዋና ዋና ሐሳቦችን ማስተዋል ይቻላል፤ (1) የእግዚአብሔር ልጆች ሁለት መለኮታዊ አማላጆች አሏቸው። ክርስቶስ በሰማይ ሆኖ ስለ አማኞች የሚማልድ ሲሆን (ቍ 34፤ 1ዮሐ 2፥1፤ ዕብ 7፥25 እና ማብ ይመ)፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በአማኙ ውስጥ ሆኖ በምድር ይማልዳል (በገጽ 1280 ላይ፣ *“የምልጃ ጸሎት”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። (2) *“በመቃተት”* የሚለው ሐሳብ አማኙ በማያሰማው መቃተት መንፈስ ይማልዳል ማለት ሊሆን ይችላል፤ ይህም መቃተት የሚካሄደው በአማኙ ልብ ውስጥ ነው። (3) የአማኞች መንፈሳዊ መሻትና መነሣሣት የሚመነጨው በውስጣቸው ከሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ራሱ የመጨረሻውን የመዋጀት ጊዜ እየጠበቀ በውስጣችን ያዝናል፣ ይቃትታል፣ አብሮንም መከራ ይቀበላል (ቍ 23-25)። ስለ መሻታችንም አብን “እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ” ይለምናል (ቍ 27)።

**8፥28 እግዚአብሔር ... ሁሉም ነገር ... ለበጎ ይሆንላቸው ዘንድ እንደሚሠራ፤** ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ልጆች መከራን ታግሠን እንድንቀበል የሚያበረታታ ነው። (1) እግዚአብሔር ከማንኛውም ዐይነት ሥቃይ፣ ፈተና፣ ስደትና መከራ መልካምን ነገር ያወጣል፤ እግዚአብሔር ከዚህ ሁሉ የሚሠራው ግን ነገር የክርስቶስን መልክ እንድንመስል የሚያደርገን ሲሆን፣ በመጨረሻም ክብርን ያጐናጽፈናል (ቍ 29፤ ገጽ 100 ላይ፣ *“መግቦተ እግዚአብሔር”* በሚልና ገጽ 744 ላይ፣ *“የጻድቃን መከራ”* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)። (2) ይህ ተስፋ እግዚአብሔርን ለሚወዱና በክርስቶስ በማመን ራሳቸውን ላስገዙለት ብቻ የተሰጠ ነው (ከዘፀ 20፥6፤ ከዘዳ 7፥9፤ ከመዝ 37፥17፤ ከኢሳ 56፥4-7፤ ከ1ቆሮ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። (3) “ሁሉም ነገር” ሲባል ኀጢአተኝነታችንና ቸልተኝነታችንን ይጨምራል ማለት አይደለም (ቍ 6፥13፤ 6፥16፤21፤23፤ ገላ 6፥8)፤ እግዚአብሔር ለበጎ ያደርገዋል ብሎ ማንም ኀጢአትን ከመቃወም ችላ መለት የለበትም።

**8፥29 እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን፤** በዚህ ጥቅስ “አስቀድሞ ያወቃቸው” ማለት “አስቀድሞ የወደዳቸው” ማለት ሲሆን ይህም “መውደድ”፣ “ከዘላለሙ ለመውደድ መምረጥ” የሚለውን ሐሳብ ያንፀባርቃል (ከዘፀ 2፥25፤ ከመዝ 1፥6፤ ከሆሴ 13፥5፤ ከማቴ 7፥23፤ ከ1ቆሮ 8፥3፤ ከገላ 4፥9፤ ከ1ዮሐ 3፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

(1) “አስቀድሞ ማወቅ” ሲባል የሰውን ዘር በክርስቶስ በኩል ለመውደድና ለማዳን እግዚአብሔር ከዘላለም ጀምሮ አቀደ ማለት ነው (5፥8፤ ዮሐ 3፥16)። የእግዚአብሔር ቀዳሚ ዕውቀት ወይም ቀዳሚ ፍቅር ተቀባይ ሆነው የተጠቀሱት በብዙ ቍጥር ስለሆነ፣ ይህ የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያንን ነው። ያም ማለት፣ የእግዚአብሔር ቀዳሚ ፍቅር በመሠረቱ አንድ ለሆነው የክርስቶስ አካል ሲሆን (ኤፌ 1፥4፤ 2፥4፤ 1ዮሐ 4፥19)፣ ግለሰቦችን የሚያቅፉትም በክርስቶስ በማመንና ከእርሱ ጋር ኅብረት በማድረግ ከአካሉ ጋር ሲተባበሩ ነው (ዮሐ 15፥1-6፤ በገጽ 1860 ላይ፣ *“ምርጫና አስቀድሞ መወሰን”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) አንድ የሆነው የክርስቶስ አካል ወደፊት ክብርን ይጐናጸፋል (ቍ 30)። እያንዳንዱ አማኝ አስቀድሞ ከተወደደው አካል ራሱን ቢለይና በክርስቶስ ላይ ያለውን እምነት ቢያጐድል፣ ከዚህ ክብር ውጪ ይሆናል (ቍ 12-14፤17፤ ቈላ 1፥21-23)።

**8፥30 አስቀድሞ የወሰናቸውን፤** ስለ ቅድመ ውሳኔ የተብራራ ሐሳብ ለማግኘት በገጽ 1860 ላይ፣ *“ምርጫና አስቀድሞ መወሰን”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**8፥34 ስለ እኛ ይማልዳል፤** ክርስቶስ በሰማይ

እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር
ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ
እኛ ይማልዳል። 35ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን
ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ
ስደት፣ ወይስ ራሀብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣
ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? 36ይህም፣
"ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር
እንጋፈጣለን፤
እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን"
ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።
37ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን
በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። 38ይህን
ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣
መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣ª ያለውም
ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኀይል፣
39ከፍታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም
2ቆሮ 11፥12-15 ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው
ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።

## የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ

9 በክርስቶስ ሆኜ እውነት እናገራለሁ፤
አልዋሽም፤ ኅሊናዬም በመንፈስ
ቅዱስ ይመሰክርልኛል። 2ታላቅ ሐዘንና
የማያቋርጥ ጭንቀት በልቤ አለ። 3ለወገኖቼ
ስል ስለ ወንድሞቼ እኔ ራሴ የተረገምሁና
ከክርስቶስም ተለይቼ የተጣልሁ እንድሆን
እንኳ እወድ ነበር፤ 4እነርሱም የእስራኤል
ሕዝብ ናቸው፤ ልጅ መሆን፣ መለኮታዊ
ክብር፣ ኪዳን፣ ሕግን መቀበል፣ የቤተ
መቅደስ ሥርዐትና ተስፋ የእነርሱ ናቸውና።
5አባቶችም የእነርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም
በሥጋ የትውልድ ሐረጉ የሚቈጠረው
ከእነርሱ ነው፤ እርሱም፣ ከሁሉ በላይ የሆነ
ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ነው፤ᵇ አሜን።
6ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአል
ማለት አይደለም፤ ከእስራኤል የተወለደ
ሁሉ እስራኤላዊ አይደለምና። 7ከአብርሃም
ዘርም ስለሆኑ፣ ሁሉም ልጆቹ አይደሉም፤
ይልቁ ንስ፣ "ትውልድህ በይሥሐቅ በኩል
ይጠራልሃል" እንደ ተባለው ነው። 8ይህም
ማለት የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የሥጋ
ልጆች አይደሉም፤ ነገር ግን የአብርሃም
ልጆች የተባሉት የተስፋው ልጆች ናቸው።
9"ጊዜው ሲደርስ እመለሳለሁ፤ ሳራም
ወንድ ልጅ ትወልዳለች" ተብሎ ተስፋው
ተሰጥቶአልና።
10ይህም ብቻ ሳይሆን፣ የርብቃ ልጆች
አንድ አባት አላቸው፤ እርሱም አባታችን
ይሥሐቅ ነው። 11መንትዮቹ ገና ሳይወለዱ፣

8፥35 ቍ37-39፤ 1ቆሮ4፤ 2ቆሮ11፥26፤ 27
8፥36 መዝ44፥22 1ቆሮ4፥9፤ 15፥30፡31፤ 2ቆሮ4፥11፤ 6፥9፤ 11፥23
8፥37 ሮሜ5፥8፤ 1ቆሮ15፥57፤ ገላ2፥20፤ ኤፌ5፥2፤ ራእ1፥5፤ 3፥9
8፥38 1ቆሮ3፥22፤ ኤፌ1፥21፤ ቈላ1፥16፤ 1ጴጥ3፥22
8፥39 ቍ1፤ ሮሜ5፥8፤ 16፥3
9፥1 መዝ15፥2፤ ሮሜ1፥9፤ 2ቆሮ11፥10፤ ገላ1፥20፤ 1ጢሞ2፥7
9፥3 ዘፀ32፥32፤ ሐሥ22፥5፤ ሮሜ1፥14፤ 1ቆሮ12፥3፤ 16፥22
9፥4 ዘፍ17፥2፤ ዘፀ4፥22፤ 6፥7፤ ዘዳ7፥6፤ 14፥13፤ መዝ147፥19፤ ሐሥ13፥32፤ 3፥25፤ ገላ3፥16፤ ኤፌ2፥12፤ ዕብ9፥1፤ 9፥5

9፥5 ማቴ1፥1-16፤ ዮሐ1፥1፤ ሮሜ1፥3፤ 1፥25፤ 11፥28፤ 2ቆሮ11፥31፤ ቈላ2፥9 9፥6 ሮሜ2፥28፡29፤ ገላ6፥16፤ ዕብ4፥12 9፥7 ዘፍ21፥12፤ ዕብ11፥18 9፥4 ቍ6
9፥8 ሮሜ8፥14፤ ገላ3፥16 9፥9 ዘፍ18፥10፡14
9፥10 ዘፍ25፥21 9፥11 ቍ16፤ ሮሜ8፥28

*ª8፥38 ወይም በሰማይ ያሉ አለቆች*
*ᵇ9፥5 ወይም ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ይሁን ወይም ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን*

ለአማኞች ስለሚያደርገው ምልጃ የዕብ 7፥25 ማብራሪያ ይመልከቱ፤ እንዲሁም በገጽ 1280 ላይ፣ «*የምልጃ ጸሎት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ።

**8፥36 እንደሚታረዱ በጎች፤** ሐዋርያው በቍ. 35-36 ላይ የዘረዘራቸው የሥቃይ ዐይነቶች በዘመናት ሁሉ የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ያለፉባቸው ሁኔታዎች ናቸው (ሐሥ 14፥22፤ 2ቆሮ 11፥23-29፤ ዕብ 11፥35-38)። አማኞች ችግር፣ ስደት፣ ረሃብ፣ ድኽነት ወይም አደጋ ቢገጥማቸው መሸበር አይገባቸውም። ችግርና መከራ ደረሰ ማለት እግዚአብሔር ረስቶናል ወይም እኛን መውደድ ትቷል ማለት አይደለም (ቍ. 35)። በአንጻሩ እንደ እማኝ መከራ መቀበላችን የእግዚአብሔርን ፍቅርና መጽናናት ለመለማመድ በር ይከፍትልናል ማለት ነው (2ቆሮ 1፥4-5)። ጳውሎስ በዚህ ሁሉ መከራችን ውስጥ በክርስቶስ በአሸናፊነት እንደምንወጣና ከአሸናፊዎችም እንደምንበልጥ ያረጋግጥልናል (ቍ. 37-39፤ ከማቴ 5፥10-12፤ ፊል 1፥29 ጋር ያነጻጽሩ)።

**8፥39 በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር፤** ማንም በመንፈሳዊ ሕይወት ቢደክም ከመለኮታዊ ጸጋ እና ፍቅር መንደል (ቍ. 31-34) ወይም ከውጫዊ ኀይል ወይም መከራ (ቍ. 35-39) የመጣ ነው ብሎ ማሰብ የለበትም፤ ይልቁንስ በክርስቶስ ኢየሱስ ለመኖር ችላ ከማለት የተነሣ የደረሰበት መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል (ዮሐ 15፥6 እና ማብ ይመ)። የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጠው «በክርስቶስ ኢየሱስ» በኩል ሲሆን፣ ልንለማመደው የምንችለውም በእርሱ በኩል ብቻ ነው። «ጌታችን» እንደ ሆነ በማመን በእርሱ ስንጸና ብቻ ከእግዚአብሔር ፍቅር እንደማንለይ ማረጋገጥ እንችላለን።

**9፥1-33** በዚህ ክፍል የእስራኤል አለማመን ተገልጾአል፤ ከምዕራፍ 9—11 ጳውሎስ የቀደመው የእስራኤል መመረጥ ያስከተለባቸውን ተጽዕኖ (9፥6-29)፤ የአሁኑን የወንጌል ተቃውሞ (9፥30—10፥21) እና የወደፊቱን ድነት (11፥1-36) በተመለከተ ጽፎአል። እርሱም የሚያነሣቸውን ነጥቦች በተመለከተ በገጽ 1758 ላይ፣ «*እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**9፥2 ታላቅ ሐዘን ... በልቤ አለ፤** ክርስቶስ ለሌላቸው ሰዎች ጳውሎስ የነበረው የማያቋርጥ ሐዘንና ግድ መሰኘት (10፥1፤ 11፥14፤ 1ቆሮ 9፥22) የማንኛውም ክርስቲያን ጕዳይ ሊሆን ይገባል። ይህን የመሰለው ሳልጸኑት ማዘንና መከራን ለመቀበል መፍቀድ በሙሴ (ዘፀ 32፥32) ዘንድም ታይቶአል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ተገልጦአል (ማቴ 23፥37፤ ሮሜ 3፥24-25)።

**9፥6 የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአል፤** ጳውሎስ ከዚህ ጥቅስ በመነሣት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስላለው ግንኙነትና በጊዜው ስለ ነበራቸው አለማመን ሰፋ ያለ ትንታኔ ይሰጣል (በገጽ 1758 ላይ፣ «*እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**9፥11 የእግዚአብሔር ሐሳብ፤** በዔሳውና በያዕቆብ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ በተመለከተ በገጽ 68 ላይ፣ «*እግዚአብሔር ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር የገባው ኪዳን*» በሚልና በገጽ 1758 ላይ፣ «*እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ*» በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመልከቱ።

*ወይም በጎም ሆነ ክፉ ሳያደርጉ፣ የእግዚአብሔር
ሐሳብ በምርጫ ይጸና ዘንድ፣ [12]በሥራ
ሳይሆን ከጠሪው በመሆኑ፣ "ታላቁ ታናሹን
ያገለግላል" ተብሎ ተነገራት። [13]ይህም፣
"ያዕቆብን ወደድሁ፤ ዔሳውን ግን ጠላሁ"
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።*
*[14]እንግዲህ ምን እንላለን? እግዚአብሔር
አድልዎ ያደርጋልን? በፍጹም አያደርግም!
[15]ለሙሴ፣*

*"የምምረውን እምረዋለሁ፤
ለምራራለትም እራራለታለሁ"
ይላልና።*
*[16]እንግዲህ ይህ ከሰው ፍላጎት ወይም
ጥረት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ምሕረት
የተነሣ ነው። [17]መጽሐፍ ፈርዖንን፣ "ኀይሌ
በአንተ እንዲታይ፣ ስሜም በምድር ሁሉ
እንዲነገር ለዚህ አስነሣሁህ" ይላልና።
[18]ስለዚህ እግዚአብሔር ሊምረው ለሚወደው
ምሕረት ያደርግለታል፤ ልቡ እንዲደነድን
የፈለገውንም ያደነ ድነዋል።*
*[19]ከእናንተ አንዱ፣ "ታዲያ እንደዚህ
ከሆነ እግዚአብሔር እስከ አሁን ለምን
ይወቅሰናል? ምክንያቱም ፈቃዱን ሊቋቋም
የሚችል ማን አለ?" ይለኝ ይሆናል።*

9፥12 ዘፍ25፥23
9፥13 ሚል1፥2፡3
9፥14 2ዜና19፥7፤ ሮሜ8፥31
9፥15 ዘፀ33፥19
9፥16 ኤፌ2፥8፤ ቲቶ3፥5
9፥17 ዘፀ9፥16፤ 14፥4፤ መዝ76፥10
9፥18 4፥21፤ 7፥3፤ 14፥4፡17፤ ዘዳ2፥30፤ ኢሱ11፥20፤ ሮሜ11፥25
9፥19 2ሳሙ16፥10፤ 2ዜና20፥6፤ ዳን4፥35፤ ሮሜ3፥7፤ 11፥19፤ 1ቆሮ15፥35፤ ያዕ2፥18
9፥20 ኢሳ64፥8፤ 29፥16፤ 45፥9፤ 10፥15፤ ኤር18፥6፤ ኢዮ1፥22፤ 9፥12፤ 40፥2
9፥21 2ጢሞ2፥20
9፥22 ምሳ16፥4፤ ሮሜ2፥4

*[20]ነገር ግን ለእግዚአብሔር መልስ የምትሰጥ
አንተ ማን ነህ? "ሥራ ሠሪውን፣ 'ለምን
እንዲህ ሠራኸኝ?' ይለዋልን?" [21]ሸክላ
ሠሪ፣ ከሚሠራው ጭቃ፣ አንዳንዱን ሸክላ
ለክብር፣ ሌላውን ደግሞ ለተራ አገልግሎት
የማድረግ መብት የለው ምን?*
*[22]እግዚአብሔር ቍጣውን ለማሳየት፣
ኀይሉንም ለማሳወቅ ፈልጎ የቍጣው
መግለጫ የሆኑትን፣ ለጥፋትም የተዘጋጁትን
እጅግ ታግሦ ቢሆንሳ! [23]አስቀድሞ ለክብር
ላዘጋጃቸው፣ የምሕረቱም መግለጫዎች
ለሆኑት፣ የክብሩ ባለ ጠግነት እንዲታወቅ
ይህን አድርጎ እንደ ሆነስ? [24]የጠራው
ከአይሁድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከአሕዛብ ወገን
የሆነውን እኛን እንኳ ሳይቀር አይደለምን?
[25]በሆሴዕ እንዲህ እንደሚል፤
"ሕዝቤ ያልሆኑትን፣ 'ሕዝቤ'
ብዬ እጠራቸዋለሁ"፤
ያልተወደደችውንም 'የተወደደችው'
ብዬ እጠራለሁ።
[26]ደግሞም፣ " 'ሕዝቤ አይደላችሁም'፤
ተብሎ በተነገራቸው በዚያ ቦታ፣
'የሕያው እግዚአብሔር ልጆች' ተብለው*

9፥23 ሮሜ2፥4፤ 8፥30 9፥24 ሮሜ8፥28፤ 3፥29
9፥25 ሆሴ2፥23፤ 1ጴጥ2፥10 9፥26 ሆሴ1፥10፤
ማቴ16፥16፤ ሮሜ8፥14

**9፥13 *ያዕቆብን ወደድሁ፣ ዔሳውን ግን ጠላሁ፤*** ይህ ጥቅስ ያዕቆብና ትውልዱ ለዘላለም ሕይወት፣ ዔሳውና ትውልዱ ደግሞ ለዘላለም ኵነኔ እንደ ተመረጡ አያመለክትም፤ በእንጻሩ ግን ምርጫው የያዕቆብ ውልድ ለዓለም ሁሉ የሚሆነው የእግዚአብሔር መገለጥና በረከት መተላለፊያ መንገድ እንዲሆን ነበር (ሚል 1፥3 እና ማብ ይመ)። በምዕ 9-11 መሠረት አብዛኛው የያዕቆብ ልጆች ጥሪያቸውን ተቀብለው መኖር እንዳልቻሉና በመጨረሻም በእግዚአብሔር እንደ ተተዉ ልብ ይበሉ (ቍ 27፡30-33፤ 10፥3፤ 11፥20)። በተጨማሪም፣ "ያልተወደዱት" (አሕዛብ) በእምነት እግዚአብሔርን ከመውደዳቸው የተነሣ "የሕያው እግዚአብሔር ልጆች" ተብለው ተጠርተዋል (ቍ 25-26)።

**9፥15 *እምረዋለሁ፤*** ይህ ጥቅስ ስለ እግዚአብሔር ምሕረት በአጽንዖት ይሰጣል። የማያቋርጥ የተትረፈረፈ ርኅራኄውን ሰው ይገባኛል ብሎ የራሱ ሊያደርገውም ሆነ ሊቈጣጠረው አይችልም (ቍ 16)፤ ጌታ ግን ለሁሉም ምሕረት ያደርግ ዘንድ ፈቀደ (11፥32)።

**9፥18 *ሊምረው ለሚወደው፤*** ንስሓ በመግባት ኢየሱስን ጌታና አዳኝ አድርገው ለሚቀበሉት እግዚአብሔር ምሕረቱን ማሳየት የሚፈልግ ሲሆን፣ ንስሓ መግባትን ባለመቀበል በኀጢአት ለመቀጠል የሚፈልጉትንና በክርስቶስ ያለውን ድነት የሚያጣጥሉትን ደግሞ ልባቸውን ያደነድናል፤ ይህም ለማንም ሰው ወይም ሕዝብ ሲባል የማይለወጥ ቋሚ መለኮታዊ ዐላማ ነው (ከ2፥4-11 ጋር ያነጻጽሩ)።

**9፥18 ልቡ እንዲደነድን የፈለገውንም፤** የፈርዖን ልብ መደንደን አንዳንዴ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ሲገለጽ (ዘፀ 4፥21፤ 7፥3፡13፤ 9፥12፤ 10፥1፤ 11፥10፤ 14፥17) በሌላ ጊዜ ደግሞ ከራሱ ከፈርዖን እንደነበር ተመልክቷል (ዘፀ 7፥22-23፤ 8፥15፡32)። ከልቡ ትዕቢት የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላው ፈርዖን ተገቢውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ተቀበለ። ለእግዚአብሔር ፈቃድም እምቢተኛ እየሆነ በመምጣቱም እግዚአብሔር የበለጠ ልቡን አደነደነው (ዘፀ 7፥3 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ያደነደነው በዘፈቀደ አይደለም፤ እግዚአብሔር ጽድቅ በሆነው መርሑ መሠረት በእርሱ ላይ የማያምኑትን ሁሉ ልባቸውን ያደነድናል (ከ1፥12-32 ጋር ያነጻጽሩ)።

**9፥21 ሸክላ *ሠሪ* ... *መብት* የለውምን?** እግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅዱን ለመፈጸም ማንንም ሳያማክር የፈለገውን ሕዝብ እንደሚጠቀም ጳውሎስ ያመለክታል። (1) እግዚአብሔር ከሰዎችና መንግሥታት ጋር ግንኙነትን ሲፈጥር በተቀደሰ ባሕርይው ውስጥ ግብረ ገባዊ መርሕ የለውም ማለት አይደለም፤ እግዚአብሔር በባሕርይው የሚመራው በሰው ፈቃድ ሳይሆን በፍቅሩ (ዮሐ 3፥16)፣ በምሕረቱ (መዝ 25፥6) እንዲሁም ፍጹም በሆነው ምግባሩና ርኅራኄው (መዝ 116፥5) ነው። (2) ከቍ 6-29 ባለው ክፍል ላይ ተንተርሰው እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለድነት ሌሎችን ደግሞ ለጥፋት ይመርጣል የሚሉ ሰዎች የቀቀሰቹን ሐሳብ ለማዛባት የተረዱ ናቸው (በገጽ 1860 ላይ፣ *"ምርጫና አስቀድሞ መወሰን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**9፥22-23 የቍጣው መግለጫ ... የምሕረቱም መግለጫዎች፤** *"የቍጣው መግለጫዎች"* የሚለው ሐረግ ለዘላለም ጥፋት የተዘጋጁትን ያመለክታል። ጳውሎስ አስቀድሞ *"ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ ልብህ ምክንያት ... ቍጣን ታከማቻለህ"* (2፥5) እንዳለ፣ ሰዎች የቍጣ መግለጫ የሚሆኑት ከገዛ ራሳቸው የኀጢአት ሥራና ዐመፅ የተነሣ ነው፣ ይሁንና *"የቍጣ መግለጫዎች"* የተባሉት ንስሓ ሊገቡ፣ ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱና ምሕረቱን ሊቀበሉ ይችላሉ። *"የምሕረቱ መግለጫዎች"* የሚለው ሐረግ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑትን አይሁድንም ሆነ አሕዛብን ያመለክታል (ቍ 24-33)።

# እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ

*ሮሜ 9፥6 "ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአል ማለት አይደለም፥ ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤል አይደለምና።"*

**መግቢያ፤** በሮሜ 9—11 ሐዋርያው ጳውሎስ ስለቀድሞ የእስራኤል ምርጫ፣ አሁን ደግሞ ወንጌልን ስላለመቀበሏና ወደፊት ስላለው ድነቷ ያሉትን ጉዳዮች ያቀርባል። እነዚህ ሦስት ምዕራፎች የተጻፉት አይሁድ አማኞች እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሕዝበ እስራኤል የገባቸው ተስፋዎች እስራኤላውያን የወንጌል ተካፋይ በማይሆኑበት ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆኑት እንዴት ነው) በማለት ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። ይህ የትኩረት ጽሑፍ የጳውሎስን ማስረጃ ባጭሩ ያቀርባል።

**አጠቃላይ ምልከታ፤** እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ ውስጥ ያላትን ድርሻ በማመልከት በጳውሎስ ሐተታ ውስጥ ሦስት ፍሬ ሐሳቦች ይገኛሉ፤

(1) የመጀመሪያው (ሮሜ 9፥6-29) የእስራኤልን የቀድሞ ምርጫ የሚዳስስ ነው። (ሀ) በ9፥6-13 ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባው ተስፋ እንዳልታጠፈ ያጸናል፣ ምክንያቱም ድሮም ቢሆን ተስፋው ከሕዝቡ ታማኝ ያልሆኑትን ስለማያጠቃልል ነው። ተስፋው ቀድሞም ቢሆን የታቀደው ለተስፋው ታማኝ ለሆኑት እውነተኛ እስራኤላውያን ብቻ ነው (ዘፍ 12፥1-3፤ 17፥19 ይመ)። ሁልጊዜም በዚያው በእስራኤል ሕዝብ ውስጥ ተስፋውን የተቀበሉ ታማኝ እስራኤላውያን ይገኛሉ። (ለ) በ9፥14-29 ላይ ደግሞ ጳውሎስ እግዚአብሔር በግለሰቦችም ሆነ በሕዝቦች ላይ የፈቀደውን ሊያደርግ እንደሚችል ይጠቁማል። እስራኤልን ባለመታዘዟ ሊተዋት ለአሕዛብም ምሕረትን አሳይቶ ድነትን ሊሰጣቸው ይችላል።

(2) ሁለተኛው ዐብይ ክፍል (ሮሜ 9፥30—10፥21) ደግሞ እስራኤል ወንጌልን አሁን ባለመቀበላቸው ጉዳይ ላይ ያተኩራል። ክርስቶስን ያለመቀበላቸው ጉዳይ እግዚአብሔር በማያወላዳ ሁኔታ ደንግጎባቸው ሳይሆን ካለማመናቸውና ካለመታዘዛቸው የተነሣ ነው (ሮሜ 10፥3 እና ማብ ይመ)።

(3) በመጨረሻም በሮሜ11 ላይ የእስራኤል መተው በከፊልና ጊዜአዊ መሆኑን ጳውሎስ ያብራራል። የኋላ ኋላ ግን እስራኤል በክርስቶስ ኢየሱስ እውን የሆነውን የእግዚአብሔርን ድነት ትቀበላለች፤ በዚህም ሐተታው ላይ በርካታ ደረጃዎች አሉ፤ (ሀ) እግዚአብሔር እውነተኛይቱን እስራኤል አልተዋትም፤ ምክንያቱም እርሱ ታማኝ በመሆኑ ክርስቶስን በመቀበል ታማኝ ለሆኑ "ቅሬታዎቹ" ታማኝ ሆኖአልና (11፥1-6)። (ለ) እግዚአብሔር አሁን ብዙዎቹን እስራኤላውያንን ያደነደነበት ምክንያት ክርስቶስን ለማመን እምቢ በማለታቸው ነው (11፥7-10 ይመ፤ ከ9፥31—10፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። (ሐ) የእስራኤልን አለማመን (ይህም በክርስቶስ መስቀል አለማመናቸው) ነው። እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ ድነትን የማወጅ ምክንያት አድርጎታል (11፥11-12፡15)። (መ) እስራኤል በማያምኑበት በአሁኑ ጊዜ በግለሰብ ደረጃ ያለው የአይሁድም ሆነ የአሕዛብ ድነት (ከ10፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ) የሚወሰነው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ነው (11፥13-24)። (ሠ) ከፊሉ የእስራኤል ሕዝብ በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያምንበት ጊዜ ወደፊት ይሆናል (11፥25-29)። (ረ) የእግዚአብሔር ዋና ዐላማ አይሁድንም ሆነ አሕዛብን ማለትም በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ወደ መንግሥቱ ለመጠቅለል ነው (11፥30-36 ይመ፤ ከ10፥12-13 እና ከ11፥20-24 ጋር ያነጻጽሩ)።

**እይታ፤** በሮሜ መጽሐፍ ባሉ በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች (9—11) ውስጥ በርካታ ጉዳዮች ጐልተው ይታያሉ፤

(1) ይህ ስለ እስራኤል የተሰጠው ዘገባ ደረጃ ከሥጋ ሞት በኋላ ስለማሆነው ግለሰብን በተመለከተ የዘላለም ሕይወትና ሞትን በቀዳሚነት የሚያወሳ አይደለም። ይልቁንም ጳውሎስ የሚገልጸው እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሕዝቦች ላይ የነበረውን አሠራር፣ ማለትም አንዳንድ አገሮችንና ሕዝቦችን እንደ ፈቃዱ እንዴት እንደሚጠቀመባቸው ለማሳየት ነው። ለአብነት ያህልም፣ ከወንድሙ ከዔሳው ይልቅ የያዕቆብ መመረጥ (ሮሜ 9፥11) ከእነርሱ የወጡትን የእስራኤልና የኤዶምን ሕዝብ ለመመሥረትና ለመጠቀም ካለው ዐላማ አንጻር ነው። ይህ ምርጫ ከእነዚህ ግለሰቦች የመዳንና የመጥፋት የዘላለም ዕጣ ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም።

ዋናው ነጥብ እግዚአብሔር እነዚህን የመረጣቸውን ግለሰቦችም ሆነ ሕዝቦች የመጥራትና ኀላፊነት የመስጠት መብት አለው የሚለው ነው።

(2) ጳውሎስ ለአይሁድ ሕዝብ ያለውን የማያቋርጥ ጭንቀትና ጥልቅ ሐዘን ይገልጻል (ሮሜ 9፥1-3)። የአገሩ ሕዝቦች ይድኑ ዘንድ መጸለዩ በራሱ፣ ሰዎች ሁሉ አስቀድመው ከመወለዳቸው በፊት ለገሃነም አለዚያም ለመንግሥተ ሰማይ ተመድበዋል በማለት የሚያስተምርን የቅድመ ውሳኔ አስተምህሮ የማይቀበል መሆኑን ያሳያል። ይልቁንም የጳውሎስ የልብ መሻትና ጸሎት እግዚአብሔር የአይሁድ ሕዝብ ይድኑ ዘንድ ያለውን ምኞት ያሳያል (ከሮሜ 10፥21 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 19፥41 እና ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳን በየትኛውም ስፍራ አንዳንድ ሰዎች ከመወለዳቸው በፊት ለገሃነም አስቀድመው ተመድበዋል የሚልን ትምህርት አናገኝም (በገጽ 1860 ላይ፣ "ምርጫና አስቀድሞ መወሰን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) በዚህ ሁሉ ማብራሪያ ውስጥ ዐብይ የሆነው የእምነት ጉዳይ ነው። አብዛኛው የእስራኤል ሕዝብ በመንፈሳዊ ሁኔታቸው ተጠፋበት ጉዳይ እግዚአብሔር በዘፈቀደ ፍርድ ስጥቶባቸው ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ለተገለጠው የእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ ለመገዛት ካለመፍቀዳቸው የተነሣ ነው (ሮሜ 9፥33፤ 10፥3፤ 11፥20)። ይሁን እንጂ ብዙ አሕዛብ የእግዚአብሔርን የእምነት መንገድ ተቀበሉ፤ በእምነት የሆነውንም ጽድቅ አገኙ። እግዚአብሔርን በእምነት ታዘዙት፤ "የሕያው አምላክም ልጆች" ሆኑ (9፥25-26)። ይህም ከእግዚአብሔር ጥሪና ምርጫ አንጻር በእምነት የሚገኘውን መታዘዝ (1፥5፤ 16፥26) እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል።

(4) አሁንም ቢሆን እስራኤል ባለማመኗ ባትቀጥል ተስፋ ተሰጥቶአታል (ሮሜ 11፥23)። በተመሳሳይ ሁኔታም ከእግዚአብሔር ማኅበር የሆኑ አሕዛብ አማኞችም በጥንቃቄ ካልተመላለሱ ከድነት ሊቈረጡ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። ስለዚህ፣ የእስራኤል ሁኔታ እንዳይደርስባቸው በፍርሃት እምነታቸውን ይቀጥሉ ዘንድ መትጋት ይገባቸዋል (11፥20-23)። ይህ ማስጠንቀቂያ ጳውሎስ በጻፈበት ጊዜ እንደነበረ ሁሉ አሁንም ተፈጻሚነት አለው።

(5) መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤል የኋላ ኋላ በመሲሑ በማመን መንፈሳዊ ተሐድሶ እንደምታገኝ ብዙ ተስፋዎች ተሰጥቶአታል፤ ይህ መታደስ በታላቁ መከራ ፍጻሜ ከክርስቶስም ዳግም ምጽአት በፊት ጥቂት ቀደም ብሎ ይከሰታል (ኢሳ 11፥10-16 እና ማብ፤ 24፥17-23 እና ማብ፤ 49፥22-26 እና ማብ፤ ኤር 31፥31-34 እና ማብ፤ ሕዝ 37፥12-14 እና ማብ፤ ሮሜ 11፥26 እና ማብ፤ ራእ 12፥6 እና ማብ ይመ)።

ይጠራሉ።"
27ኢሳይያስም ስለ እስራኤል እንዲህ ሲል
ይጮኻል፤
"የእስራኤል ልጆች ቍጥር
በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ቢሆንም፣
ትሩፉ ብቻ ይድናል።
28ጌታ ፍርዱን በምድር ላይ፣
በፍጥነትና ለመጨረሻ ጊዜ
ይፈጽማልና።"
29ይኸውም ቀደም ሲል ኢሳይያስ
እንደ ተናገረው ነው፤
"የሰራዊት ጌታ፣ ዘር ባያስቀርልን ኖሮ፣
እንደ ሰዶም በሆን ነበር፤
ገሞራንም በመሰልን ነበር።"

### የእስራኤል አለማመን

30እንግዲህ ምን እንበል? በእምነት
የሆነውን ጽድቅ፣ ለጽድቅ ያልደከሙት
አሕዛብ አገኙት፤ 31ነገር ግን የጽድቅን ሕግ
የተከታተሉት እስራኤል አላገኙትም። 32ይህ
ለምን ሆነ? በእምነት ሳይሆን በሥራ እንደ
ሆነ አድርገው በመቍጠር ስለ ተከታተሉት
ነው፤ እነርሱም፣ "በማሰናከያው ድንጋይ"
ተሰናከሉ።
33ይህም፣
"እነሆ፤ ሰዎችን እንዲደናቀፉ
የሚያደርግ ድንጋይ፣
እንዲወድቁ የሚያደርግ ዐለት፣
በጽዮን ላይ አስቀምጫለሁ፤
በእርሱም የሚያምን አያፍርም"
ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

10 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እስራኤላው
ያን የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም
የምለምነው እንዲድኑ ነው። 2ስለ እግዚአብሔር
ቀናተኞች እንደ ሆኑ ስለ እነርሱ
መመስከር እችላለሁና፤ ቅናታቸው ግን
ከዕውቀት የተነሣ አይደለም። 3ከእግዚአብሔር
የሚመጣውን ጽድቅ ስላላወቁና የራሳቸውን
ጽድቅ ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣ ለእግዚአብሔር
ጽድቅ አልተገዙም። 4ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ
ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።
5ሙሴ በሕግ በኩል የሆነውን ጽድቅ ሲገ
ልጽ፣ "እነዚህን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ
ይኖራል" ይላል። 6ከእምነት የሆነው ጽድቅ
ግን እንዲህ ይላል፤ " 'በልብህ ማን ወደ
ሰማይ ይወጣል?' አትበል"፤ ይህ ክርስቶስን
ለማውረድ ነው፤ 7"ወይም 'ወደ ጥልቁስ ማን
ይወርዳል?' አትበል"፤ ይህም ክርስቶስን
ከሙታን ለማውጣት ነው። 8ነገር ግን ምን
ይላል? "ቃሉ በአጠገብህ ነው፤ በአፍህና
በልብህም ውስጥ ነው፤" የምንሰብከውም
የእምነት ቃል ይህ ነው፤ 9"ኢየሱስ ጌታ ነው"
ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም

9፥27 ዘፍ22፥17፤ ኢር44፥14፤ 50፥20፤ ሆሴ1፥10፤ 2ነገ19፥4፤ ኢል2፥32፤ ሮሜ11፥5
9፥28 ኢሳ10፥22-23
9፥29 ዘፍ19፥24-29፤ ዘዳ29፥23፤ ኢሳ1፥9፤ 13፥19፤ ኤር50፥40፤ ያዕ5፥4
9፥30 ሮሜ8፥31፤ 1፥17፤ 3፥22፤ 4፥5፣13፤ 10፥6፤ ገላ2፥16፤ ፊል3፥9፤ ዕብ11፥7
9፥31 ዘዳ6፥25፤ ኢሳ51፥1፤ ሮሜ10፥2-3፤ 11፥7፤ ገላ5፥4
9፥32 1ጴጥ2፥8
9፥33 ኢሳ8፥14፤ 28፥16፤ ሮሜ10፥11፤ 1ጴጥ2፥6-8
10፥1 መሣ20፥4
10፥2 ሐሥ21፥20
10፥3 ሮሜ1፥17፤ 9፥31
10፥4 ሮሜ7፥1-4፤ 3፥22፤ ገላ3፥24
10፥5 ዘሌ18፥5፤ ዘዳ4፥1፤ 6፥24፤
10፥5 ነህ9፥29፤ ምሳ19፥16፤ ኢሳ55፥3፤ ሕዝ20፥11፣13፣21፤ ሮሜ7፥10 10፥6 ዘዳ30፥12፤ ሮሜ9፥30 10፥7 ዘዳ30፥13፤ ሐሥ2፥24 10፥8 ዘዳ30፥14 10፥9 ማቴ10፥32፤ ዮሐ13፥13፤ 3፥15፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ11፥14

**9፥32 በእምነት ሳይሆን፤** የአብዛኛው እስራኤል መንፈሳዊ ችግር በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የእግዚአብሔርን የድነት ዕቅድ ለመቀበል ፈቃደኛ ካለመሆን የተነሣ የመጣ ነበር (ቍ 33)። ይሁን እንጂ አሕዛብ የእግዚአብሔርን የድነት መንገድ ሲቀበሉ በእምነት የሆነውን ጽድቅ አገኙ (ቍ 30)።

**10፥1 የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም የምለምነው፤** የጳውሎስ ምኞት ሰዎች ለመንግሥተ ሰማያት ወይም ለገሃነም የተወሰኑ ወይም የተመደቡ ናቸው ከሚለው ሐሳብ ጋር እንዴት እንደማይስማማ ለመረዳት፣ በገጽ 1758 ላይ፣ *«እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**10፥3 አልተገዙም፤** ምዕ 10 ከምዕ 9—11 ድረስ ካለው የጳውሎስ ትንታኔ ጋር እንዴት እንደሚጣጣም ለማየት በገጽ 1758 ላይ፣ *«እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**10፥9-10 ብትመሰክር ... በልብህ ብታምን፤** የድነት መሠረታዊ እውነቶች በዚህ ስፍራ በአጭሩ ተገልጸዋል። በክርስቶስ ጌትነትና በአካላዊ ትንሣኤው ላይ ባለ እምነት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው። እምነት ከልብ ነው፥ ልብም ፍልቅ ስሜትን፣ አእምሮንና ፈቃድን ያጠቃልላል፤ የሰውንም ሁለንተና ይይዛል። እምነት በቃልና በተግባር ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአደባባይ መግለጥ አለበት (በገጽ 1746 ላይ፣ *«እምነትና ጸጋ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**10፥9 «ኢየሱስ ጌታ ነው» ብለህ ... ብትመሰክር፤** የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የጥንቱ የእምነት መግለጫ ወይም ምስክርነት «ኢየሱስ አዳኝ ነው» ከሚለው ይልቅ «ኢየሱስ ጌታ ነው» የሚል ነበር (ከሐሥ 8፥16፤ 19፥5፤ ከ1ቆሮ 12፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን «አዳኝ» ተብሎ የተጠራው 16 ጊዜ ሲሆን፣ «ጌታ» በመባል ደግሞ ከ450 ጊዜ በላይ ተጠርቷል። (1) ዛሬ በአንዳንድ የወንጌል አማኞች ዘንድ ኢየሱስ የአንድ ሰው የሕይወቱ ጌታ ሳይሆን አዳኝ ሊሆን ይችላል በማለት የሚሰጠው ትምህርት በአዲስ ኪዳን የትም ቦታ የማገኝ አይደለም። ማንም ሰው ኢየሱስን የሕይወቱ ጌታ አድርጎ ካልተቀበለው አዳኙ ሊሆን አይችልም፤ ይህም በሐዋርያት ትምህርት ውስጥ ዋና አስተምህሮ ነበር (ሐሥ 2፥36-40)።

(2) «ጌታ» (በግሪክ «ኪሪዮስ») ማለት ኀይል፣ አገዛዝ፣ ሥልጣንና የጌትነት መብት ያለው ማለት ነው። «ኢየሱስ ጌታ ነው» ብሎ መመስከር ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል እንደሆነና (ቍ 13፤ ዮሐ 20፥28፤ ሐሥ 2፥36፤ ዕብ 1፥10) ኀይል (ራእ 5፥12)፣ አምልኮ (ፊል 2፥10-11)፣ መታመን (ዮሐ 14፥1፤ ዕብ 2፥13)፣ ታዛዥነት (ዕብ 5፥9) እና ወደ እርሱም መጸለይ (ሐሥ 7፥59-60፤ 2ቆሮ 12፥8) እንደሚገባው ማወጅ ነው።

(3) የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ኢየሱስን «ጌታ» ብለው ሲጠሩ አፋዊ ሳይሆን፤ ክርስቶስንና ቃሉን የሕይወታቸው ሁሉ ጌታ ያደረጉበት (ሉቃ 6፥46-49፤ ዮሐ 15፥14) ጥልቅ የሆነ እውነተኛ የልብ ሐሳብ መግለጫ ነው (ከ1ጴጥ 3፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። ኢየሱስ በቤትና በቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ጌታ መሆን አለበት፤ በተጨማሪም የአእምሮ፥ የገንዘብ፥ የትምህርት፣ የመዝናኛ ሁኔታዎችና በአጠቃላይ የሥራ መስኮች ሁሉ ማለትም በሕይወት ገጠመኞች ሁሉ ላይ

ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣
ትድናለህ። 10የምትጸድቀው በልብህ አምነህ
ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክረህ
ነውና። 11መጽሐፍ እንደሚለው፣ "በእርሱ
የሚያምን ሁሉ አያፍርም።" 12በአይሁድና
በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፤ አንዱ
ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፤ የሚለምኑትንም
አብዝቶ ይባርካል፤ 13"የጌታን ስም የሚጠራ
ሁሉ ይድናልና።"
14ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው
ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት
ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስ
ማት ይችላሉ? 15ካልተላኩስ እንዴት
መስበክ ይችላሉ? ይህም፣ "የምሥራችን
የሚያመጡ እግሮች እንዴት ያማሩ
ናቸው!" ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።
16ነገር ግን የሰሙት ሁሉ የምሥራቹን ቃል
አልተቀበሉም፤ ኢሳይያስም፣ "ጌታ ሆይ፤
መልእክታችንን ማን አምኖአል?" ብሎአልና።
17እንግዲያስ እምነት የሚገኘው መልእክቱን
ከመስማት ነው፤ መልእክቱም በክርስቶስ
ቃል ነው። 18ነገር ግን አልሰሙ ይሆን?
ብዬ እጠይቃለሁ፤ በርግጥ ሰምተዋል፤
"ድምፃቸው በምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ
ተሰማ።"
19ደግሜም እጠይቃለሁ፤ እስራኤል አላስ
ተዋሉ ይሆን? በቅድሚያ ሙሴ እንዲህ
ይላል፤
"ሕዝብ ባልሆኑት አስቀናቸዋለሁ፤
ማስተዋል በሌለው ሕዝብ አስቈጣ
ቸዋለሁ"
20ኢሳይያስም በድፍረት፣
"ላልፈለጉኝ ተገኘሁ፤
ላልጠየቁኝ ራሴን ገለጥሁላቸው" ይላል።
21ስለ እስራኤል ግን፣
"ወደማይታዘዝና እሺ ወደማይል
ሕዝብ፣
ቀኑን ሙሉ እጄን ዘረጋሁ" ይላል።

10፥11 ኢሳ28፥16፤ ሮሜ9፥33
10፥12 ማቴ28፥18፤ ሮሜ3፥22፡29
10፥13 ኢዩ2፥32፤ ሐሥ2፥21
10፥15 ኢሳ52፥7፤ ናሆ1፥15
10፥16 ኢሳ53፥1፤ ዕብ4፥2፤ ዮሐ12፥38
10፥17 ገላ3፥2፡5፤ ቈላ3፥16
10፥18 መዝ19፥4፤ ማቴ24፥14፤ ሮሜ1፥8፤ ቈላ1፥6፡23፤ 1ተሰ1፥8
10፥19 ዘዳ32፥21፤ ሮሜ11፥11፡14
10፥20 ኢሳ65፥1፤ ሮሜ9፥30
10፥21 ኢሳ65፥2፤ ኤር35፥17
11፥1 ዘሌ26፥44፤ 1ሳሙ12፥22፤ መዝ94፥14፤ ኤር31፥37፤ 33፥24-26፤ 2ቆሮ11፥22፤ ፊል3፥5
11፥2 ቍ1፤ ሮሜ8፥29
11፥3 1ነገ19፥10፡14
11፥4 1ነገ19፥18
11፥5 ሮሜ9፥27፤ 3፥24
11፥6 ሮሜ4፥4
11፥7 ቍ25፤ ሮሜ9፥18፤ 9፥31
11፥8 ዘዳ29፥4፤ ኢሳ29፥10፤ ማቴ13፥13-15
11፥10 ቍ8፤ መዝ69፥22፡23
11፥11 ቍ1፤ 14፤ ሐሥ13፥46፤ ሮሜ10፥19

## የእስራኤል ትሩፋን

11 እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ተዋቸውን? ብዬ እጠይቃለሁ፤
በፍጹም! እኔ ራሴ ከብንያም ነገድ፣
የአብርሃም ዘር የሆንሁ እስራኤላዊ ነኝ።
2እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ
አልጣላቸውም። ኤልያስ በእስራኤል ላይ ክስ
ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንዳቀረበ፣ መጽሐፍ
ስለ እርሱ ምን እንደሚል አታውቁምን?
3"ጌታ ሆይ፤ ነቢያትህን ገድለዋል፤ መሠ
ዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ እኔም ብቻዬን
ቀረሁ፤ ሊገድሉኝም ይፈልጋሉ።" 4እግዚአ
ብሔር የሰጠው መልስ ግን ምን ነበር? "ለበኣል
ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለራሴ
አስቀርቻለሁ።" 5በአሁኑ ጊዜም እንደዚሁ
በጸጋ የተመረጡ ትሩፋን አሉ። 6እንግዲህ
በጸጋ ከሆነ በሥራ አይደለም፤ በሥራ
ቢሆንማ ኖሮ ጸጋ፣ ጸጋ መሆኑ በቀረ ነበር።[a]
7እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል
አጥብቀው የፈለጉትን አላገኙትም፤
የተመረጡት ግን አገኙት፤ የቀሩትም
ልባቸው ደነደነ፤
8እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
"ዐይናቸው እንዳያይ፣
ጆሮአቸውም እንዳይሰማ፣
እግዚአብሔር እስከዚህ ቀን ድረስ
የድንዛዜ መንፈስ ሰጣቸው።"
9ዳዊትም አለ፤
"ማእዳቸው አሽክላና ወጥመድ፣
ዕንቅፋትና ቅጣት ይሁንባቸው።
10ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጋረዱ፤
ወገባቸውም ለዘላለም ይጕበጥ።"

## የተጸቀሉ ቅርንጫፎች

11ተመልሰው እስከማይድኑ ድረስ
ተሰናከሉን? ብዬ እንደ ገና እጠይቃለሁ፤
ከቶ አይደለም፤ ይልቁንም እስራኤልን
ለማስቀናት ሲባል በእነርሱ መተላለፍ

[a]11፥6 አንዳንድ ቅጆች በሥራ ቢሆንማ ኖሮ ጸጋ መሆኑ በቀረ ነበር፤ በጸጋ ከሆነም ሥራ፣ ሥራ መሆኑ ይቀራል። ይላሉ

ጌታ መሆን አለበት (12፥1-2፤ 1ቆሮ 10፥31)።

**10፥9 እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው፤** የክርስቶስን የአካል ትንሣኤ የሚክድ ማንም ሰው እውነተኛ ክርስቲያን ነኝ ብሎ ሊናገር አይችልም፤ በድነት ውስጥ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መሠረታዊ ነገር ስለሆነ፣ እንዲህ ዐይነቱ ሰው ያለው ገና ባለማመን ውስጥ ነው (1፥4፤ 4፥25፤ 5፥10፡17፤ 6፥4-10፤ 8፥11፡34)።

**11፥1 እግዚአብሔር ሕዝቡን ተዋቸውን?** እግዚአብሔር እስራኤልን መተው በከፊልና ጊዜአዊ እንደሆነ ጳውሎስ ይናገራል፤ በመጨረሻ እስራኤል በክርስቶስ ያለውን የእግዚአብሔርን ድነት ይቀበላሉ። በምዕ 11 ላይ ያለው የጳውሎስ ትንታኔ ከምዕ 9፥11 ጋር እንዴት እንደሚጣጣም ለማወቅ በገጽ 1758 ላይ፣ «እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**11፥5 በጸጋ የተመረጡ፤** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከበትን ቸርነት የተሞላበት ዕቅዱን ነው። ምርጫው «ዓለም ሳይፈጠር» ከእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የወጣ ነው (ኤፌ 1፥4)። ይህ ምርጫ ከመሲሑ መምጣት፣ ሞትና ትንሣኤ ጀምሮ በክርስቶስና በወንጌል አምነው የሚታዘዙትን ሁሉ ያካትታል። ስለዚህ እግዚአብሔርም ሆነ ሰው በዚህ ምርጫ የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። በጸጋ የሆነው የዚህ ምርጫ ግብም በእግዚአብሔር ፊት «ቅዱስና ነውር የሌለብን» ሆነን እንድንገኝ ነው (ኤፌ 1፥4 ይመ፤ ከሮሜ 3፥22፤ 4፥1-5፡16፤ 11፥11-24፤ ከ2ቆሮ 5፥19-20፤ ከኤፌ 2፥8-10 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1860 ላይ፣ «ምርጫና አስቀድሞ መወሰን» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**11፥7 የቀሩትም ልባቸው ደነደነ፤** የልብን መደንደን በተመለከተ 9፥18 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**11፥11 ድነት ለአሕዛብ መጥቶአል፤** የእስራኤል በደል ይኸውም ኢየሱስ መቃወማቸውና መስቀላቸው ለዓለም ድነትን አስገኘ (ኢሳ 49፥5-6 እና ማብ ይመ)።

ምክንያት ድነት ለአሕዛብ መጥቶአል።
12ነገር ግን የእነርሱ መተላለፍ ለዓለም
በረከት ከሆነ፣ ውድቀታቸ ውም ለአሕዛብ
በረከት ከሆነ፣ ሙላታቸው ምን ያህል ታላቅ
በረከት ያመጣ ይሆን?
13አሕዛብ ሆይ፤ ለእናንተ እናገራለሁ፤
የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኔ መጠን
አገልግሎቴን በትጋት እፈጽማለሁ፤
14ይኸውም የገዛ ወገኖቼን እንዲቀኑ
እንዲገፋፉና ከእነርሱ ጥቂቱን ለማዳን ተስፋ
በማድረግ ነው። 15የእነርሱ መተው ለዓለም
ዕርቅን ካስገኘ፣ ተቀባይነት ማግኘታቸውማ
ከሞት መነሣት ነው ከማለት በቀር ሌላ
ምን ሊሆን ይችላል? 16በኵር ሆኖ የቀረበው
የሊጡ ክፍል ቅዱስ ከሆነ፣ ሊጡ
ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩ ቅዱስ ከሆነ፣
ቅርንጫፎቹም ቅዱሳን ናቸው።
17ከቅርንጫፎቹ አንዳንዶቹ ቢሰበሩ፣
አንተም የበረሓ ወይራ ሆነህ ሳለ በሌሎቹ
መካከል ገብተህ ከተጣበቅህና ከወይራው
ዘይት ሥር የሚገኘውን በረከት ተካፋይ
ከሆ ንህ፣ 18በእነዚያ ቅርንጫፎች ላይ አትኵ
ራራ። ብትኰራ ግን ይህን አስተውል፤
አንተ ሥሩን አትሸከምም፤ ሥሩ ግን
አንተን ይሸከ ምሃል እንጂ። 19እንግዲህ፣
"ቅርንጫፎች የተሰበሩት እኔ እንድገባ
ነው" ትል ይሆናል። 20ትክክል ነው፤
እነርሱ የተሰበሩት ካለማመን የተነሣ ነው፤
አንተም በእምነት ቆመ ሃል፤ ፍራ እንጂ
ትዕቢተኛ አትሁን። 21እግዚአብሔር በተፈጥሮ
ቅርንጫፎች ለሆኑት ካልራራላቸው፣
ለአንተም አይራራልህምና።
22እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭካኔ
ተመልከት፤ ጭካኔውም በወደቁት ላይ
ነው፤ ቸርነቱ ግን በቸርነቱ ውስጥ እስካለህ
ድረስ ለአንተ ነው፤ ያለዚያ ግን አንተም
ትቈረጣለህ። 23እነርሱም ባለማመናቸው
ጸንተው ባይኖሩ፣ ተመልሰው ይገባሉ፤
እግዚአብሔር መልሶ ሊያስገባቸው ይችላልና።
24የበረሓ ከሆነው የወይራ ዛፍ የተቈረጥህና
ተፈጥሮህ ወዳል ሆነው ወደ መልካሙ ወይራ
የገባህ ከሆንህ፣ በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፎቹ
የሆኑት እነዚህ ወደ ራሳቸው ወይራ
ዛፍ መግባታቸ ውማ ምን ያህል ይሆን?

## እስራኤል ሁሉ ይድናል

25ወንድሞች ሆይ፤ ልባሞች የሆናችሁ
እንዳይመስላችሁ፣ ይህን ምስጢር ሳታውቁ
እንድትቀሩ አልፈልግም፤ የአሕዛብ ሙላት
እስኪገባ ድረስ፣ እስራኤል በከፊል በድንዳኔ
ውስጥ ሀልፋለች። 26ስለዚህ እስራኤል ሁሉ

11፥12 ቍ25
11፥13 ሐሥ9፥15
11፥14 ቍ11፤ ማቴ1፥21፤ ሉቃ2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ ሐሥ4፥12፤ 16፥31፤ ሮሜ10፥19፤ 1ቆሮ1፥21፤ 10፥33፤ 1ተሰ2፥16፤ 1ጢሞ2፥4፤ ቲቶ3፥5
11፥15 ሉቃ15፥24፡32፤ ሮሜ5፥10
11፥16 ዘሌ23፥10፡17፤ ዘኍ15፥18-21
11፥17 ኤር11፥16፤ ዮሐ15፥2፤ ሐሥ2፥39፤ ኤፌ2፥11-13
11፥18 ዮሐ4፥22
11፥20 1ቆሮ10፥12፤ 2ቆሮ1፥24፤ 1ጢሞ6፥17፤ 1ጴጥ1፥17
11፥22 ዮሐ15፥2፤ ሮሜ2፥4፤ 1ቆሮ15፥2፤ ቈላ1፥23፤ ዕብ3፥6
11፥23 2ቆሮ3፥16 11፥24 ኤር11፥16 11፥25 ቍ7፤ ሉቃ21፥24፤ ሮሜ1፥13፤ 9፥18፤ 12፥16፤ 16፥25፤ 1ቆሮ10፥1፤ 12፥1፤ 2ቆሮ1፥8፤ 1ተሰ4፥13
11፥26 ኢሳ45፥17፤ ኤር31፥34

11፥12 **ሙላታቸው፤** የእስራኤል "ሙላታቸው" የሚለው ሐሳብ ብዙ እስራኤላውያን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅና መሲሕ እንደሆነ (ቍ 15 ይመ) እንዲሁም ወደ ዓለምም የላቀ በረከት እንደሚያመጣ ማመናቸውን ሳያመለክት አይቀርም (ኢሳ 11፥10-16 እና ማብ፤ 29፥17-24 እና ማብ ይመ)።

11፥14 **እንዲቀኑ እንዲገፋፉ፤** የአብያት ክርስቲያናት ሁሉ ምኞትና ጸሎት በእስራኤል ያሉ በቅናት ተነሣሥተው ወደ ጌታ እንዲመለሱ የእግዚአብሔር ኀይልና በረከት እንዲያርፍባቸው መሆን አለበት። በክርስቶስ የሚገኘው ድነትና የመንግሥቱ በረከቶች በሕይወታችን ሲታዩ እስራኤላውያን ባርኮቱን እንዲናፍቁ ያደርጋል።

11፥20 **ካለማመን የተነሣ፤** እስራኤል አሁን ለደረሰባት ሁኔታ ዋናው ምክንያት እግዚአብሔር በዘፈቀደ የደነገገበት ሳይሆን ባለማመኗና በክርስቶስ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ በማጣጣሏ ነው (በገጽ 1758 ላይ፣ *"እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

11፥22 **አንተም ትቈረጣለህ፤** ጳውሎስ ለአሕዛብ አማኞች በሙሉ ይኸውም ለአብያተ ክርስቲያናት ማኅበረ ምዕመናን፣ ለቤተ እምነቶች ወይም ኅብረቶች ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤ (1) ማንም ሰው፣ ማንኛውም አገልግሎት፣ ቤተ ክርስቲያን ወይም አብያተ ክርስቲያናት በ"ቸርነቱ" እንዲሁም በአዲስ ኪዳን የሐዋርያት እምነትና የጽድቅ መለኪያ የማይጸና ከሆነ ዕጣ ፈንታው ከእግዚአብሔር መቈረጥ ይሆናል (ቍ 22)።

(2) እግዚአብሔር ለበመፀኛይቱ እስራኤል ካልራራ (ቍ 21) መንገዱን ለሚያጥላሉና በዓለማዊ አካሄድ ለሚመላለሱ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ኅብረቶች እንዴት ይራራሊ (12፥2 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መፍራት (ቍ 20)፣ "የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭካኔ" ልብ ማለት (ቍ 22) እንዲሁም በሐዋርያት እምነትና በአዲስ ኪዳን ልምምድ ለመጽናት አስፈላጊውን ሁሉ ትጋት ማሳየት አለባቸው። የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም አገልግሎት ደፍሮ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ፈጽሞ አልወድቅም ብሎ ሊያስብ አይገባም። ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሰው "እግዚአብሔር ለማንም አያደላምና" (2፥11፤ ራእ 2—3 እና ማብ ይመ)።

11፥25 **የአሕዛብ ሙላት፤** "የአሕዛብ ሙላት" የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ከአሕዛብ መካከል ሰዎችን የመጥራት ዕቅዱ ተፈጻሚ መሆኑን ያመለክታል (ሐሥ 15፥14)። በሌላ አንጻር የአሕዛብ በደል ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበትን ጊዜ ይኸውም በዓለም ያለው ኀጢአት በእግዚአብሔር ላይ ከመጨረሻው የዐመፅ ደረጃ ላይ የሚደርስበትን ጊዜ ሊያመለክትም ይችላል (ከዘፍ 15፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚያን ጊዜ በዓለም ላይ ለመፍረድ ክርስቶስ ይመጣል (ሉቃ 21፥24፡27 ይመ፤ ከዘፍ 6፥5-7፡11-13፤ 18፥20-33፤ 19፥24-25፤ ከሉቃ 17፥26-30 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥26 **እስራኤል ሁሉ፤** "እስራኤል ሁሉ" የሚለው አባባል በእስራኤል ያሉትን አማኞች በሙላ እንደሚመለከት ልብ ልንል ይገባል፤ (1) በክርስቶስ የሚያምኑ አይሁድ ጨለማ በነገሠበት በታላቁ የመከራ ዘመን ቍጥራቸው እጅግ ይበዛል (ዘዳ 4፥30-31፤ ሆሴ 5፥14—6፥3፤ ራእ 7፥1-8)። መከራው የሚያበቃው ክርስቶስ በእስራኤል ላሉ አማኞች አርነት ሲያመጣና የተቀሩትን የማያምኑ አይሁድ ሲያጠፋ ነው (ኢሳ 10፥20 እና ማብ፤ ዘካ 13፥8-9 እና ማብ ይመ)። ዐመፀኞች ሁሉ (የማያምኑ አይሁድ) ይነቀላሉ (ሕዝ 20፥34-44 እና ማብ ይመ)። (2) የሚያምኑት የእስራኤል ትሩፋን

ይድናሉ፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
"አዳኝ ከጽዮን ይወጣል፤
ከያዕቆብም ክፋትን ያስወግዳል።
27 ኃጢአታቸውንም ሳስወግድ፣
ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳኔ ይህ
ነው።"[*]
28 እንደ ምሥራቹ ቃል ለእናንተ ሲባል
ጠላቶች ናቸው፤ እንደ ምርጫ ከሆነ
ግን፣ ለአባቶች ሲባል የተወደዱ ናቸው፤
29 የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም።
30 እናንተም ቀድሞ በእግዚአብሔር የማትታዘዙ
እንደ ነበራችሁ፣ ከእነርሱ አለመታዘዝ
የተነሣ አሁን ምሕረት እንዳገኛችሁ ሁሉ፣
31 እግዚአብሔር ለእናንተ ምሕረት ከማድረጉ
የተነሣ፣ እነርሱም ምሕረት ያገኙ ዘንድ
አሁን[*] የማይታዘዙ ልጆች ሆነዋል፤
32 እግዚአብሔር ለሁሉም ምሕረት ያደርግ ዘንድ
ሰውን ሁሉ ባለመታዘዝ ዘግቶታልና።

## ውዳሴ

33 የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለ
ጠግነት[*] እንዴት ጥልቅ ነው!
ፍርዱ አይመረመርም፤
ለመንገዱም ፈለግ የለውም።
34 "የጌታን ልብ ያወቀ ማነው?
አማካሪውስ የነበረ ማን ነው?"
35 "እግዚአብሔር መልሶ እንዲሰጠው፣
ለእግዚአብሔር ያበደረ ከቶ ማን ነው?"

11፥27 ኢሳ59፥20፡21፤ 27፥9፤ ዕብ8፥10፡12
11፥28 ዘዳ7፥8፤ 10፥15፤ ሮሜ5፥10፤ ሮሜ9፥5
11፥29 ሮሜ8፥28፤ ዕብ7፥21
11፥30 ኤፌ2፥2
11፥32 ሮሜ3፥9
11፥33 መዝ92፥5፤ 139፥6፤ ኢዮ5፥9፤ 11፥7፤ መክ8፥17፤ ኢሳ40፥28፤ ሮሜ2፥4፤ ኤፌ3፥10፤ ቈላ2፥3
11፥34 ኢዮ15፥8፤ ኢሳ40፥13፡14፤ ኤር23፥18፤ 36፥22፤ 1ቆሮ2፥16
11፥35 ኢዮ41፥11፤ 35፥7
11፥36 ሮሜ16፥27፤ 1ቆሮ8፥6፤ 11፥12፤ ኤፌ3፥21፤ ቈላ1፥16፤

36 ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤
ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤
አሜን።

## ሕያው መሥዋዕት

12 እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤
ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን
ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት
አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር
ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ
አእምሮ የምታቀርቡት[*] አምልኮአችሁ
ነው። 2 መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም
የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ
ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ
መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም
አትምሰሉ። 1ቆሮ 2፥6-16
3 እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ በሰጣችሁ

11፥36 1ጢሞ1፥17፤ 1ጴጥ5፥11፤ ዕብ2፥10፤ ይሁ1፥25፤ ራእ5፥13፤ 7፥12
12፥1 ሮሜ6፥13፡16፡19፤ ኤፌ4፥1፤ 1ቆሮ6፥20፤ 1ጴጥ2፥5፡11
12፥2 ኤፌ4፥23፤ 5፥17፤ 1ቆሮ1፥20፤ 2ቆሮ10፥2፤ 1ጢሞ5፥4፤ 1ጴጥ1፥14፤ 1ዮሐ2፥15
12፥3 ሮሜ15፥15፤ 1ቆሮ15፥10፤ ገላ2፥9፤ ኤፌ3፥7፤ 4፥7፤ 1ጴጥ4፥10፡11

*[*] 11፥27 ወይም ይህ ይሆናል*
*[*] 11፥31 አንዳድ ቅጆች አሁን የሚለው ቃል የላቸውም*
*[*] 11፥33 ወይም ባለጠግነቱ፣ ጥበብና እውቀቱ*
*[*] 12፥1 ወይም መንፈሳዊ*

(የመጨረሻውን ዘመን የሚያልፉ) እና የኋለኛው ትውልድ ታማኞች በአንድነት "እስራኤል ሁሉ" በመባል ይታወቃሉ (ሕዝ 37፥12-14 እና ማብ ይመ)።

**11፥29 የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ፤** እነዚህ ቃላት በምዕ 9፥4-5 እና በ11፥26 ላይ የተጠቀሱትን የእስራኤልን በረከቶች ያመለክታሉ። በሙዱ በግልጽ የሚያመለክተው እስራኤልንና እግዚአብሔር ለእርሷ ያለውን ዐላማ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ጋር የተያያዘውን መንፈሳዊ ስጦታ ወይም የአገልግሎት ጥሪ አይደለም (ከ12፥6-8፤ ከ1ቆሮ 12 ጋር ያነጻጽሩ)። አንድ ሰው ለመጋቢነት ወይም ለሽማግሌነት መጠራቱ፣ መሾምና በቤታው መጽናት የሚገባው በግል የባሕርይ ብቃቱና በመንፈሳዊ ታሪኩ መሆን አለበት (በገጽ 1925 ላይ፣ *"የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**12፥1 ሰውነታችሁን ... ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ፤** አማኞች እግዚአብሔርን በፍቅር፣ በመስጠት፣ በምስጋናና በቅድስና ጌታን ደስ ለማሰኘት ለጥሪው ሰውነታቸውን ለማቅረብ ፍጹም መሻት ሊኖራቸው ይገባል፦ (1) ትልቁ መሻታችን በቅድስና ሕይወት ለመኖርና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት መሆን ይኖርበታል። ይህም ራሳችንን ከዓለም እንድንለይና ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ የሚጠይቅ ነው (ቍ 2)። ለእግዚአብሔር ተለይተን ልንኖር፣ እርሱንም ልናመልከው፣ ልንታዘዘው፣ ስለ ኃጢአትና ጽድቅ ያለውን አቋሙን ልናንፀባርቅ፣ ክፉውን ልንጠላና ልንቃወም፣ ለሌሎች ልግስናን ልናደርግ፣ ክርስቶስን ልንመስል፣ ልንከተለው፣ ልናገለግለው፣ በመንፈስ ልንመላለስና በመንፈስ የተሞላን ልንሆን ይገባል። (2) ሰውነታችንን ለኃጢአት እንደሞተና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አድርገን ለእግዚአብሔር ማቅረብ አለብን (የሚቀጥለውን ማብ ይመ፤ ከ1ቆሮ 6፥15፡19 ጋር ያነጻጽሩ)።

**12፥2 ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፤** እዚህ ጳውሎስ ይህን ሲል ብዙ ነገሮችን ያመለክታል፤ (1) ይህ ዓለም ክፉ እንደሆነና (ሐሥ 2፥40፤ ገላ 1፥4) በሰይጣን አገዛዝ ሥር እንዳለ (ዮሐ 12፥31፤ 1ዮሐ 5፥19) መገንዘብ ይኖርብናል፤ በገጽ 2022 ላይ፣ *"ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ስለ ክርስቶስ ብለን የዘላለሙን እውነትና የእግዚአብሔርን ቃል የጽድቅ መስፈርቶች በማወጅ በዚህ ዓለም ላይ የተንሰራፋውንና የገነነውን መንፈስ መዋጋት አለብን (1ቆሮ 1፥17-24)።

(3) ክፉ የሆነውን በመጥላት ጽድቅ የሆነውን መውደድ ያለብን ሲሆን (ቍ 9፤ 1ዮሐ 2፥15-17፤ ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ) ለስስት፣ ለራስ ወዳድነት፣ ለግል ጥቅም አሳዳጅነት፣ ለሥጋዊ አስተሳሰብ፣ ሥልጣን ለማግኘት ፖለቲካዊ አድማ ለማካሄድ፣ ለቅናት፣ ለጥላቻ፣ ለበቀል፣ ለርኩሰት፣ ለጸያፍ ንግግር፣ ለነውረኛ ተዝናኖት፣ ለፈታኝና ሳሉተገባ አለባበስ፣ ለኢግብረገባዊነት፣ ሱስ በሚያሲዝ ዕፅ ለመጠመድ፣ የሚያሰክር መጠጥና ዓለማዊ ወዳጆችን ለማብዛት እና ለመሳሰሉት ቤተ ክርስቲያንን ለከበቡ ጥፋቶች መገዛት የለብንም።

(4) ቃሉን በማንበብና የጸሎት ጊዜ በመውሰድ (መዝ 119፥11፡148፤ ዮሐ 8፥31-32፤ 15፥7) አእምሮአችንን ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር ማስማማት ይኖርብናል (1ቆሮ 2፥16፤ ፊል 2፥5)። ዓላማችንንና ጉጉታችንን ሁሉ በዚህ ክፉ፣ ጊዜአዊና ተለዋዋጭ ዘመን ሳይሆን በሰማያዊውና በዘላለማዊው እውነት መመሥረት ይኖርብታል።

እምነት መጠን ራሳችሁን በአግባቡ መዝኑ
እንጂ፣ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ
አድርጋችሁ እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያ
ንዳንዳችሁን እመክራለሁ። 4እያንዳንዳችን
በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣
እነዚህም ብልቶች አንድ ዐይነት ተግባር
እንደ ሌላቸው ሁሉ፣ 5እንዲሁም እኛ ብዙ
ዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን።
እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን። 6እንደ
ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፤
ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር
ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን* ይናገር።
7ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም
ከሆነ ያስተምር፤ 8መምከር ከሆነ ይምከር፤
ለሌላቸው መለገስ ከሆነም አብዝቶ ይለግስ፤
ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር፤
ሮሜ 15፥19 ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር።

## ፍቅር

9ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፤ ክፉ
የሆነውን ሁሉ ተጸየፉ፤ በጎ ከሆነው ነገር
ጋር ተቈራኙ። 10እርስ በርሳችሁ በወንድ
ማማች መዋደድ እጥብቃችሁ ተዋደዱ፤
አንዱ ሌላውን ከራሱ በማስበለጥ እርስ በር
ሳችሁ ተከባበሩ። 11ጌታን ለማገልገል በመ
ንፈስ የጋላችሁ ሁኑ እንጂ ከዚህ ትጋት ወደ
ኋላ አትበሉ። 12በተስፋ ደስተኞች ሁኑ፤
በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ። 13ችግረኛ
ለሆኑ ቅዱሳን ካላችሁ አካፍሉ፤ እንግዶችን
ተቀበሉ።

14የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፤ መርቁ
እንጂ አትርገሙ። 15ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ
ይበላችሁ፤ ከሚያዝኑም ጋር እዘኑ። 16እርስ
በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ። ዝቅተኛ ኑሮ*
ውስጥ ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ
እንጂ አትኵራሩ፤ በራሳችሁም አትመኩ።

17ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤ በሰው
ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ።

12፥4 1ቆሮ12፥12-14፤ ኤፌ4፥16 12፥5 1ቆሮ6፥15፤ 10፥17፤ 12፥12፡20፡27፤ ኤፌ2፥16፤ 4፥4፡25፤ 5፥30፤ ቈላ3፥15 12፥6 1ቆሮ7፥7፤ 12፥4፡8-10፤ ኤፌ4፥11፤ 1ጴጥ4፥10፡11 12፥7 ኤፌ4፥11 12፥8 ሐሥ11፥23፤ 13፥15፤ 15፥32፤ 2ቆሮ8፥2፤ 9፥5-13 12፥9 መዝ97፥10፤ አሞ5፥15፤ 2ቆሮ6፥6፤ 1ተሰ 5፥21፡22፤ 1ጢሞ1፥5 12፥10 መዝ133፥1፤ ፊል2፥3፤ 1ተሰ4፥9፤ ዕብ13፥1፤ 1ጴጥ1፥22

12፥11 ሐሥ18፥25 12፥12 ሉቃ18፥1፤ ሮሜ5፥2፤ ዕብ10፥32፡36 12፥13 2ነገ4፥10፤ ኢዮ31፥32፤ ሐሥ24፥17፤ 1ጢሞ3፥2፤ 5፥10፤ ዕብ13፥2፤ 1ጴጥ4፥9 12፥14 ማቴ5፥44 12፥15 ኢዮ30፥25 12፥16 ምሳ3፥7፤ ኢሳ5፥21፤ ኤር45፥5፤ መዝ131፥1፤ ሮሜ11፥25፤ 15፥5 12፥17 ምሳ19፤ ምሳ20፥22፤ 24፥29፤ 2ቆሮ8፥21

*12፥6 ወይም እንደ አገልጋይ ተግባር
*12፥16 ወይም ዝቅተኛ ሥራ ለመሥራት ፍቀዱ

**12፥6 እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች፤** ጳውሎስ የጸጋ ስጦታዎች (በግሪኩ ካሪዝማታ) ተብለው ሊጠሩ የሚችሉትን ይዘረዝራል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲታነጽና የእግዚአብሔር ፍቅር ለሌሎች እንዲገለጽ (1ቆሮ 12፥1 እና ማብ ይመ፤ 14፥12፡26፤ 1ጴጥ 4፥10) *መንፈስ ቅዱስ በማኅበረ ምዕመናን ውስጥ ላሉ ግለሰቦች የሚሰጠው የውስጥ መሻት ወይም ባሕርያት* (ፊል 2፥13)፣ ችሎታ ወይም ዐቅም ናቸው:: እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ ከእነዚህ አንዱ ስጦታ አለው (1ቆሮ 12፥11፤ 1ጴጥ 4፥10):: ይሁንና፣ አንድ ሰው በዋናነት የተሰጠ ው ስጦታ ቢኖርም፣ አስፈላጊ ሲሆን ውስጡ ሊገለጡ የሚችሉ ሌሎች ስጦታዎችንም ችላ ማለት የለበትም:: ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚዘረዝራቸው ሰባት ስጦታዎች ለአብነት የተጠቀሱ ናቸው እንጂ ሁሉም አይደሉም (የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በተመለከተ የተብራራ ሐሳብ ለማግኘት 1ቆሮ 12-14፤ ኤፌ 4፥11 ይመ)::

**12፥6 ትንቢት መናገር፤** ስለ ትንቢት ስጦታ በይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1800 ላይ፣ *«ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች»*፣ በገጽ 1866 ላይ፣ *«የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች»* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመልከቱ::

**12፥7 ማገልገል ... ማስተማርም፤** (1) *«ማገልገል»*፣ የቤተ ክርስቲያን አባላትና መሪዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ኀላፊነት መወጣት ይችሉ ዘንድ እገዛን የሚያገኙበት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሻት፣ ችሎታና ኀይል ነው (ከሐሥ 6፥2-3 ጋር ያነጻጽሩ):: (2) *«ማስተማር»*፣ የእግዚአብሔርን ቃል መርምሮ ለማጥናት፣ ለማብራራት፣ ለመጠበቅና ሌሎች በጸጋና ጌታን በመምሰል እንዲያድጉ ለመግለጽ ከእግዚአብሔር የሚሰጥን መሻት፣ ችሎታና ኀይል ነው (1ቆሮ 2፥10-16፤ 1ጢሞ 4፥16፤ 6፥3፤ 2ጢሞ 4፥1-2፤ 2ጢሞ 2፥2 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1866 ላይ፣ *«የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች»*፣ በገጽ 1937 ላይ፣ *«የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና»* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)::

**12፥8 መምከር ... መለገስ ... ማስተዳደር ... ምሕረት፤** (1) *«መምከር»*፣ የእግዚአብሔር ቃል የሰሚዎችን ልብ፡ ሕሊናና ፈቃድ ይነካ ዘንድ እንዲሁም እምነትን በመቀስቀስ ለክርስቶስ መስጠትን፡ ከዓለም ደግሞ ፈጽሞ መለየትን ይፈጥር ዘንድ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሻት፣ ችሎታና ኀይል ነው (ሐሥ 11፥23፤ 14፥22፤ 15፥30-32፤ 16፥40፤ 1ቆሮ 14፥3፤ 1ተሰ 5፥14-22፤ ዕብ 10፥24-25)::

(2) *«መለገስ»*፣ ለኑሮ አስፈላጊ ከሆኑት መሠረታዊ ፍላጎቶች በላይ ያለው ሰው ወይም ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መሥዋዕት በማድረግ ለእግዚአብሔር ሥራና ሕዝብ እንዲሁ እንዲለግስ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሻት፣ ችሎታና ኀይል ነው (2ቆሮ 8፥1-8፤ ኤፌ 4፥28)::

(3) *«ማስተዳደር»*፣ የቤተ ክርስቲያንን የተለያዩ ተግባራት ለመምራትና ለመጠበቅ ለሁሉም መንፈሳዊ ጥቅም ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሻት፣ ችሎታና ኀይል ነው (ኤፌ 4፥11-12፤ 1ጢሞ 3፥1-7፤ ዕብ 13፥7፡17፡24፤ በገጽ 1866 ላይ፡ *«የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(4) *«ምሕረት»*፣ በችግር ወይም በሐዘን ያሉትን ለማገዝና ለማጽናናት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሻት፣ ችሎታና ኀይል ነው (ከኤፌ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

**12፥9 ክፉ የሆነውን ሁሉ ተጸየፉ፤** ዕብ 1፥9 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**12፥10 እርስ በርሳችሁ ... አጥብቃችሁ ተዋደዱ፤** በእምነት ራሳቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጡ ሁሉ እንደ ወንድምና እኅት እርስ በርስ በእውነተኛ፣ ግርና የተፈተነ ፍቅር መተሳሰር አለባቸው (1ተሰ 4፥9-10):: ስለ ወንድሞችና እኅቶች ደህንነት፣ ፍላጎትና መንፈሳዊ ሁኔታ በማሰብ አብረናቸው ልንሆን፣ በሐዘንና በችግራቸው ወቅት ልንረዳቸው ይገባል:: በሌሎች አማኞች ውስጥ ያለውን መልካም ስጦታ ዋጋ በመስጠት እርስ በርስ ልንከባበር ያስፈልጋል (ዮሐ 13፥34-35 እና ማብራሪያውን ይመ)::

18ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር
በሰላም ኑሩ። 19ወዳጆቼ ሆይ፤ ለእግዚአብሔር
ቊጣ ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤ "በቀል
የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" ይላል
ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። 20ይልቁንስ፣
"ጠላትህ ቢራብ አብላው፤
ቢጠማም አጠጣው።
ይህን በማድረግህም የእሳት ፍም
በራሱ ላይ ትከምራለህ።"
21ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ
አትሸነፍ።

## ባለ ሥልጣናትን መታዘዝ

13 ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት
ሹማምት መገዛት ይገባዋል፤
ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤
ያሉትም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር
የተሾሙ ናቸው። 2ስለዚህ፣ በባለ ሥልጣን
ላይ የሚያምፅ በእግዚአብሔር ሥርዐት ላይ
ማመፁ ነው፤ ይህን የሚያደርጉትም
በራሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣሉ። 3ገገሮች
ክፉ ለሚሠሩ እንጂ መልካም ለሚያደርጉ
የሚያስፈሩ አይ ደሉምና። ባለ ሥልጣንን
እንዳትፈራ ትፈልጋለህን? እንግዲያስ
መልካሙን አድርግ፤ እርሱም ያመሰግንሃል፤
4እርሱ ለአንተ መልካሙን ለማድረግ
የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። ነገር ግን ክፉ
ብታደርግ ፍራ፤ ምክንያቱም ሰይፉን በከንቱ
አልታጠቀም፤ ክፉ የሚያደርገውን ለመቅጣት

12፥18 ማር9፥50፤ ሮሜ14፥19
12፥19 ቍ17፤ ዘፍ50፥19፤ ዘሌ19፥18፤ ዘዳ32፥35፤ 1ሳሙ26፥10፤ ምሳ20፥22፤ 24፥29፤ 94፥1፤ ኤር51፥36
12፥20 ዘፀ23፥4፤ ምሳ25፥21፥22፤ ማቴ5፥44፤ ሉቃ6፥27
13፥1 ዳን2፥21፤ 4፥17፤ ዮሐ19፥11፤ ቲቶ3፥1፤ 1ጴጥ2፥13፥14
13፥2 ዘፀ16፥8
13፥3 1ጴጥ2፥14
13፥4 1ተሰ4፥6
13፥5 ምሳ24፥21፥22
13፥6 ማቴ22፥17
13፥7 ማቴ7፥25፤ 22፥17፥21፤ ሉቃ23፥2
13፥8 ቍ10፤ ማቴ5፥43፤ ዮሐ13፥34፤ ቈላ3፥14
13፥9 ዘፀ20፥13-15፥17፤ ዘዳ5፥17-19፥21፤ ዘሌ19፥18፤

የቍጣ መሣሪያ የሆነ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ
ነው። 5ስለዚ ህም ቅጣትን በመፍራት ብቻ
ሳይሆን፣ ለኅሊና ሲባል ለባለ ሥልጣናት
መገዛት ተገቢ ነው።
6ግብር የምትከፍሉትም ደግሞ ለዚህ
ነው፤ ባለ ሥልጣናቱ፣ በዚሁ ተግባር ላይ
የተሠማሩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፤
7ለእ ያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ፤ ግብር
ከሆነ ግብርን፣ ቀረጥ ከሆነም ቀረጥን፣
መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር
ለሚገባውም ክብርን ስጡ።

## ጊዜው ተቃርቦአልና ተዋደዱ

8እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር የማንም
ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ባልንጀራውን የሚወድ
እርሱ ሕግን ፈጽሞአልና። 9"አታመንዝር"፣
"አትግደል"፣ "አትስረቅ"፣ "አትመኝ"
የሚሉ ትና ሌሎችም ትእዛዛት ቢኖሩም፣
"ባልን ጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ"
በሚ ለው በዚህ በአንድ ሕግ ተጠቃለዋል።
10ፍቅር በባልንጀራው ላይ ክፉ አያደርግም፤
ስለዚህ ፍቅር የሕግ መፈጸሚያ ነው።
11ዘመኑን በማስተዋል ይህን አድርጉ፤
ከእንቅልፋችሁ የምትነቁበት ጊዜ አሁን
ነው፤ መዳናችን መጀመሪያ ካመንበት ጊዜ
ይልቅ አሁን ወደ እኛ ቀርቦአልና። 12ሌሊቱ

13፥9 ማቴ5፥43፤ 7፥12 13፥10 ቍ8፥9 13፥11 1ቆሮ7፥29-31፤ 10፥11፤ ኤፌ5፥14፤ 1ተሰ5፥5፥6፤ ያዕ5፥8፤ 1ጴጥ4፥7፤ 1ዮሐ2፥18፤ ራእ22፥10 13፥12 ኤፌ5፥11፤ 6፥11፥13፤ 1ተሰ5፥8፤ ዕብ10፥25፤ 1ዮሐ2፥8

**13፥1 በሥልጣን ላሉት ሹሞች መገዛት፤** *መንግሥት እንደ አንድ ተቋም በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመሠረትና የሚቋቋም ስለሆነ ክርስቲያኖች ይታዘዙት ዘንድ እግዚአብሔር አዟል። እግዚአብሔር መንግሥትን ያቋቋመበት ምክንያት የኀጢአታዊ ተፈጥሮ ውጤት ከሆኑት ሕገ ወጥነትና ሁከት እንጠበቅ ዘንድ ገደብ ለማበጀት ነው። (1) ሕይወት በእግዚአብሔር ሕግ ሥር እንደሆነ ሁሉ የመንግሥት አስተዳዳርም እንደዚሁ ነው። (2) እግዚአብሔር መንግሥትን የሚሾመው የፍትሕ ወኪል እንዲሆን፣ ወንጀለኛን በመቅጣት ክፉን እንዲገታና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን መልካም ሰው እንዲጠብቅ ነው (ቍ 3-4፤ 1ጴጥ 2፥13-17)። (3) ጳውሎስ ስለ መንግሥት የተናገረው መሆን ካለበት አንጻር ነው። መንግሥት ተገቢ ተግባሩን ሳያከናውን ሲቀር ግን ከእግዚአብሔር አይደለም፤ የጌታንም ሐሳብ አይፈጽምም። ለምሳሌም፤ መንግሥት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረንን ተግባር እንዲደረግ ቢያዝ ክርስቲያኖች ከሰው ይልቅ መታዘዝ የሚኖርባቸው እግዚአብሔርን ነው (ሐሥ 5፥29፤ ከዳን 3፥16-18፤ 6፥6-10 ጋር ያነጻጽሩ)። (4) በሥልጣን ላይ ላሉት ሹሞች መጸለይ የአማኞች ሁሉ ግዴታ ነው (1ጢሞ 2፥1-2)።*

**13፥4 ሰይፉን፤** *ሰይፍ ብዙውን ጊዜ የሞት ቅጣት መፈጸሚያ መሣሪያ ነው (ማቴ 26፥52፤ ሉቃ 21፥24፤ ሐሥ 12፥2፤ 16፥27፤ ዕብ 11፥34፤ ራእ 13፥10)። እግዚአብሔር አስከፊ ወንጀል የሚፈጽሙ አደገኛ ወንጀለኞች እንዲገደሉ አዟል (ዘፍ 9፥6፤ ዘኍ 35፥31፥33)።*

**13፥8 የማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፤** *አማኞች ያልተከፈለ ዕዳ ሊኖርባቸው አይገባም፤ እንዲህ ስለተባለ ግን በጣም ሲያስፈልገን ከሌሎች መበደር አንችልም ማለት አይደለም (ከዘፀ 22፥25፤ ከመዝ 37፥26፤ ከማቴ 5፥42፤ ከሉቃ 6፥35 ጋር ያነጻጽሩ)። የመልእክቱ ሐሳብ የሚቃወመው አስፈላጊ ላልሆኑ ነገሮች ዕዳ ውስጥ መግባትንና ዕዳን ለመክፈል ቸልተኛ መሆንን ነው (ከመዝ 37፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። ነጻ ልንሆንበት የማንችለው ብቸኛ ዕዳ እርስ በርስ መዋደዳችን ነው።*

**13፥10 ፍቅር በባልንጀራው ላይ ክፉ አያደርግም፤** *በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልክ የቀረቡትን ትእዛዞች (12፥9-21፤ 1ቆሮ 13፥4፥6-7) በመፈጸም ፍቅር ይገለጣል። እዚህ ላይ የሰፈሩት ትእዛዛት ሁሉ አሉታዊ መልክ አላቸው (ቍ 9፤ ከ1ቆሮ 13፥4-6 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) ፍቅር አወንታዊ ነው፤ ይሁን እንጂ ፍቅር ሰው ኀጢአትን፣ ራስ ወዳድነትንና ጭካኔን እንዲያጣጥል ስለሚፈልግ ደግም አሉታዊ ገጽታ አለው። ከበጎነት ይልቅ ኀጢአት በቀላሉ ከተፈጥሮአችን የሚመጣ ስለሆነ ከዐሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ስምንቱ ክልካይ ናቸው። የክርስቲያናዊ ፍቅር የመጀመሪያው ማስረጃ ከኀጢአት እንዲሁም በሌሎች ላይ ጕዳትና ሐዘን ከሚያመጡ ነገሮች መለየት ነው። (2) ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በአወንታዊ መልክ ብቻ መገለጽ አለበት የሚለው አመለካከት፣ የኀጢአተኛን ልቅ ምኞት ከሚገታ ክልከላ ኅብረተሰብን ነጻ ለማድረግ የሚፈልግ የተዛባ አስተሳሰብ ነው (ገላ 5፥19-21)።*

**13፥12 ሌሊቱ ሊያልፍ ... ነው፤** *ጳውሎስ ጌታ የታመኑትን የቤቱን ሰዎች ወደ ሰማይ ለመውሰድ ዳግም እንዲመጣ አምኖ የነበር ሲሆን (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1907 ላይ፣ «ንጥቀት» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ ይህም በእርሱ ትውልድ ዘመን ሊፈጸም እንደሚችል ተስፋ*

ሊያልፍ፤ ቀኑም ሊጀምር ነው። ስለዚህ
የጨለማን ሥራ ጥለን፤ የብርሃንን ጦር ዕቃ
እንልበስ። [13]በቀን እንደምንመላለስ በአግባብ
እንመላለስ። በጭፈራና በስካር አይሁን፤
በዝሙት ትና በመዳራት አይሁን፤ በክርክርና
በቅናም አይሁን። [14]ይልቁንም ጌታ ኢየሱስ
ገላ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም ይፈጽም
5፥13- ዘንድ ለሥጋ በሐሳባችሁ አትመቻቹለት።
18

## በወንድምህ ላይ አትፍረድ

**14** በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው፣
አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ
በአቋሙ ሳትፈርዱበት ተቀበሉት። [2]የአንድ
ሰው እምነቱ ማንኛውንም ነገር እንዲበላ
ይፈቅድለታል፤ በእምነቱ ያልጠነከረው
ሌላው ሰው ግን አትክልት ብቻ ይበላል።
[3]ማንኛውንም የሚበላ የማይበላውን
አይናቅ፤ የማይበላውም፣ የሚበላውን
አይኰንን፤ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና።
[4]ሌላውን በሚያገለግል ላይ የምትፈርድ
አንተ ማን ነህ? እርሱ ቢወድቅ ወይም
ቢቆም ለጌታው ነው፤ ጌታ ሊያቆመው
ስለሚችልም ይቆማል።
[5]አንድ ሰው አንዱን ቀን ከሌላው የተሻለ
ቅዱስ አድርጎ ይቈጥራል፤ ሌላው ደግሞ
ቀኖች ሁሉ እኩል እንደ ሆኑ ያስባል። እያ
ንዳንዱ የራሱን ውሳኔ ልብ ብሎ ይወስን።
[6]አንድን ቀን ከሌላው የተለየ አድርጎ የሚ
ያስብ ሰው፣ እንዲህ የሚያደርገው ለጌታ
ብሎ ነው፤ ሥጋ የሚበላውም ለጌታ ብሎ
ይበ ላል፤ እግዚአብሔር ምስጋና ያቀርባልና።
የማይበላም ለጌታ ሲል አይበላም፤
እግዚአብሔርም ምስጋና ያቀርባል። [7]ከእኛ
ማንም ለራሱ የሚኖር፣ ለራሱም የሚሞት
የለምና። [8]ብንኖር ለጌታ እንኖራለን፤
ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን፤ ስለዚህ
ብንኖርም ብንሞትም የጌታ ነን።
[9]ስለዚሁ፣ የሙታንና የሕያዋን ጌታ ይሆን
ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአል፤ በሕይወትም
ተነሥቶአል። [10]ታዲያ አንተ በወንድምህ
ላይ ለምን ትፈርዳለህ? ለምንስ ወንድምህን
ትንቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ
ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ [11]እንዲህ
ተብሎ ተጽፎአል፤
" 'እኔ ሕያው ነኝና'፤
'ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤
ምላስም ሁሉ በእግዚአብሔር ይመሰክራል' "
ይላል ጌታ።
[12]ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን
ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።
[13]ስለዚህ እርስ በርሳችን፣ አንዱ በሌላው
ላይ ከመፍረድ እንቈጠብ፤ በዚህ ፈንታ ግን
በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ
ወይም ወጥመድ እንዳታስቀምጥ ቊርጥ
ሐሳብ አድርግ። [14]በጌታ በኢየሱስ ሆኜ
በራሱ ንጹሕ ያልሆነ ምንም ምግብ[ለ] እንደ
ሌለ ተረድቻለሁ፤ ነገር ግን አንድ ሰው አን
ድን ነገር ንጹሕ እንዳልሆነ የሚቈጥር ከሆነ፣
ያ ነገር ለእርሱ ንጹሕ አይደለም። [15]ወንድ
ምህ በምትበላው ምግብ የሚያዝን ከሆነ፣
በፍቅር አልተመላለስህም፤ ክርስቶስ የሞተ
ለትን ወንድምህን በመብልህ አታጥፋው።
[16]መልካም ነው ብለህ የምታስበው ነገር ክፉ
ተብሎ እንዲነቀፍ አታድርግ። [17]የእግዚአብሔር
መንግሥት ጽድቅና ሰላም፣ በመንፈስ

13፥13 ሉቃ21፥34፤ ገላ5፥20፡21፤ ኤፌ5፥18፤ 1ጴጥ4፥3
13፥14 ገላ3፥27፤ 5፥24፤ ኤፌ4፥24፤ ቈላ3፥10፡12
14፥1 ሮሜ15፥1፤ 1ቆሮ8፥9-12፤ 9፥22
14፥2 ቍ 14
14፥3 ቍ 10፡13፤ ሉቃ18፥9፤ ቈላ2፥16
14፥4 ማቴ7፥1
14፥5 ገላ4፥10፤ ቈላ2፥16
14፥6 ማቴ14፥19፤ 1ቆሮ10፥30፡31፤ 1ጢሞ4፥3፡4
14፥7 2ቆሮ5፥15፤ ገላ2፥20
14፥8 ፊል1፥20
14፥9 ሐሥ10፥42፤ 2ቆሮ5፥15፤ ራእ1፥18፤ 2፥8
14፥10 ቍ 3፤ ማቴ7፥1፤ 2ቆሮ5፥10
14፥11 ኢሳ49፥18፤ 45፥23፤ ፊል2፥10፡11
14፥12 ማቴ12፥36፤ 1ጴጥ4፥5
14፥13 ቍ 1፤ ማቴ7፥1፤ 2ቆሮ6፥3
14፥14 ቍ 20፤ ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ8፥7
14፥15 ቍ 20 ኤፌ5፥2፤ 1ቆሮ8፥11 14፥16 1ቆሮ10፥30
14፥17 ኢሳ32፥17፤ ሮሜ15፥13፤ 1ቆሮ8፥8፤ ገላ5፥22

[ሀ] 13፥14 ወይም ለኀጢአተኛ ተፈጥሮ
[ለ] 14፥14 ወይም ምንም ነገር

አድርጎ ነበር:: ክርስቶስ የታመኑት ይመጣል ብለው በማይጠረጥሩበት ሰዓት እንደሚመጣ አስጠንቅቋል (ማቴ 24፥42፡44 እና ማብ ይመ):: በዚህም ምክንያት፣ የእግዚአብሔር እጆች ሁልጊዜ በመንፈስ የተዘጋጁና «የጨለማን ሥራ የጣሉ» መሆን አለባቸው (ሉቃ 12፥35 እና ማብ ይመ)::

**13፥14 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤** ሕይወቱን የኑሮአችን መመሪያ አድርገን እንድንከተል፥ መርሖቹን የራሳችን እንድናደርግ፣ ትእዛዞቹን እንድንከተልና እርሱን እንድንመስል ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን አለብን፡ ይህም ርኵሰትንና የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራን ሙሉ በሙሉ ማስወገድን የሚጠይቅ ነው (ከገላ 15፥19-21 ጋር ያነጻጽሩ)::

**14፥2 ማንኛውንም ነገር እንዲበላ ... አትክልት ብቻ ይበላል፤** ብሮም የነበሩ በርካታ አማኞች አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በሐሳብ ተከፋፍለው ነበር፤ አንዳንዶች አትክልትን ብቻ ሲበሉ ሌሎች ደግሞ ሥጋን ጨምሮ አትክልትንና ሁሉን ዐይነት ምግብ ይበሉ ነበር:: ጳውሎስ መብላት በራሱ የሥነ ምግባር ጉዳይ እንዳልሆነ በመግለጽ ስለመብል የሚሰጠው አስተያየት ግን ሌላውን ያለአግባብ ለመኰነን ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አሳይቷል::

**14፥5 አንዱን ቀን ከሌላው የተሻለ ቅዱስ አድርጎ ይቈጥራል፤** ይህ ምናልባት የብሉይ ኪዳን የበዓላት ቀን ሥርዐትን ሳይመለከት አይቀርም:: አንዳንድ ክርስቲያኖች የተቀደሱት ቀናት አስፈላጊ እንደሆኑ ሲያምኑ፣ ሌሎች በርከት ያሉት ደግሞ ችላ ብለዋቸው ነበር:: ጳውሎስ ለዚህ ጥያቄ ሲመልስ እግዚአብሔር ከሰባት ቀናት መካከል ለዕረፍትና ለአምልኮ አንድ ቀን የመረጠበትን መርሕ አልሻረም (ማቴ 12፥1 እና ማብ ይመ):: ከሰባቱ ቀናት መካከል አንዱ የዕረፍት ቀን እንዲሆን የወሰነው እግዚአብሔር ራሱ ነው (ዘፍ 2፥2-3 ይመ፤ ከዘፀ 20፥11፤ 31፥17፤ ከኢሳ 58፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ):: በአዲስ ኪዳን የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከኢየሱስ ትንሣኤ የተነሣ የተለየ ትርጕም አለው (ሐሥ 20፥7፤ 1ቆሮ 16፥2፤ ራእ 1፥10)::

**14፥13 ከመፍረድ እንቈጠብ፤** በማይረባ ነገር አንዱ በሌላው ላይ ከመፍረድ መቈጠብ ያለብን ቢሆንም፣ አማኞች እምነትን፣ አስተምህሮንና ምግባርን በተመለከተ ክርስቶስን ወደ መምሰልና ወደ ቅድስና እንድንመጣ እርስ በርስ መበረታታት ለአብን (ዕብ 10፥24):: ይህም በቅንነት መፈተንን (1ተሰ 5፥21፤ 1ዮሐ 4፥1)፣ በፍቅርና በትሕትና እርስ በርስ መተራረምንና ተግሣጽን መቀባበልን (ሉቃ 17፥3) እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የቤተ ክርስቲያንን የእርምት እርምጃ መቀበልን የሚያቅፍ ነው (ከ1ቆሮ 5፥12-13፤ ከ2ተሰ 3፥6፡14፤ ከ1ጢሞ 5፥20-21፤ ከ2ጢሞ 2፥24-26፤ 4፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

ቅዱስም የሆነ ሐሤት ነው እንጂ፣ የመብልና
የመጠጥ ጉዳይ አይደለም፤ [18]በዚህ ሁኔታ
ክር ስቶስን የሚያገለግል እግዚአብሔርን ደስ
ያሰኛልና፤ በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው።
[19]ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ
በርሳችንም የምንተናነጽበትን ማንኛውንም
ጥረት እናድርግ። [20]ለምግብ ስትል
የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ። ሁሉ ንጹሕ
ነው፤ ነገር ግን ለሌላው ሰው የመሰናከያ
ምክንያት የሚሆ ነውን መብላት ስሕተት
ነው። [21]ለወንድ ምህ መሰናከል ምክንያት
የሚሆነውን ሥጋን አለመብላት፣ ወይንን
አለ መጠጣት፣ ወይም አንዳች ነገርን
አለማድረግ መልካም ነው።
[22]እንግዲያስ ስለ እነዚህ ነገሮች ያለህ እም
ነት በአንተና በእግዚአብሔር መካከል የተጠበቀ
ይሁን፤ ትክክል ነው ብሎ በተቀበለው
ነገር ራሱን የማይኰንን የተባረከ ሰው
ነው። [23]ነገር ግን የሚጠራጠር ሰው ቢበላ
በእምነት ስላልሆነ፣ ተፈርዶበታል፤ በእም
ነት ያልተደረገ ሁሉ ኀጢአት ነውና።
15 እኛ ብርቱዎች የሆንን፣ የደካሞችን
ጕድለት መሸከም እንጂ ራሳችንን
ማስደሰት የለብንም። [2]እያንዳንዳችን
ባልንጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም
ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ
ይገባናል፤
[3]ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር
ግን፣ "አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ
ላይ ደረሰብኝ" ተብሎ እንደ ተጻፈው
ሆነበት። [4]በጽናትና ቅዱሳት መጻሕፍት
በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ እንዲኖረን፣
ቀድም ብሎ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን
ተጽፎአልና።
[5]በርታትንና መጽናናትን የሚሰጥ
አምላክ፣ ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ፣
በመካከላችሁ የአንድነትን መንፈስ
ይስጣችሁ፤ [6]ይኸውም በአንድ ልብና በአንድ
አፍ ሆናችሁ፣ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
አምላክና አባት ታከብሩ ዘንድ ነው።
[7]እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሆን
ዘንድ ክርስቶስ እንደ ተቀበላችሁ፣ እርስ
በርሳችሁ ተቀባበሉ። [8]ለአባቶች የተሰጠውን
የተስፋ ቃል ያጸና ዘንድ ስለ እግዚአብሔር እውነት
ሲል ክርስቶስ የአይሁድ[T] አገልጋይ እንደ
ሆነ እነግራችኋለሁና፤ [9]እንዲሁም አሕዛብ
እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ ያመሰግኑት ዘንድ
ነው፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
"ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ለስምህም እዘምራለሁ።"
[10]ደግሞም፣
"አሕዛብ ሆይ፤ ከሕዝቡ ጋር ደስ
ይበላችሁ" ይላል።
[11]እንደ ገናም፣
"አሕዛብም ሁላችሁ ጌታን
አመስግኑ፤
ሕዝቦች ሁሉ ወድሱት" ይላል። ኢሳ 11፥3-6
[12]ኢሳይያስም እንዲሁ፣
"በሕዝቦች ሁሉ ላይ የሚነግሠው፣
የእሴይ ሥር ይመጣል፤
በእርሱም አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ"
ይላል።
[13]በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ
ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፤
ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተስፋ
ተትረ ፍርፎ እንዲፈስላችሁ ነው።

## የአሕዛብ አገልጋይ የሆነው ጳውሎስ

[14]ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተ ራሳችሁ
በበጎነት የተሞላችሁ፣ በዕውቀት ሁሉ እንደ
ተሞላችሁና እንዱ ሌላውን ለመምከር ችሎታ
ያላችሁ መሆናችሁን እኔ ራሴ ርግጠኛ ሆኜ
አለሁ። [15]እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ መሠረት፣
እንደ ገና በሳስባችሁ ዘንድ በአንዳንድ
ጕዳዮች ላይ በድፍረት የጻፍሁላችሁ፣

14፥18 ሉቃ2፥52፤ ሐሥ24፥16፤ 2ቆሮ8፥21 14፥19 መዝ34፥14፤ ሮሜ12፥18፤ 15፥2፤ 1ቆሮ7፥15፤ 14፥3-5፤12፥17፡26፤ 2ቆሮ12፥19፤ ኤፌ4፥12፡29፤ 2ጢሞ2፥22፤ ዕብ12፥14 14፥20 ቍ13፤ 14፥15፤ ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ8፥9-12 14፥21 ማቴ5፥29 14፥22 1ዮሐ3፥21 14፥23 ቍ5 15፥1 ሮሜ14፥1፤ 1ተሰ5፥14 15፥2 ሮሜ14፥29፤ 1ቆሮ10፥24 15፥3 መዝ69፥9፤ 2ቆሮ8፥9 15፥4 ሮሜ4፥23፡24 15፥5 ሮሜ12፥16፤ 1ቆሮ1፥10፤ 2ቆሮ13፥11፤ ኤፌ4፥3፤ ፊል2፥2፤ ቈላ3፥14፤ 1ጴጥ3፥8 15፥6 መዝ34፥3፤ ራእ1፥6 15፥7 ሮሜ14፥1 15፥8 ማቴ15፥24፤ ሐሥ3፥25፡26፤ 2ቆሮ1፥20 15፥9 2ሳሙ22፥50፤ መዝ18፥49፤ ማቴ9፥8፤ ሮሜ3፥29 15፥10 ዘዳ32፥43፤ ኢሳ66፥10 15፥11 መዝ117፥1 15፥12 ኢሳ11፥10፤ ራእ5፥5፤ ማቴ12፥21 15፥13 ቍ19፤ ሮሜ14፥17፤ 1ቆሮ2፥4፤ 4፥20፤ 1ተሰ1፥5 15፥14 ኤፌ5፥9፤ 2ቆሮ8፥7፤ 2ጴጥ1፥12 15፥15 ሮሜ12፥3

[T]15፥8 ግሪኩ የመገረዝ ይላል

**14፥21 ወይንን አለመጠጣት፤** መጽሐፍ ቅዱስ ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያን ወይንን (በግሪኩ ,አይኖስ) በተመለከተ፣ የፈላውን ወይም ያልፈላውን የወይን ፍሬ ጭማቂ ይጨምራል፤ ይህም ሁለት ዋና ዋና ሕጎችን ይሰጣል (በገጽ 1547 ላይ፣ «*የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (1) ከፈላና ከሚያሰክር የወይን ጠጅ መታቀብን የሚያዘው ሕግ (ምሳ 23፥31 እና ማብ፤ ተሰ 5፥6 እና ማብ፤ ቲቶ 2፥2 እና ማብ ይመ)። (2) ሌሎችን ሊጎዳ ከሚችል ነገር መታቀብን የሚያዘው ክርስቲያናዊ የፍቅር ሕግ (ከ1ቆሮ 8፥13፤ 10፥27-32 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ የሚያሳስበው የሚያሰክር መጠጥና ስካር የተለመደ በሆነበት ጣዖት አምላኪ ኅብረተሰብ ውስጥ (አይሁዳዊ ባልሆነ ማኅበረሰብ) ሌላውን ክርስቲያን ላለማሰናከል ያልፈላውን ወይን ጠጅ መጠጣት እንኳን የማያስፈልግ እንደሆነ ነው። ያልፈላን ወይን መጠጣት ለአንዳንድ ክርስቲያኖች ምንም ችግር ባይኖርበትም እንኳን፣ ደካማ ክርስቲያኖች የፈላውን ወይን ጠጅ ጠጥተው ራሳቸውን ለጕዳትና ለስካር እንዲዳርጉ በር ሊከፍት ይችላል። ጢሞቴዎስ ይህንኑ ክርስቲያናዊ የፍቅር ሕግ በጥንቃቄ ተከትሏል (1ጢሞ 5፥23 እና ማብ ይመ)።

**15፥3 ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤** ራሳችንን ለማስደሰት ስንል የሌሎችን እምነት ማጣጣል የእግዚአብሔርን ሥራ ያበላሻል (14፥15፡20)፤ ሌሎችን ለመርዳት ራስን መሥዋዕት እያደረጉ መኖር የእግዚአብሔርን መንግሥት ያጠነክራል። ክርስቶስ የራሱን ፍላጎት ሳይሆን የሌሎችን ጥቅም ለማሟላት ምሳሌ በመሆን እንደኖረ ጳውሎስ ያሳያል።

**15፥4 ቀደም ብሎ የተጻፈው ሁሉ፤** የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ስለ እያንዳንዱ የሕይወት ክፍል የተጠቀሱት የእግዚአብሔር የጥበብና የምግባር ሕጎች እንዲሁም ስለ ራሱ፣ ስለ ድነትና ስለ ክርስቶስ ምጽአት የተሰጡት መግለጦች ዘላቂ ዋጋ አላቸው (2ጢሞ 3፥16፤ ማቴ 5፥17 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 144 ላይ፣ «*የብሉይ ኪዳን ሕግ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

16በእግዚአብሔር ወንጌል የክህነት ተግባር፣
ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ
ለመሆን ነው፤ ይኸውም አሕዛብ በመንፈስ
ቅዱስ ተቀድሰው በእግዚአብሔር ዘንድ
ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት እንዲሆኑ
ነው።
17ስለዚህ እግዚአብሔርን በማገልገሌ በክር
ስቶስ ኢየሱስ እመካለሁ። 18በተናገርሁ ትና
በአደረግሁት ነገር አሕዛብ ለእግዚአብ ሔር
እንዲታዘዙ፣ ክርስቶስ በእኔ ሆኖ ከፈጸ መው
በቀር ሌላ ነገር ለመናገር አልደፍርም፤
19ይህም የሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣
በምልክቶችና በታምራት ነበር። በዚህም
ሁኔታ ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ዙሪያ
1ቆሮ ድረስ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአ
1፡7 ለሁ። 20ሌላው በጣለው መሠረት ላይ
እንዳልገነባ ብዬ፣ ክርስቶስ ባልተጠራበት
ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዘወትር ምኞቴ
ነበር። 21ይልቁንም፣

"ስለ እርሱ ያልተነገራቸው ያያሉ፤
ያልሰሙም ያስተውላሉ" ተብሎ
እንደ ተጻፈ ነው።

22በዚህም ምክንያት ወደ እናንተ
እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ።

### ሮምን ለመጐብኘት የጳውሎስ ዕቅድ

23አሁን ግን በእነዚህ አካባቢዎች
የምሠራው ስለሌለ፣ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ
እናንተን ለማየት እናፍቅም ስለ ነበር፣
24ይህን ዕቅድ ወደ እስጳንያ በምሄድበት ጊዜ
ልፈጽ መው አስባለሁ። በማልፍበትም ጊዜ
ልጐበ ኛችሁና ከእናንተ ጋር ለጥቂት ጊዜ
ቈይቼ ናፍቆቴን ከተወጣሁ በኋላ በጕዞዬ
እንድም ትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ።25አሁን
ግን በዚያ የሚገኙትን ቅዱሳን ለማገልገል
ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ነኝ። 26ምክንያ
ቱም መቄዶንያና አካይያ፣ በኢየሩሳሌም
ካሉት ቅዱሳን መካከል የሚገኙትን ድኾች
ለመርዳት ተነሣሥተዋልና። 27ርዳታ ለማ
ድረግ ወደዋል፤ በርግጥም ባለ ዕዳዎቻቸው
ናቸው። አሕዛብ የአይሁድ መንፈሳዊ በረ
ከት ተካፋዮች ከሆኑ፣ ያገኙትን ምድራዊ
በረከት ከአይሁድ ጋር ይካፈሉ ዘንድ የእ
ነርሱ ባለ ዕዳዎች ናቸው። 28ስለዚህ ሥራ
ውን ከጨረስሁና ይህን ፍሬ መቀበላቸውን
ካረጋገጥሁ በኋላ ወደ እስጳንያ እሄዳለሁ፤
እግረ መንገዴንም እናንተን አያለሁ።
29ወደ እናንተም ስመጣ፣ በክርስቶስ በረከት
ሙላት እንደምመጣ በውቃለሁ።
30ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር
በመጸለይ የተጋድሎዬ አጋር እንድ ትሆኑ
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ
ፍቅር እለምናችኋለሁ። 31በይሁዳ ካሉት
ከማያምኑት እጅ እንድድንና በኢየሩሳሌም
ያለው አገልግሎቴም በዚያ ባሉት ቅዱሳን
ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩልኝ፤
32ይኸውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ
እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም
ጋር እንድታደስ ነው። 33የሰላም አምላክ
ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

### የግል ሰላምታ

16 በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገል
ጋይ[ሀ] የሆነችውን እኅታችንን ፌቤ
ንን ዐደራ እላችኋለሁ። 2ለቅዱሳን ተገቢ
በሆነው አቀባበል በጌታ እንድትቀበሏትና
ከእናንተም የምትፈልገውን ማንኛውንም
ርዳታ እንድታደርጉላት አሳስባችኋለሁ፤
ለብዙ ሰዎችና ለእኔም ጭምር ታላቅ ድጋፍ
ነበረችና።
3በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ
ለሚያገለግሉት ለጵርስቅላና[ለ] ለአቂላ
ሰላምታ አቅርቡልኝ። 4እነርሱም ለእኔ
ሲሉ ሕይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው
ሰጡ፤ እኔ ብቻ ሳልሆን የአሕዛብ አብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ ያመሰግኗቸዋል።
5በእነርሱ ቤት ላለች ቤተ ክርስቲያንም
ሰላምታ አቅርቡልኝ።

15፥16 ቍ 19፡ ኢሳ66፥20፤ ሐሥ9፥15፤ ሮሜ1፥1 15፥17 ፊል3፥3፤ ዕብ2፥17 15፥18 ሐሥ15፥12፤ 21፥19፤ ሮሜ1፥5፤ 16፥26 15፥19 ቍ13፡ ዮሐ4፥48፡ ሐሥ22፥17-21፤ 19፥11፤ 2ቆሮ2፥12 15፥20 ሮሜ1፥15፡ 2ቆሮ10፥15፥16 15፥21 ኢሳ52፥15 15፥22 ሮሜ1፥13 15፥23 ሐሥ19፥21፤ ሮሜ1፥10፥11 15፥24 ቍ 28፤ 1ቆሮ16፥6፡ ቲቶ3፥13 15፥25 ሐሥ19፥21፤ 24፥17፤ 9፥13 15፥26 ሐሥ16፥9፤ 18፥12፤ 24፥17 15፥27 1ቆሮ9፥11 15፥28 ቍ 24 15፥29 ሮሜ1፥10፥11 15፥30 2ቆሮ1፥11፤ ገላ5፥22፤ ቈላ1፥8፤ 4፥12 15፥31 ቍ 25፤ ሐሥ9፥13፡ 24፥17፡ 2ቆሮ1፥10፤ 2ተሰ3፥2፤ 2ጢሞ3፥11፡ 2ጴጥ2፥9 15፥32 ሐሥ18፥21፤ ሮሜ1፥10፥13፡ 1ቆሮ16፥18፤ ፊልሞ1፥7 15፥33 ሮሜ16፥20፤

15፥33 2ቆሮ13፥11፤ ፊል4፥9፡ 1ተሰ5፥23፤ 2ተሰ3፥16፡ ዕብ13፥20 16፥1 ሐሥ18፥18፡ 2ቆሮ3፥1
16፥2 ሐሥ9፥13፤ ፊል2፥29 16፥3 ቍ 7፡9፡10፡ ሐሥ18፥2፡ ሮሜ8፥1፥39፤ 1ቆሮ1፥30፤ 2ቆሮ5፥17፤ ገላ1፥22፤ 5፥6፤ ኤፌ1፥13፤ ፊል2፥25 16፥5 ሐሥ2፥9፤ 1ቆሮ16፥15፡ 19፤ ቈላ4፥15፤ ፊልሞ1፥2

[ሀ]16፥1 ወይም *ዲያቆን*
[ለ]16፥3 በግሪክ *ጵርስቃ* *የጵርስቅላ* ተለዋጭ ስም ነው፡፡

**15፥17 እመካለሁ፤** በትሕትና መንፈስና እግዚአብሔርን በሚያመሰግን ሁኔታ እስከሆነ ድረስ እግዚአብሔር በሕይወታችን የሠራውን ሥራ በደስታና በአድናቆት መግለጽ ስሕተት አይደለም፡፡ መመካት የሰው ቍጥር ስለበዛ ሳይሆን ከእውነተኛ ሥራና ከኀይል ከሚገለጸው መንፈስ በሚመነጨውና የመታዘዝን እምነት በቃልና በሥራ በሚገልጠው አገልግሎት መሆን አለበት (ቍ 18-19)፡፡

**20 ክርስቶስ ባልተጠራበት ስፍራ፤** የጳውሎስ ...ሕ የወንጌል ስርጭትን ያማከለ ነበር፡ ...ታ ባልደረሰባቸው አካባቢዎች የበለጠ ...ን ሲሆን፡ ይህንንም በማድረጉ ወንጌልን ...ስን ለመቀበል ያልቻሉትን ወገኖች ...ል (ቍ 21)፡፡

**...ስቶስ በረከት ሙላት፤** የጳውሎስ አገልግሎት በክርስቶስ የበረከት፣ የኀይል፣ የጸጋና የሀልዎት ሙላት የታጀበ ነበር፡፡ እርሱ በሚያገለግልበት ቦታ ሁሉ ሌሎች የእነዚህ ሙላቶች ተካፋይ ይሆናሉ፡፡ ጌታንና አብያተ ክርስቲያናቱን የምናገለግል እኛም እነዚህ ሙላቶች በአገልግሎታችን እንዲገለጡ መሻት አለብን፡፡

**16፥1 ፌበን፤** ይህን መልእክት ለሮሜ ሰዎች ያደረሰች ፌበን ሳትሆን አትቀርም፡፡ በክንክራኦስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ (ወይም ዲያቆን) የነበረች ሲሆን ድኾችን፣ የታመሙትንና የተቸገሩትን በመርዳት እንዲሁም ጳውሎስንና የመሳሰሉትን የወንጌል መልእክተኞች በማገዝ ታገለግል ነበር፡፡ ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ከስምንት ለማያንሱ ሴቶች ሰላምታ ማቅረቡ፣ ሴቶች በአብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት ውስጥ ጉልህ ሚና እንደነበራቸው ምስክር ነው፡፡

ከእስያ አገር ለመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ
ለተመለሰው፣ ለወዳጄ ለአጤኔጦን ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
6ለእናንተ ብዙ ለደከመችው ለማርያ ሰላ
ምታ አቅርቡልኝ።
7ከእኔ ጋር ታስረው ለነበሩት ዘመዶቼ
ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሰላምታ
አቅርቡልኝ፤ እነርሱ በሐዋርያት መካከል
ስመጥሮችና በክርስቶስ በማመንም እኔን
የቀደሙ ናቸው።
8በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
9በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራው ለኢሩ
ባኖንና ለውድ ወዳጄ ለስንጣክን ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
10በክርስቶስ ያለው እምነቱ ተፈትኖ
ለተመሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ
አቅርቡልኝ፤
ከአርስጣባሉ ቤተ ሰብ ለሆኑትም ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
11ለዘመዴ ለሄሮድዮና ሰላምታ
አቅርቡልኝ፤
በጌታ ላሉት ለንርቀሱ ቤተ ሰቦች
ሰላምታ አቅርቡልኝ።
12በጌታ ሆነው በትጋት ለሚሠሩት
ሴቶች፣ ለፕሮፌሞናና ለጢሮፌሞሳ ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
በጌታ ሆና እጅግ ለደከመችው ለሌላዋ
ሴት፣ ለተወደደችው ለጠርሲዳ ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
13በጌታ ለተመረጠው ለሩፎንና የእኔም
እናት ለሆነችው ለእናቱ ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ።
14ለአስቀሪጦንና ለአፍለሶንጳ፣ ለሄሮሜን፣
ለጳጥሮባን፣ ለሄርማን፣ ከእነርሱም ጋር
ላሉት ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ።
15ለፍሌጎን፣ ለዩልያ፣ ለኔርያና ለእኅቱ፣
እንዲሁም ለአልንጦን፣ ከእነርሱም ጋር
ላሉት ቅዱሳን ሰላምታ አቅርቡልኝ።
16በቅዱስ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ።
የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
17ወንድሞች ሆይ፤ መለያየትን
ከሚፈጥሩትና የተማራችሁትን
ትምህርት በመቃወም በጕዞአችሁ
መሰናክል ከሚያደርጉት እንድትጠነቀቁ
አሳስባችኋለሁ፤ ከእነርሱም ራቁ። 18እንደ
እነዚህ ያሉት ሰዎች የሚያገለግሉት
ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን፣
የራሳቸውን ሆድ ነው፤ በለሰለሰ አንደ
በታቸውና በሽንገላ፣ የዋሆችን ያታልላሉ።
19የእናንተን ታዛዥነት ሁሉም ሰምተዋል፤
በዚህም እኔ እጅግ ተደስቻለሁ። ሆኖም በጎ
ስለ ሆነው ነገር ጥበበኞች፣ ክፉ ስለ ሆነውም
የዋሆች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ።
20የሰላም አምላክ፣ ሰይጣንን ከእግራችሁ

16፥7 ቆላ3፥11፤21፤ ቈላ4፥10፤ ፊሞ1፥23
16፥9 ቆላ3
16፥10 ቆላ3፥ ሐዋ11፥14
16፥11 ቆላ7፥21፤ ሐዋ11፥14
16፥13 ማር15፥21፤ 2ዮሐ1
16፥15 ቆላ2፥14፤ ሐዋ9፥13
16፥16 1ቆሮ16፥20፤ 2ቆሮ13፥12፤ 1ተሰ5፥26፤ 1ጴጥ5፥14
16፥17 ማቴ18፥15-17፤ ገላ1፥8፡9፤ 1ቆሮ5፥11፤ 2ተሰ3፥6፡14፤ 1ጢሞ1፥3፤ 6፥3፤ 2ጢሞ3፥5፤ ቲቶ3፥10፤ 2ዮሐ10
16፥18 2ሳሙ15፥6፤ መዝ12፥2፤ ኢሳ30፥10፤ ሮሜ14፥18፤ ፊል3፥19፤ ቈላ2፥4
16፥19 ሮሜ1፥8፤ 1ቆሮ14፥20
16፥20 ዘፍ3፥15፤ ማቴ4፥10፤ ሮሜ15፥33፤ 2ቆሮ13፥14፤ ገላ6፥18፤ 1ተሰ5፥28፤ ራእ22፥21

**16፥7 በሐዋርያት መካከል ስመጥሮች፤** አንዲራኒቆንና ዩልያን ሐዋርያት ተብለው ተጠርተዋል። በዚህ ስፍራ "ሐዋርያት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመጀመሪያዎቹን ሐዋርያት ሳይሆን ማንኛውንም ተጓዥ መልእክተኛ ወይም ሚስዮናዊ ነው (1ቆሮ 9፥1-2፤ 2ቆሮ 8፥23፤ 12፥2፤ ፊል 2፥25 ይመ፤ ከሐዋ 14፥4 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 1866 ላይ፣ "*የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**16፥17 ከሚያደርጉት እንድትጠነቀቁ፤** ጳውሎስ በመልእክቱ ማጠቃለያ ላይ የእርሱንና የሌሎችን ሐዋርያት "ትምህርት" በማጣመም ቤተ ክርስቲያንን አደጋ ላይ ከሚጥሉ ሰዎች የሮም ቤተ ክርስቲያን ነቅታ እንድትጠብቅ ያስጠነቅቃል። ከሐሰት አስተምህሮ አቀንቃኞችና ከአገልግሎታቸው እንዲጠነቀቁና እንዲርቁ ያሳስባቸዋል። እነዚህ ሰዎች የሕግ ተጻራሪዎች ናቸው፤ ስለሆነም ድነት በጸጋ ስለሆነ፣ ለድነት ለሚያበቃው እምነት የግድ ክርስቶስን መታዘዝ አያስፈልገውም ብለው ያስተምራሉ (ከ6፥1-2፤ ከ2ቆሮ 4፥2፤ 11፥3፤ ከኤፌ 4፥14፤ ከራእ 2፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 1519 ላይ፣ "*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። እነዚሁ አስተማሪዎች አንድ ሰው በኀጢአት እየኖረና የእግዚአብሔርን ግብረገባዊ ሕግ ንቆ በመተው የዘላለም ሕይወት ሊኖረው ይችላል ብለው ያምኑ ነበር። እነዚህ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች እንደበተ ርቱዕ፣ በለሰለሱ ቃላትና በሚያባብል ንግግር የሚናገሩ (ከይሁ 16 ጋር ያነጻጽሩ) ሲሆኑ፣ በሥራቸው ግን አታላዮች ነበሩ።

**16፥19 ክፉ ስለሆነውም የዋሆች፤** "የዋህ" (በግሪኩ አኪሪዮስ) የሚለው ቃል "ያልተቀላቀለ" ወይም "ንጹሕ" ማለት ሲሆን፣ አእምሮው ለክፋት ገና ያልተጋለጠ ወይም ከዓለም እሴት ጋር ገና ያልተደባለቀ ቀና ሕፃን ማለትም ይሆናል (ከ1ቆሮ 14፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የክርስቲያን ልጆች ፈተናን መቋቋም ይችሉ ዘንድ ለኀጢአት፣ ለርኩሰት፣ ለነውርና ለሰይጣናዊ ነገሮች መጋለጥ አለባቸው ብለው ከሚያምኑት አንዳንድ ሰዎች አስተሳሰብ ጋር የሚቃረን ነው። አንዳንድ ሰዎች ልጆች ከርኩሰት መራቅ የለባቸውም ብለው ያምናሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ከሆነ ይህ ፍልስፍና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚቃረን ነው፤ ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ሰው ክፉውንና መልካሙን ያውቅ ዘንድ ዕድል ሊሰጠው ይገባል ከሚለው የሰይጣን ምኞትም ጋር የሚስማማ (ዘፍ 3፥5)።

(2) ለሰይጣን መንገድ አዘውትሮ በመጋለጥ ክፉትን መሥራት ብዙዎችን ከእምነትና ከመታዘዝ መንገድ ያስወጣል። ሎጥ ቤተሰቡን በሞላ ካጣ በኋላ ከመራራ ሐዘን ጋር ይህንን እውነት ተረድቶታል (ዘፍ 13፥12-13፤ 19፥1-38)። መጽሐፍ ቅዱስ "መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን ጠባይ ያበላሻል" (1ቆሮ 15፥33) በማለት የሚያስጠነቅቅ ሲሆን፤ ከዚህም የተነሣ "... ኢየሱስ ክርስቶስ ... ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ ... ራሱን ሰጠ" (ገላ 1፥3-4) በማለትም ይናገራል። ልጆችን ርኩሰት ባለበት ሁኔታ ወይም ለርኩሰት ተጽዕኖ ማጋለጥ እንደሚያስፈልግ የሚያምኑ ሰዎች በማቴ 18፥16 ላይ የቀረበውን የኢየሱስን ማስጠንቀቂያ በመተላለፍ ተጠያቂ ይሆናሉ።

(3) አማኞች ልጆቻቸው ለኀጢአት ማታለልና ለዚህ ትውልድ ጠማማነት እልፈው እንዳይሰጡ የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ መከላከል ይገባቸዋል። ልጆቻችንን ከመጠበቅ ቸል ማለት ክፉ ለሆነው ነገር የዋህ እንዲሆኑ ለሚፈልገው ለመንፈስ ቅዱስ ቦታ አለመስጠት ነው።

በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል።
የጌታችን የኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር
ይሁን።
[21]አብሮኝ የሚሠራው ጢሞቴዎስ፣
እንዲሁም ዘመዶቼ የሆኑት ሉቂዮስ፣
ኢያሶንና ሱሲጴጥሮስ ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል።
[22]ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ፣
በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ።
[23]በመልካም መስተንግዶው እኔና
በዚህ የምትገኘዋ መላዋ ቤተ ክርስቲያን
ደስ የምንሰኝበት ጋይዮስ፣ ሰላምታ
ያቀርብላችኋል።
የከተማዪቱ ግምጃ ቤት ሹም የሆነው
ኤርስጦስ፣ ወንድማችንም ቍአስጥሮስ
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። [24]የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር
ይሁን፤ አሜን።*
[25-26]በዘላለማዊ አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች
ሁሉ አምነው እንዲታዘዙ፣ በነቢያት
መጻሕፍት አሁን በተገለጠው፣ ላለፉት
ረጅም ዘመናት ተሰውሮ በነበረው ምስጢር
መገለጥ መሠረት፣ በአስተማርሁት ወንጌልና
በኢየሱስ ክርስቶስ መሰበክ ሊያጸናችሁ
ለሚችለው፣ [27]እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነ
አምላክ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለዘላለም
ክብር ይሁን፤ አሜን።

16፥21 ቍ7፥11፤ ሐሥ16፥1፤ 13፥1፤ 17፥5
16፥23 ሐሥ19፥22፥29፤ 2ጢሞ4፥20
16፥25 ኢሳ48፥6፤ ሮሜ2፥16፤ 2ቆሮ9፥8፤ ኤፌ1፥9፤ 3፥20፤ ቈላ1፥26፥27፤ 2፥2፤ 1ጢሞ3፥16፤ 2ጢሞ2፥8፤ 3፥3-6፥9፤ ይሁ24
16፥26 ሮሜ1፥2፥5
16፥27 ሮሜ11፥36

*16፥24 ቍጥር 24 የሚገኘው በአንዳንድ ቅጆዎች ብቻ ነው።

# የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች

## (ሀ) የቤተክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች

| ስጦታ | ትርጉም | ማገናዘቢያ ጥቅሶች | ግልጽ ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|
| ሐዋርያ (ውስን) | ቤተክርስቲያን ለመመሥረትና የወንጌልን ትክክለኛ መልእክት ለማስተማር ከሙታን በተነሣው ጌታ የተሾመ | ሐሥ4፥33-37፤ 5፥12፡18-42፤ 6.6፤ 8፥14፡18፤ 9፥27፤ 11፥1፤ 15፥1-6፡22-23፤ 16፥4፤ 1ቆሮ9፥5፤ 12፥28-29፤ ገላ1፥17፤ ኤፌ2፥20፤ 4፥11፤ ይሁ17 | 12 ሐዋርያት፤ ማቴ10፥2፤ ማር3፥14፤ ሉቃ6፥13፤ ሐሥ1፥15-26፤ ራእ21፥14፤ ጳውሎስ ሮሜ1፥1፤ 11፥13፤ 1ቆሮ1፥1፤ 9፥1-2፤ 15፥9-10፤ 2ቆሮ1፥1፤ ገላ1፥1፤ 1ጢሞ2፥7፤ ጴጥሮስ 1ጴጥ1፥1፤ 2ጴጥ1፥1 |
| ሐዋርያ (ማንኛውም) | ለሚስዮናዊነትም ሆነ ለሌላ ለተለየ ኀላፊነት የተሾመ ማንኛውም መልእክተኛ | ሐሥ13፥1-3፤ 1ቆሮ12፥28-29፤ ኤፌ4፥11 | በርናባስ፤ ሐሥ14፥4፡14 እንድራኒቆንና ዩልያን፤ ሮሜ16፥7 ቲቶና ሌሎችም፤ 2ቆሮ8፥23 አፍሮዲጡ፤ ፊል2፥25 የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ ገላ1፥19 |
| ነቢይ | ከእግዚአብሔር መልእክትን ለቤተ ክርስቲያን በማምጣት በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት የተናገረና የሚናገር እንዲሁም ትኩረቱና ዋነኛው የልቡ ተነሣሥቶ መንፈሳዊ ሕይወትና የቤተ ክርስቲያን ቅድስና የሆነ ሰው | ሮሜ12፥6፤ 1ቆሮ12፥10፤ 14፥1-33፤ ኤፌ4፥11፤ 1ተሰ5፥20-21፤ 1ጢሞ1፥18፤ 1ጴጥ4፥11፤ 1ዮሐ4፥1-3 | ጴጥሮስ፤ ሐሥ2፥14-40፤ 3፥12-26፤ 4፥8-12፤ 10፥34-44፤ ጳውሎስ፤ ሐሥ13፥1፡16-41 በርናባስ፤ ሐሥ13፥1 ስምዖን፤ ሐሥ13፥1 ሉክዮስ፤ ሐሥ13፥1 ምናሔ፤ ሐሥ13፥1 አጋቦስ፤ ሐሥ11፥27-28፤ 21፥10 ይሁዳና ሲላስ፤ ሐሥ15፥32 ዮሐንስ፤ ራእ1፥1፡3፤ 10፥8-11፤ 11፥18 |
| ወንጌላዊ | ወንጌልን ላልዳኑት እንዲያውጅ እግዚአብሔር የነፍሳት ሽክም የሰጠው ሰው | ኤፌ4፥11 | ፊልጶስ፤ ሐሥ8፥5-8፡26-40፤ 21፥8 ጳውሎስ፤ ሐሥ26፥16-18 |
| መጋቢ (ሽማግሌ ወይም ኤጲስቆጶስ) | የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ፍላጎት በማሟላት የበላይ ሆኖ እንዲመራ የተመረጠና ስጦታው ያለው ሰው | ሐሥ14፥23፤ 15፥1-6፡22-23፤ 16፥4፤ 20፥17-38፤ ሮሜ12፥8፤ ኤፌ4፥11-12፤ ፊል1፥1፤ 1ጢሞ3.1-7፤ 5.17-20፤ ቲቶ1.5-9፤ ዕብ13.17፤ 1ጴጥ5.1-5 | ጢሞቴዎስ፡ 1ጢሞ1.1-4፤ 4.12-16፤ 2ጢሞ1.1-6፤ 4.2፡5 ቲቶ1.4-5 ጴጥሮስ፡ 1ጴጥ5.1 ዮሐንስ፡ 1ዮሐ2.1፡12-14 ጋይዮስ፡ 3ዮሐ1-7 |

# የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች

## (ሀ) የቤተክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች

| ስጦታ | ትርጉም | ማገናዘቢያ ጥቅሶች | ግልጽ ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|
| አስተማሪ | ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የእግዚአብሔርን ቃል የማብራራትና የመግለጽ ተሰጥኦ ያለው ሰው | ሮሜ12:7፤ ኤፌ4:11-12፤ ቈላ3:16፤ 1ጢሞ3:2፤ 5:17፤ 2ጢሞ2:2-24 | ጳውሎስ፡ ሐሥ15:35፤ 20:20፤ 28:31፤ ሮሜ12:19-21፤ 13:8-10፤ 1ቆሮ4:17፤ 1ጢሞ1:5፤ 4:16፤ 2ጢሞ1:11፤<br>ባርናባስ፡ ሐሥ15:35፤<br>አጵሎስ ሐሥ18:25-28፤<br>ጢሞቴዎስ፡ 1ቆሮ4:17፤ 1ጢሞ1:3-5፤ 4:11-13፤ 6:2፤ 2ጢሞ4:2፤<br>ቲቶ2:1-3:9-10 |
| ዲያቆን | ለምእመናን ተግባራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ የተመረጠና ስጦታው ያለው ሰው | ሐሥ6:1-6፤ ሮሜ12:7፤ ፊል1:1፤ 1ጢሞ3:8-13፤ 1ጴጥ4:11 | ሰባት ዲያቆናት፡ ሐሥ6:5<br>ፌቤን፡ ሮሜ16:1-2 |
| ረዳት | የተለያዩ የርዳታ አገልግሎቶችን ለማከናወን ስጦታ ያለው ሰው | 1ቆሮ12:28 | ጳውሎስ፡ ሐሥ20:35፤<br>ልድያ፡ ሐሥ16:14-15፤<br>ጋይዮስ፡ 3ዮሐ5-8 |
| አስተዳዳሪ | የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ለመምራትና በበላይ ሆኖ ለመቈጣጠር ስጦታው ያለው ሰው | 1ቆሮ12:7፤ ኤፌ4:11-12፤ 1ጢሞ3:1-7፤ ዕብ13:7-17:24 | ጴጥሮስ፡ ሐሥ6:3-4፤ 11:1-18<br>ጳውሎስ፡ ሐሥ20:17-35፤ 1ቆሮ11:23-24፤ 14፤ 16:1-9 |
| አበረታች | ሌሎች ክርስቲያኖች ጠለቅ ያለ እምነትና ለክርስቶስ የተሰጠ ሕይወት እንዲኖራቸውና ከዓለምም ፍጹም ተለይተው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በሙላት እንዲታይባቸው የማበረታታት ስጦታ ያለው ሰው | ሮሜ12:8፤ 1ቆሮ14:3፤ 1ተሰ5:11:14-22፤ ዕብ10:24-25 | በርናባስ፡ ሐሥ11:23-24፤ 14:22<br>ጳውሎስ፡ ሐሥ14:22፤ 16:40፤ 20:1፤ ሮሜ8:26-39፤ 12:1-2፤ 2ቆሮ6:14—7:1፤ ገላ5:16-26<br>ይሁዳና ሲላስ፡ ሐሥ15:32፤ 16:40<br>ጢሞቴዎስ፡ 1ተሰ3:2፤ 2ጢሞ4:2፤<br>ቲቶ፡ ቲቶ2:6:13<br>ጴጥሮስ፡ 1ጴጥ5:1-2<br>ዮሐንስ፡ 1ዮሐ2:15-17፤ 3:1-3 |
| ሰጪ | የእግዚአብሔርን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት ሀብትና ንብረታቸውን በነጻ ለመስጠት ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች | ሐሥ2:44-45፤ 4:34-35፤ 11:29-30፤ 1ቆሮ16:1-4፤ 2ቆሮ8-9፤ ኤፌ4:28፤ 1ጢሞ6:17-19፤ ዕብ13:16፤ 1ዮሐ3:16-18 | በርናባስ፡ ሐሥ4:36-37<br>የመቄዶንያ ክርስቲያኖች፡ ሮሜ15:26-27፤ 2ቆሮ8:1-5፤<br>የአካይ ክርስቲያኖች፡ ሮሜ15:26-27፤ 2ቆሮ9:2 |

# የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች

## (ሀ) የቤተክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች

| ስጦታ | ትርጒም | ማገናዘቢያ ጥቅሶች | ግልጽ ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|
| አጽናኝ | በሐዘን ላይ ላሉ ሰዎች በመራራት የማጽናናት ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች | ሮሜ12፡8፤ 2ቆሮ1፡3-7 | ጳውሎስ፡ 2ቆሮ1፡4<br>የዕብራውያን ክርስቲያኖች፡ ዕብ10፡34<br>የተለያዩ ክርስቲያኖች፡ ቈላ4፡10-11<br>ዶርቃ፡ ሐሥ9፡36-39 |

## (ለ) በእያንዳንዱ አማኝ በኩል የሚገለጡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

| ስጦታ | ትርጒም | ማገናዘቢያ ጥቅሶች | ግልጽ ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|
| የጥበብን ቃል መናገር | በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ላይ የእግዚአብሔርን ቃልና ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መናገር | ሐሥ6፡3፤ 1ቆሮ12፡8፤ 13፡2፡9፡12 | እስጢፋኖስ፡ ሐሥ6፡10<br>ያዕቆብ፡ ሐሥ15፡13-21 |
| የዕውቀትን ቃል መናገር | ስለ ሰዎች፣ ስለ ሁኔታዎች ወይም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነታ የተሰወረውን በመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት ገልጾ መናገር | ሐሥ10፡47-48፤ 13፡2፤ 15፡7-11፤ 1ቆሮ12፡8፤ 13፡2፡9፡12፤ 14፡25 | ጴጥሮስ፡ ሐሥ5፡9-10 |
| እምነት | እግዚአብሔር ታምራትን እንደ ሚያደርግ ክርስቲያን ያምን ዘንድ የሚያስችል በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሚተላለፍ ልዩ ጸጋ ተፈጥሮአዊ መተማመን ነው | ማቴ21፡21-22፤ ማር9፡23-24፤ 11፡22-24፤ ሉቃ17፡6፤ ሐሥ3፡1-8፤ 6፡5-8፤ 1ቆሮ12፡9፤ 13፡2፤ ያዕ5፡14-15 | አንድ መቶ አለቃ፡ ማቴ8፡5-10፣<br>አንዲት ሕመምተኛ ሴት ማቴ9፡20-22፣<br>ሁለት ዐይነስውራን፡ ማቴ9፡27-29፣<br>አንዲት ከነዓናዊት ሴት፡ ማቴ15፡22-28<br>አንዲት ኀጢአተኛ ሴት፡ ሉቃ9፡36-50፣<br>ለምጻም ሰው፡ ሉቃ17፡11-19 |
| ፈውስ | ከመለኮት በሆነ ጸጋ ተፈጥሮአዊ አሠራር፣ አንድን ሰው ጤናማ አካል እንዲኖረው ማድረግ | ማቴ4፡23-24፤ 8፡16፤ 9፡35፤ 10፡1፡8፤ ማር1፡32-34፤ 6፡13፤ 16፡18፤ ሉቃ4፡40-41፤ 9፡1-2፤ ዮሐ 6፡2፤ 14፡12፤ ሐሥ4፡30፤ 5፡15-16፤ 19፡11-12፤ 1ቆሮ12፡9፡28፡30 | ኢየሱስ፡ በገጽ 1657 ላይ፥ "የኢየሱስ ታምራት" በሚል ርእስ የቀረበውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ። ሐዋርያት፡ በገጽ 1655 ላይ፣ "የሐዋርያት ታምራት" በሚል ርእስ የቀረበውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ። |

# የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች

## (ለ) በእያንዳንዱ አማኝ በኩል የሚገለጡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

| ስጦታ | ትርጒም | ማጣቀሻ ጥቅሶች | ግልጽ ምሳሌዎች |
|---|---|---|---|
| ታምራትን የማድረግ ኀይል | አጋንንትን ለማስወጣትና የተፈጥሮ ሂደትን ለመቀየር የሚያስችል ከመለኮት የሆነ ዲበ ተፈጥሮአዊ ኀይል | ማቴ4፥23-24፤ 8፥16፤ 10፥1:8፤ 13፥54፤ ማር1፥32-33:39፤ 3፥15፤ 6፥13፤ 16፥17፤ ሉቃ4፥40-41፤ 9፥1፤ 10፥17፤ ዮሐ7፥3፤ 10፥25:32፤ 14፥11፤ 15፥24፤ ሐሥ2፥22:43፤ 4፥30፤ 5፥15-16፤ 6፥8፤ 8፥6-7፤ 14፥3፤ 15፥12፤ 19፥11-12፤ ሮሜ15፥19፤ 1ቆሮ12፥10:29፤ 2ቆሮ12፥12፤ ገላ3፥5 | ኢየሱስ፡ በገጽ 1657 ላይ፣ "የኢየሱስ ታምራት" በሚል ርእስ የቀረበውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ። ሐዋርያት፡ በገጽ 1655 ላይ፣ "የሐዋርያት ታምራት" በሚል ርእስ የቀረበውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ። |
| ትንቢት | በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከእግዚአ ብሔር ዘንድ ቃልን፣ ማስጠንቀቂያን፣ መጽናናትንና መገለጥን ለማምጣት የሚያስችል ጊዜያዊ ልዩ ስጦታ | ሉቃ12፥12፤ ሐሥ2፥17-18፤ 1ቆሮ 12፥10፤ 13፥9፤ 14፥1-33፤ ኤፌ4፥11፤ 1ተሰ5፥20-21፤ 2ጴጥ1፥20-21፤ 1ዮሐ 4፥1-3 | ኤልሳቤጥ፡ ሉቃ1፥40-45 ማርያም፡ ሉቃ1፥46-55 ዘካርያስ፡ ሉቃ1፥67-79 ጴጥሮስ፡ ሐሥ2፥14-40፤ 4፥8-12 በኤፌሶን የነበሩ ዐሥራ ሁለት ወንድሞች ሐሥ19፥6፤ የፊልጶስ አራት ሴቶች ልጆች ሐሥ21፥9፤ አጋቦስ ሐሥ21፥10ጠ11 |
| መናፍስትን መለየት | ትንቢቶችና መልእክቶች ከመንፈስ ቅዱስ መሆናቸውንና አለመሆና ቸውን ለመለየት የሚረዳ ልዩ ስጦታ | 1ቆሮ12፥10፤ 14፥29 | ጴጥሮስ፡ ሐሥ8፥18-24 ጳውሎስ፡ ሐሥ13፥8-12፤ 16፥16-18 |
| በልሳኖች መናገር | የራስን መንፈስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር በማድረግ በማያውቁትና ባልተማሩት ቋንቋ ለመናገር ራስን ከፍቶ መልቀቅ | 1ቆሮ12፥10:28:30፤ 13፥1፤ 14፥1-40 | ደቀ መዛሙርት፡ ሐሥ2፥4-11 ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ፡ ሐሥ 10፥44-45፤ 11፥17 የኤፌሶን አማኞች፡ ሐሥ19፥2-7 ጳውሎስ፡ 1ቆሮ14፥6:15:18 |
| በልሳኖች የተነገረውን መተርጐም | በልሳኖች የተነገረውን ለመተርጐም የሚያበቃ ልዩ ስጦታ | 1ቆሮ12፥10:30፤ 14፥5:13:26-28 | |